# 15

# አምሳያዎች [Types]

አምሳያዎች ጠቃሚና ውስብስብ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ክፍል ናቸው። አምሳያዎችን አስመልክቶ በሚነሡ ጥያቄዎች ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ብዙ ጊዜ አይስማሙም። ይሁንና ምሳሌዎች ሊታወቁ የሚገባቸውንና ዋጋ ያላቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች ውብ በሆነ አኳኋን ያቀርቧቸዋል።

የተለያዩ ዓይነት አምሳያዎች አሉ፡- "ሰዎች" (አዳም፥ ሙሴ፥ ኤልያስ፥ መልከጼዴቅ የመሳሰሉት)፥ "ሁነቶች" (የነሐሱን እባብ መሰቀልና የጥፋት ውኃን የመሳሰሉት)፤ "የተለያዩ ነገሮች-ቁሳቁሶች" (መሰዊያ፥ ጠቦት፥ ዕጣን)፤ "ሥርዓት ወይም መታሰቢያዎች" (የፋሲካና ሌሎች በዓላት)፤ "ስፍራዎች" (ከነዓንና ኢየሩሳሌም) እና "ሹመት ወይም አገልግሎት" (ነቢይና ካህን)።

አምሳያ በብሉይ ኪዳን የአዲስ ኪዳንን መንፈሳዊ እውነታ በጥላነት የሚያመለክት መለኮታዊ ትልም ነው ልንል እንችላለን። ይህን አስመልክቶ ሦስት ዋንኛ ነጥቦች እነሆ፡-

1. *አምሳያ በመለኮት የታለመ ነው።* እግዚአብሔር በአምሳያና በፍጻሜው መካከል ግንኙነት እንዳለ ማመልከቱን ከመጽሐፍ ቅዱስ ማረጋገጥ አለብን። አዲስ ኪዳን ከብሉይ ኪዳን ጋር ስላለው ተዛምዶ በሚናገርበት ጊዜ ስለ ሁኔታው አጠራጣሪ ነገር ሊኖር አይችልም። ምንም የማይጠቅስ ከሆነ ግን፥ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል። እንዲህ ባለው ሁኔታ የአምሳያው ግንኙነት ለጥርጣሬ በር በማይከፍት መልኩ በጣም ግልጥ ሆኖ መታየት አለበት።

በብሉይና በአዲስ ኪዳናት መካከል በብዙ ነገሮች መለስተኛ ተመሳሳይነቶች ይኖሩ ይሆናል። እነዚህንም ተመሳሳይነቶች ጥሩ ምናባዊ ግንዛቤ ያላቸው ሰዎች ከሌሎቹ በተሻለ አኳኋን ሊያገኟቸው ይችላሉ። ይሁን እንጂ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ በጭራሽ በይሆን ይሆናል ላይ ሊመሠረት አይችልም። እንዲያው በአጋጣሚ ሳይሆን፥ በጣም ግልጥ የሆኑ አምሳያ ማረጋገጫዎችን ከግምት ማስገባትና በምሳሌነት መቀበል አለብን።

2. *አምሳያ የሚገኘው በብሉይ ኪዳን ሲሆን፥ ፍጻሜው በአዲስ ኪዳን ነው።* አምሳያን ከሌሎቹ ዘይቤዎች፥ ማለት መንፈሳዊ ትርጉማቸው ለተመሳሳይ ድርጊትና ጊዜ ሊውል ከሚችለው ከምስልና ምሳሌያዊ አነጋገሮች የሚለየው ይህ ሁኔታ ነው።

3. *አምሳያ "ጥላ" ነው።* እንደ መገናኛው ድንኳን ሁሉ እውን የነበረ ነገር ሊሆን ቢችልም፥ ፍጻሜውን ከሚያመለክተው መንፈሳዊ እውነት ጋር ሲተያይ ገና ጥላ ብቻ ነበር። ለምሳሌ፥ በአንድ የዛፍ ፎቶግራፍ እውነተኛው ዛፍ ባይኖርም፥ ፎቶው፥ ወረቀቱና ንጥረ ነገሮቹ ያሉ ቁሶች ናቸው። ፎቶግራፉም የእውነተኛው ዛፍ አምሳያ ነው። በዚሁ አኳኋን የመገናኛው ድንኳን በእውን ኖሯል፤ ቁሳዊ እውነታነትና ትርጉምም ነበረው። ከዚያ ባሻገር ክርስቶስ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ መንገድ የመሆኑን የፍጻሜ እውነትም የማመልከት ትርጉም ነበረው። አምሳያ ብዙ ጊዜ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ተምሳሌቶች ስለሚኖሩት ትርጓሜያቸውን በዚያው በአምሳያው ውስጥ እንመለከታለን። ለምሳሌ፥ ሊቀ ካህን የክርስቶስ አምሳያ ነበር። የሊቀ ካህኑ የበፍታ ልብስ የምን ተምሳሌት ነው (ዘጸ. 28፡39፤ ዕብ. 4፡14)? አዲስ ኪዳን ስለ ምስል ሲናገር በተምሳሌት አይጠቀም ይሆናል።

የመጀመሪያው፥ ምናልባትም ዋናው ችግር በአዲስ ኪዳን ያልተገለጡትን አምሳያዎች መረዳቱ ነው። ይህን ነጥብ በተመለከተ በመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች መካከል ሁለት የተራራቁ አመለካከቶች አሉ። አንዳንዶቹ በአምሳያነት መቀበል ያለብን አዲስ ኪዳን የሚያመለክታቸውን ነገሮች ብቻ ነው ይላሉ። ይህ አመለካከት አምሳያዎችን መሰየም ያለበት እግዚአብሔር ራሱ ነው በሚል እምነት ላይ የተመሠረተ ሲሆን፥ እኛ ሌሎች ነገሮችን አምሳያዎች ናቸው ካልን፥ የራሳችንን ግምት ብቻ መጠቀማችን እንጂ፥ መጽሐፍ ቅዱስን መተርጎማችን አይደለም የሚል ነው። ሌሎቹ ደግሞ በብሉይ ኪዳን በተግባር የነበረ ነገር ሁሉ ወደ አዲስ ኪዳን ያመለክታል፤ ስለሆነም በብዙ ዝርዝሮች ውስጥ አምሳያዊ ትርጉም ይገኛል ይላሉ። ልናገኘው ባንችልም ሌላው ትርጉሙ አለ።

ትርጉሙን ከቅዱስ ቃሉ ማግኘት እንጂ፥ የሌለን ነገር ወደ ቅዱስ ቃሉ ማስገባት የለብንም የሚለው አባባል ጤናማ የትርጓሜ መርህ ነው። በመሆኑም አዲስ ኪዳን የሚገልጣቸውን እና ሌሎች በብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን ውስጥ ያሉ ግልጥ የሆኑ ተመሳሳይ እውነቶች የሚታዩባቸውን አምሳያዎች መቀበሉ ብልህነት ይመስላል። እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ ከእርሱ በሚለዩት ሰዎች ላይ ተቃራኒ ወይም ቀኖናዊነት አቋም እንዳይኖረው እንደዚህ ስላለው ተመሳሳይነት የራሱን በጸሎት የታገዘ ውሳኔ መጠቀም አለበት።

ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ስለርሱ የተጻፈውን "ሁሉ" ለሁለት ደቀ መዛሙርቱ ነገራቸው (ሉቃስ 24፡27)። በዚያን እሁድ ከሰዓት በኋላ የእግር ጉዞ ወቅት በብሉይ ኪዳን ያለውን ምንባብ ሁሉ (ስለ እያንዳንዱ ሁነትና ስለ እያንዳንዱ ሰው) ተናግሮ ሊጨርስ አይችልም

ነበር። የዚህ ጥቅስ ትርጉም በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያለ ነገር ሁሉ፥ በቀጥታ አምሳያዊ መሆኑን እንደሚያስረዳ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም። ቢሆንም ብሉይ ኪዳን ስለ ክርስቶስ የሚለው እጅግ ብዙ ነገር እንዳለው ያመለክታል።

## የአዲስ ኪዳን ትርጓሜ

ተመሳሳይ ነገሮችን በምንመለከትበት ጊዜ ይረዳን ዘንድ በቅድሚያ አዲስ ኪዳን አንዳንድ አምሳያዎችን እንዴት እንደሚፈታቸው መረዳቱ ጠቃሚ ነው።

1. *በምድረበዳ የነሐስ እባብ መስቀል (ዮሐ. 3፡14-15)።* በመጀመሪያ በዘኍልቁ 21 ላይ የተመዘገቡትን እውነቶች እንዘርዝርና፥ ከዚያ በኋላ ከአዲስ ኪዳን እውነት ጋር ተመሳሳይ ናቸው የተባሉትን እናስተውላለን።

| *ዘኍልቁ 21፡4-9* | ዮሐንስ 3፡ 14-15 |
|---|---|
| -ሰዎች አጕረመረሙ | አልተጠቀሰም |
| -እግዚአብሔር ተናዳፊ እባቦችን ሰደደ፥ ብዙ ሰዎችም ሞቱ | አልተጠቀሰም |
| -ሕዝቡ በድለናል ብለው ተናዘዙ | አልተጠቀሰም |
| -ሙሴ ጸለየላቸው | አልተጠቀሰም |
| -የናስ እባብ እንዲሠራ እግዚአብሔር ሙሴን አዘዘው | አልተጠቀሰም |
| -ሙሴ የናስ እባብ ሠርቶ በዓላማ (በእንጨት) ላይ ሰቀለ | ክርስቶስ ተሰቀለ |
| -እባቦችን ያዩ ሁሉ ዳኑ | የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት አለው። |

አዲስ ኪዳን አብዛኞቹን የብሉይ ኪዳን ዝርዝር ሁነቶች እንደሚተዋቸው ያስተውሉ። ይህ በአዲስ ኪዳን ያልተጠቀሱ ሁሉ አምሳላዊ ትርጉም ሊኖራቸው አይችልም ማለት ሳይሆን፥ በቃሉ ውስጥ የተሰጠው ትርጓሜ አይመለከታቸውም ማለት ነው። በአዲስ ኪዳን የተጠቀሰው የአምሳያ ገለጣ የተመለከተው አቢይ እውነት፡- እባቡ ተሰቀለ፤

ሰዎች እርሱን አዩና ዳኑ የሚል ነው። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች "ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ" የሚሉት ቃላት በሌሎች ዝርዝሮች ውስጥ ትርጉም የማግኘት ሥልጣን የሚሰጧቸው ይመስላቸዋል። ምናልባት እንዲያ ይሆን ይሆናል። ሆኖም ቃሉ ራሱ ይህን ትርጉም እንደማይነግረን ልንዘነጋ አይገባም።

2. *ፋሲካ።* እንደገና የአምሳያን ገጽታና አዲስ ኪዳን የሚሰጠውን ትርጓሜ በዝርዝር እንመልከት።

| *ዘጸአት 12፥3-13* | *1ኛ ቆሮንቶስ 5፥7-8* |
|---|---|
| -አንድ ጠቦት በየቤቱ ተሰውቷል | ክርስቶስ ተሰውቷል |
| -ከበጎች ወይም ከፍየሎች መካከል አንድ ጠቦት በአሥረኛው ቀን ተወስዶ እስከ አሥራ አራተኛው ቀን ድረስ ይጠበቃል | አልተጠቀሰም |
| -ጠቦት በምሽት ታረደ | አልተጠቀሰም |
| -ደም በበሩ መቃንና በጉበን ላይ ተረጨ | አልተጠቀሰም |
| -ሥጋው ተጠብሶ ተበላ | አልተጠቀሰም |
| -ሥጋው ካልቦካ ቂጣና ከመራራ ቅጠል ጋር ተበላ | ክርስቲያኖች እርሾ የሌለውን የቅንነትና የእውነት ቂጣ ሊበሉ ነው |
| -ሥጋው በሙሉ ተበላ፤ የቀረው በእሳት ተቃጠለ | አልተጠቀሰም |
| -ወገባቸውን እንደታጠቁ ጫማዎች ሳይወልቁ፥ በትር በእጅ እንዳለ ምግቡ ተበላ | አልተጠቀሰም |
| -እግዚአብሔር በበሩ ላይ የነበረውን ደም አይቶ አለፈ | አልተጠቀሰም |

መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ የሚሰጠውን ትርጓሜ ያስተውሉ። አንዳንድ ግልጥና ተመሳሳይ ነገሮች አልተጠቀሱም፦ ለምሳሌ መሥዋዕቱ ተባዕታይ መሆኑ፥ የታረደው ከመሸ መሆኑ፥ የተረጨውን የመሥዋዕት ደም ሲያይ

እግዚአብሔር ማለፉ። አንዳንድ ሰዎች ከሌሎች ነገሮችም ተመሳሳዮችን ያወጣሉ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ግን የትም አይጠቅሳቸውም።

## ሊሆኑ የሚችሉ፥ ነገር ግን ተለይተው ያልታወቁ አምሳያዎች

ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች በአምሳያነት የሚመለከቷቸውንና ነገር ግን አዲስ ኪዳን የማይጠቅሳቸውን አንዳንድ ሁኔታዎች መመልከቱ ጠቃሚ ነው። እጅግ ጠቃሚ ከሆኑት ድርጊቶች አንዱ በዘፍጥረት 22 ተመዝግቦ የሚገኘውና አብርሃም ልጁን ይስሐቅን በሞሪያ ተራራ ላይ ለመሥዋዕት ያቀረበበት ሁኔታ ነው። እውነቶቹ የታወቁ ናቸው። አብርሃም ወደ ተራራው ሄዶ ልጁን እንዲሰዋ እግዚአብሔር አዘዘው። አብርሃምም ታዘዘ፤ በተራራው ላይ መሠዊያ አሰናድቶ ይስሐቅን ሊሠዋ ተዘጋጀ። ያኔ እግዚአብሔር አብርሃም መታዘዙን በድርጊቱ የገለጠ መሆኑን ነግሮት ልጁን እንዳይሠዋ ከለከለው። አብርሃም ከልጁ ጋር ወደ ቤቱ ከመመለሱ በፊት በይስሐቅ ምትክ የሚታረደውን በግ እግዚአብሔር አዘጋጀ። የታሪኩ ዋና ነጥብ ለአብርሃም የቀረበለት ፈተናና የሱ ታዛዥነት ነው።

አዲስ ኪዳን በዚህ ጉዳይ ሁለት ጊዜ አስተያየት ይሰጣል። በዕብራውያን 11፡17-19፥ አብርሃም እንደተፈተነና በእምነት ይስሐቅን እንደሰጠ እናነባለን። ይህን የተሰፋ ልጁን እግዚአብሔር ከሞት እንደሚያስነሣለትም አመነ። በዘይቤያዊ አነጋገር ይስሐቅን በትንሣኤ እንደገና አገኘው። አብርሃም ይስሐቅን በመስጠቱ በሥራው እንደጸደቀና በዚህም እምነቱ ፍጹም እንደሆነለት ያዕቆብ 2፡21-22 ይናገራል። ከነዚህ ምንባቦች በየትኛውም ቢሆን እግዚአብሔር ልጁን ክርስቶስን ለመስቀል ሞት መስጠቱን የሚያመለክት አሳብ የለም። መልእክቱ አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን ግንኙነት ነው የሚመለከተው፡- መፈተኑን፥ እምነቱንና መታዘዙን። በመሰዊያው ላይ የተሰጠ ምትክ መሥዋዕት ቢኖርም፥ ምትክነቱ ለአብርሃም ልጅ ነው እንጂ፥ ልጁ ለሌላ ምትክ የሆነበት ክንውን አልነበረም። ይህ ክርስቶስ ለኃጢአተኞች ምትክ የሆነበት የአምሳያ ፍጻሜ ተገላቢጦሽ ነው።

ስለሆነም፥ ይህ ሁኔታ የክርስቶስ ሞት አምሳያ እንደሆነ የምናምን ከሆነ፥ አምሳያዊ ትርጉሙ ሊሆን የሚችል እንጂ የተረጋገጠ እውነት አለመሆኑን መገንዘብ አለብን። ትኩረታችንን ማሳረፍ ያለብን፥ ቅዱስ ቃሉ በትክክል በሚያጎላው ነገር ላይ ነው። የዘፍጥረት መጽሐፍም ሆነ አዲስ ኪዳን የሚያተኩሩት በአብርሃም መፈተንና መታዘዝ ላይ ነው። የይስሐቅን

መሥዋዕትነት፥ የክርስቶስ ሞት አምሳያ ማድረግ የቃሉን ትኩረት ማዛነፍ ይሆናል። አብርሃም ልጁን በማቅረብ ስለሰጠው መሥዋዕት ልንናገር ብንችልም፥ መፈተኑና መታዘዙ ከአምሳያው ፍጻሜ ጋር የሚስማማ አይሆንም። እግዚአብሔር አብ ከሁሉ የላቀ ስለሆነ፥ በማንም የሚፈተን ወይም የሚታዘዝ አይደለምና።

ሌላውና በሚገባ የታወቀው የዮሴፍ ታሪክ ነው። ዮሴፍ ከልጅነቱ ጀምሮ የግብጽ መሪ እስከሆነበት ጊዜ ድረስ ያለፈባቸው የሕይወት ልምምዶች ከክርስቶስ ሕይወት ጋር የሚነጻጸሩና የሚያስደንቁ ሁኔታዎች አሏቸው። ከዘፍጥረት 37-50 ያለውን አጥንተንና ዝርዝር ጉዳዮቹንም መዝግበን፥ ብዙዎቹ ተነጻጻሪ ወይም ትይዩ ጉዳዮች በአጋጣሚ የተከሰቱ መሆን አለመሆናቸውን ልናጤን እንችላለን። አጋጣሚዎች ካልሆኑ ዮሴፍን በእርግጠኛነት እንደ ክርስቶስ አምሳያ ልንቆጥረው እንችላለን።

በገላትያ 4፡21-31 አንድ የብሉይ ኪዳን ታሪክ መንፈሳዊ ወይም አምሳያዊ ትርጉም ተሰጥቶታል። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ይህን ታሪክ አምሳያ ሳይሆን፥ ሰም ለበስ ነው ይሉታል። ነገር ግን ከአጋርና ከእስማኤል፥ ከሣራና ከይስሐቅ ታሪክ የተወሰኑ ነጥቦች ተወስደው በተመሳሳይነት ተመልክተዋል። ስለዚህ አምሳያዎች አንድ ፍሬ ነገር ብቻ ሊኖራቸው አያስፈልግም ብለን እንደመድማለን። ይሁን እንጂ አዲስ ኪዳን አምሳያዎችን ብዙ ጊዜ የሚፈታቸው በዚህ አኳኋን ነው።

## የትርጓሜ መመሪያ ነጥቦች

አምሳያዎችን ለማጥናት የሚረዱ አንዳንድ የመርህ ነጥቦችን ቀጥሎ አቀርባለሁ፦

1. *ከአንዳንድ ራእዮች በቀር አምሳያዎች በታሪክ በእርግጥ የነበሩ ነገሮች ሲሆኑ፥ የአምሳያዎቹ ፍጻሜዎችም ደግሞ ብዙውን ጊዜ ታሪካዊ መሠረት አላቸው።* በእስራኤል ታሪክ የተጠቀሰው ፋሲካ፥ ታሪካዊ ወደሆነው (መንፈሳዊ ጠቀሜታ ወዳለው) ወደ ክርስቶስ ሞት አመልክቷል።

2. *አምሳያዎች መንፈሳዊ እውነቶችን የሚያመለክቱ አካላዊ ምስሎች ናቸው።* በዮሐንስ 3፡14 ባለው ምሳሌ እባቡን በአካል ማየት ክርስቶስን በእምነት የማየት አምሳያ ነው።

3. *ፍጻሜው ከአምሳያው ይልቃል።* ዮሐንስ 1፡29ን ይመልከቱ። የእግዚአብሔር በግ ከሌላ እንስሳ ምንኛ የላቀ ነው!

4. *በአንዳንድ ሁኔታዎች መለስተኛ ዝርዝሮች ቢኖሩም በንጽጽሩ ውስጥ ማዕከላዊ ጉዳይ አለ።* ይህን ጉዳይ ዮሐንስ 3፡14-15ን እና 1ኛ ቆሮንቶስ 5፡7-8ን ባብራራንበት ጊዜ አይተነዋል።

5. *መንፈሳዊ ክንውን ከአምሳያ ትርጉም የሚያድግ ወይም የሚወጣ ነው።* እርግጠኛ ተመሳሳይነት እንጂ የ'ይሆናል' ወይም የፈጠራ ግንኙነት ሊኖር አይገባም። ትርጓሜ ሰጪዎች ሁሉ ይህን መርህ በሚተላለፉበት ጊዜ የሚገጥሟቸውን ሁኔታዎች የሚከተሉት ሁለት ጥቅሶች ያሳያሉ።

አንድ ሰው ስለ ፋሲካው ጠቦት ሲጽፍ፥ "ጠቦቱ በአሥረኛው ቀን ተወስዶ እስከ አሥራ አራተኛው ቀን መጠበቁ የሚያሳየን ክርስቶስ ከዘመናት አስቀድሞ በእግዚአብሔር የተወሰነ ቢሆንም በጊዜው የተገለጠልን መሆኑን ነው" ብሏል። ለዚህ ምን ማረጋገጫ አለ?

ሌላው ሰው ደግሞ ከንጹሕ እንስሳት አንዳንዶቹን በአምሳያነት ይወስዳል (ዘሌዋ. 11፡4-6)፦ "ማመስኳት እውነተኛ የክርስቲያኖች መለያ፥ ምናልባትም የመልካም ንግግር መግለጫ ስልት ነው። እውነተኛ ክርስቲያን እውነቱን ይናገራል (ምንዣጊውን በማመስኳቱ)፤ በትክክል ይመላለሳል (የሰኮናው መሰንጠቅ ምሳሌ ነው)።" እንደገናም "ማመስኳት ቅዱስ ቃሉን ማሰላሰልን፤ ስለ እግዚአብሔርና እርሱን የሚያስደስቱትን ነገሮች መናገርን ያመለክታል። በመዝሙረ ዳዊት 1፡2 እንደተገለጠው በእግዚአብሔር ፊት መንፈሳዊነትን (ምስጉን መሆንን)...ወዘተ. ያመለክታል። ከጌታ ጋር ከተመላለስንና ስለ እግዚአብሔር ከተናገርን "ንጹሕ" እና በእግዚአብሔርም ፊት ተቀባይነት ያለን ክርስቲያኖች ነን" ብሏል። ዘሌዋውያን 11፡7 ላይ እርያ ሰኮናው የተሰነጠቀ ቢሆንም የማያመሰኳ መሆኑ ተገልጧል። ታዲያ እርያ አንደበቱ ትክክል ባይሆንም "ንጹሕ" አረማመድ አለው ማለት ነው? በዘፈቀደ ወይም በይሆናል ከድምዳሜ ላይ እንዳንደርስ መጠንቀቅ አለብን።

6. *አምሳያዎችን እንደ ቀለሞች፥ ቁጥሮች፥ ቁሳቁሶች፥ ቅርጽ ወዘተ. ባሉ ነገሮች ላይ አይመሥርቱ።* ግልጥ አምሳያ ካለና ከርሱም ጋር የሚጣጣም እንደ ቁጥር ያለ ዝርዝር ከተገኘ፥ መልካም ነው። ነገር ግን አምሳያው ከቁጥር በላቀ መሠረታዊ ነገር ላይ ይመሥረት።

7. *አዲስ ኪዳን በግልጥ በማይናገርበት ጊዜ የራስዎን ቀኖናዊነት አያክሉበት።*

አምሳያ ሊሆኑ ወይም ላይሆኑ የሚችሉ አንዳንድ ምንባቦች እነሆ። በጸሎት ያጥኗቸው። ዘፍጥረት 2፡2-3፦ የእግዚአብሔር ዕረፍት፥ ክርስቲያን በክርስቶስ ያለው መንፈሳዊ ዕረፍት አምሳያ ነው?

ዘፍጥረት 7፡1-5፦ መርከቡ፥ በክርስቶስ የሚገኘው ደኅንነት አምሳያ ነው?

ዘጸአት 30፡17-21፡- የመታጠቢያው ሰን፥ ከኃጢአት የመንጻት አምሳያ ይሆናል?

ዘሌዋውያን 4፡- ስለ ኃጢአት የሚቀርበው መሥዋዕት፥ የክርስቶስ ማስተሰረያነት አምሳያ ነው?

ዘዳግም 18፡15፡- ሙሴ፥ እንደ ነቢይ የክርስቶስ አምሳያ ሊሆን ይችላል?

ዕብራውያን 9፡24፡- የመገናኛው ድንኳን፥ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ መንገድ የሆነው የክርስቶስ አምሳያ ይሆናል?

## አምሳያዎችና ተምሳሌቶች

አምሳያዎችና ተምሳሌቶች ከመመሳሰላቸው የተነሣ ስለሚያደናግሩ፥ ይህን ምዕራፍ ከማጠናቀቃችን በፊት በመካከላቸው ስላለው ልዩነት የመጨረሻ ማጠቃለያ መጨመሩ ይጠቅማል።

1. አምሳያ እውን የሆነ (ታሪካዊ) ሲሆን፥ ተምሳሌት ግን እንዲያ ላይሆን ይችላል።

2. አምሳያ በብሉይ ኪዳን ሆኖ፥ ፍጻሜው በአዲስ ኪዳን ነው። ተምሳሌት ግን ምንም የጊዜ ማገናዘቢያ የለውም።

3. አምሳያ አንድ የተወሰነ ነገር ወይም ሁነት ሲሆን፥ ተምሳሌት አጠቃላይ ጉዳይ ሊሆን ይችላል።

4. አምሳያ ብዙ ጊዜም ባይሆን፥ አንዳንድ ዝርዝሮች ሊኖሩት ይችላል። ተምሳሌት ግን አንድ ነጥብ ወይም ጉዳይ ነው ያለው።

5. አምሳያ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ተምሳሌቶችን ሊያጠቃልል ይችላል።

# 16

# ምሳሌዎችና ምሳሌያዊ ገለጣዎች

ምሳሌ [Parable] ብዙ ጊዜ ሥነ-ምግባራዊ ወይም መንፈሳዊ እውነትን ለመግለጥ የሚነገር ታሪክ ነው ይባላል። ይህ በሕይወት ውስጥ ሊደርስ የሚችል እውነት ቢሆንም፥ ብዙ ጊዜ ግን በእርግጥ የተፈጸመ ነገር አይደለም። አንድ ሰው ምሳሌን “ሰማያዊ ትርጉም ያለው ምድራዊ ታሪክ” ብሎታል። የተስፋፋ የንጽጽር ዘይቤ ልንለውም እንችላለን። ኢየሱስ ብዙ ጊዜ በወንጌሎች ውስጥ ምሳሌዎቹን “መንግሥተ ሰማይ. . . ትመስላለች” በማለት ይጀምራል። (ለምሳሌ፡- ማቴ. 22፡1ን ይመልከቱ።) ሆኖም ሁሉም ምሳሌዎች ተመሳሳይ መነሻ ወይም አጀማመር የላቸውም። በማቴዎስ 21፡33 “ሌላ ምሳሌ ስሙ። የወይን አትክልት የተከለ ባለቤት ነበረ. . .” እንደሚለው ያለም አለ።

በብሉይ ኪዳን አንዳንድ ምሳሌዎች ቢኖሩም፥ በብዛት የሚገኙት በአዲስ ኪዳን የመጀመሪያዎቹ ሦስት ወንጌላት ውስጥ ነው። ዮሐንስ በምዕራፍ 10 እና 15 ላይ የተወሰኑ ምሳሌያዊ ገለጣዎች [Allegory/አሊጎሪ] ቢሰጥም፥ ወንጌሉ ምንም ምሳሌዎች የሉትም።

ምሳሌዎች ሦስት ክፍሎች አሏቸው፡- እነሱም መቼት (መቼ የት) ወይም መነሻ፥ ታሪኩና ተዛምዶው ናቸው። ከክርስቶስ ምሳሌዎች አንዳንዶቹ መቼት የላቸውም፤ ወይም በቀጥታ አልተጠቀሰም። በሌሎቹ ደግሞ ተዛምዶው አልተብራራም። በአንዳንዶቹ ታሪኩ ብቻ ነው ያለው። ክርስቶስ ለአንድ የሕግ አዋቂ ጥያቄ፥ የመልካሙን ሳምራዊ በጎ ተግባር ጠቅሶ መልስ በመስጠት መልእክቱን አዛምዷል (ሉቃስ 10፡25-37)። በማቴዎስ 21፡33-41 ባለው ታሪክ ውስጥ በተነሣው የሥልጣን ወይም የባለቤትነት ውዝግብ መቼት ሲሆን፥ የፍርዱ ማስጠንቀቂያ ክንውን ነው። በማቴዎስ 13፡3-9 እና በሉቃስ 13፡18-19 ውስጥ አንድ ወይም ሁለት ፍሬ ነገሮች ጎድለዋል፡- በመጀመሪያው መቼቱ ወይም መነሻው፥ በሁለተኛው ደግሞ ሁለቱም ማለት መነሻውና ተዛምዶው። መነሻና ተዛምዶው በአንድ ታሪክ ውስጥ ሲኖሩ፥ የምሳሌው ትርጓሜ ቀላል ይሆናል። በምሳሌው ውስጥ አንዱ፥ ወይም ሁለቱም በማይኖሩበት ጊዜ ችግር ይገጥመናል።

መቼት ወይም መነሻ የትርጓሜን ቁልፍ ያስጨብጠናል። ለምሳሌ፥ ሉቃስ 15 ውስጥ ኢየሱስ ሦስቱን ምሳሌዎች ለመናገር የተገፋፋው በጸሐፍትና ፈሪሳውያን ተቃውሞ መንሥኤ ነው። ሦስቱም ምሳሌዎች የሚያተኩሩት እግዚአብሔር ኃጢአተኞች ንስሐ ሲገቡ ደስ

በመሰኘቱ ላይ ሲሆን፥ ኢየሱስ ኃጢአተኞችን ሲቀበላቸው ምንም ተቃውሞ ሊኖር የማይገባ መሆኑን ያረጋግጣሉ።

በመሠረቱ ምሳሌዎች አንድ አቢይ ነጥብ አላቸው። በመሆኑም በተለያዩ ዝርዝሮች ውስጥ መንፈሳዊ ትምህርት ለማግኘት አንሞክርም፤ በዚያ ፋንታ፤ ማዕከላዊ መልእክቱን እንፈልጋለን። ይህን የምናደርገውም ኢየሱስ ራሱ ምሳሌዎቹን ካዛመደባቸው መንገዶች ወይም ዘዴዎች የተነሣ ነው። በሉቃስ 15 ኢየሱስ ስለጠፋው ልጅ የተናገረውን ምሳሌ እንደሚከተለው ያዛምደዋል፦ "ንስሐ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ታላቅ ደስታ ይሆናል" (ቁ. 7)። ቁጥር 10 ደግሞ ለተከታዩ ምሳሌ ተመሳሳይ ትርጓሜ ይሰጣል። በታሪኩ ውስጥ ሰፋ ያለ ዝርዝር ገለጣ ቢኖርም፥ በመሠረቱ ለአባካኙ ልጅ ሁኔታው ያው ነው። እንዴት ነው ኢየሱስ የመልካሙን ሳምራዊ ምሳሌ የሚፈታው ወይም የሚተረጉመው? ሕግ አዋቂው ራሱ ትርጓሜውን እንዲሰጥ ያደርገዋል። መልካም ጎረቤት መሆኑን ያረጋገጠው ሳምራዊው ነው። ኢየሱስም ሕግ አዋቂውን "ሂድ አንተም እንዲሁ አድርግ" ይለዋል። ስለ ወንበዴዎቹ፥ ስለ ሌሎቹ ሁለት ሰዎች፥ ስለ አህያው፥ ስለ ገንዘቡም ሆነ ስለ እንግዶች ማደሪያው ጠባቂ የተለየ ትርጓሜ ወይም ፍቺ አልሰጠም።

ኢየሱስ ሁልጊዜ በአንድ ምሳሌ አንድ ነጥብ አይደለም የሚያመለክተው። ለምሳሌ ስለ ዘሪው በተናገረው ምሳሌ ውስጥ፤ ስለ እንክርዳዱና ስለ ስንዴው አያሌ ዝርዝሮችን ይገልጣል (ማቴ. 13)። የወይኑ ስፍራ ሠራተኞች ጉዳይም የዚሁ ተመሳሳይ ነው (ማቴ. 20)። እነዚህ የተለዩ የሆኑበትን ምክንያት ማጥናት ጠቃሚ ቢሆንም፥ አንድ ምሳሌ አንድ አቢይ ትምህርት አለው የሚለው መመሪያ ከነዚህ ጥቂት ምሳሌዎች በስተቀር ለሌሎች ምሳሌዎች ሁሉ አጠቃላይ መመሪያ ነው።

በመጀመሪያዎቹ የክርስትና ዓመታት ለእግዚአብሔር ቃል ምንባቦች ትርጓሜ የሰጡ ወይም የፈቱ አንዳንድ የሥነ-መለኮት ጠቢባን በምሳሌዎቹ ዝርዝሮች ውስጥ አስደናቂ ፍቺ አግኝተዋል። አርጌንስ [Origen/ኦሪጅን] የተባለውና ከነዚሁ የሥነ-መለኮት ጠቢባን አንዱ የሆነው ሰው፥ ስለ መልካሙ ሳምራዊ የሚከተለውን ትርጓሜ ሰጥቷል፦ በወንበዴዎቹ እጅ የወደቀው ሰውዬ አዳም ነው። ኢየሩሳሌም መንግሥተ ሰማይን፥ ኢያሪኮ ደግሞ ዓለምን ይወክላሉ። ወንበዴዎቹ ዲያብሎስና ጭፍራዎቹ፥ ካህኑ ሕግን፥ ሌዋዊው ደግሞ ነቢያትን ይወክላሉ። ክርስቶስ መልካሙ ሳምራዊ መሆኑ እርግጥ ነው። አህያው አካሉ ሲሆን፥ የእንግዶቹ ማደሪያ ቤተ ክርስቲያን ናት። አብና ወልድ ሁለቱ ዲናሮች ናቸው።

የክርስቶስ ዳግም ምጽዓት የሳምራዊው ተመልሶ የመምጣት ቃል ተስፋ ነው። ይህ ትርጓሜ ቢያንስ ከአንዳንድ ሁኔታዎች ጋር ይስማማል፤ ይሁንና በምንባቡ ውስጥ ትርጓሜውን የሚደግፍ ምንም ፍንጭ የለም። ኢየሱስም የሚሰጠው ትርጓሜ ግን የተለየ ነው። የኦርጌንስ ትርጓሜ ምንም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለውም። ስለሆነም እርሱን ወይም ትምህርቱን ከመከተል ልንጠነቀቅ ይገባል።

ምናልባት ኢየሱስ አንዳንዶቹን ምሳሌዎች ደጋግሞ ተናግሯቸው ይሆናል። የጠፋው በግ በሁለት የተለያዩ መነሻዎች ተጠቅሷል። ማቴዎስ 18 ውስጥ እግዚአብሔር ለሕጻናት እንደሚጠነቀቅ ሲገልጥ፥ በሉቃስ 15 ግን ስለ ኃጢአተኞች የሚያስብ መሆኑን ነው የሚያመለክተው። ያም ሆነ ይህ በሁለቱም ውስጥ ጎልቶ የታየው ፍቅር የተሞላበት የእግዚአብሔር ጥበቃ ነው።

## የትርጓሜ መመሪያ ነጥቦች

1. *በቅድሚያ የታሪኩን ቀጥተኛ ትርጉም ያስቡ።* መንፈሳዊው ትምህርት በዚያ ላይ መመሥረት አለበት።

2. *ምክንያቱ ተገልጦ እንደሆን፥ ምሳሌው የተሰጠበትን ምክንያት ያስተውሉ።* ለምሳሌ ኢየሱስ በፈሪሳዊው ቤት ለተናገረው አጭር ምሳሌ መነሻ የሆነውን ምክንያት ይመርምሩ (ሉቃስ 7፡41-43)። መነሻው ግልጥ ባይሆን አይጨነቁ፤ ትርጓሜውን ከሌሎች ነገሮች ያገኙታል። ይሁንና የታሪኩ መቼት ወይም መነሻ ግልጥ መሆኑ ጠቃሚ ነው፤ የምሳሌውን መልእክት ከዚህ ጋር በማዛመድ መመልከት አለብዎት።

3. *ዋናውን ትምህርት፥ ማለት ማዕከላዊ ነጥቡን ያግኙ።* ይህ ኢየሱስ ከሚሰጠው የሕይወት ተዛምዶ ወይም ከራሱ ታሪክ ይገኛል። ኢየሱስ የአሥሩን ቆነጃጂት ታሪክ ከተናገረ በኋላ ትርጓሜውን "የመምጫዬን ዕለት ወይም ሰዓት አታውቁምና ነቅታችሁ ተጠባበቁ" በማለት አብራርቷል። የተዘጋጁት ሁሉ ከእርሱ ጋር እንደሚሄዱ ወይም እንደሚነጠቁ ከታሪኩ ለመረዳት እንችላለን።

4. *ትርጉሙን ከቅዱስ ቃሉ ቀጥተኛ ትምህርት ጋር ያገናዝቡት።* ምሳሌዎች ፈሊጣዊ አነጋገሮች ስለሆኑ የትምህርተ-ሃይማኖት መሠረት አናደርጋቸውም። ቢሆንም በቅዱስ ቃሉ የተሰጠ እውነትን የሚያጠናክሩና የሚያረጋግጡ ናቸው። ለምሳሌ፡- የአባካኙን ልጅ ምሳሌ ኃጢአተኛ ወደ እግዚአብሔር የሚመለስበትን ሁኔታ ለማስተማሪያነት የተጠቀምንበት እንደሆን፥ ንስሐ ብቻውን በቂ ስለሆነ፥ የክርስቶስ ማስተሰረያነት አያስፈልግም የሚል መልእክት ይኖረው ይሆናል።

5. ታሪኩን ለመረዳት የሚያዳግቱ ማናቸውም ዓይነት ችግሮች ከገጠሙዎ፥ ችግሩን ለመፍታት የሚረዱ አሳቦችን ከታሪካዊና ከባህላዊ ሁኔታዎች ይፈልጉ። ለምሳሌ በአይሁድ ባህል አንድ ሠርግ ደጋሽ ለእድምተኞቹ የሠርግ ልብስ መስጠት የነበረበት መሆኑን ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ያውቃሉ። ያለ ሠርግ ልብስ የተገኘው ሰው ከሩኛ የተቀጣው ለዚህ መሆኑን ታሪኩ ይገልጣል (ማቴ. 22፡11-13)። ሰውዬው ተሰጥቶት የነበረውን ልብስ አልወሰደም ብለን ለመደምደም እንችላለን።

## የወይኑ አትክልት ሠራተኞች

እነዚህን የመመሪያ ነጥቦች ከምሳሌዎቹ አንዱ በሆነው የወይኑ አትክልት ሠራተኞች እንጠቀምባቸው (ማቴ. 20፡1-16)።

መጀመሪያ ከበቂ የአገባብ መረዳት ጋር ጽሑፉን የማንበብና የማስተዋል መሠረታዊ መመሪያን ይከተሉ። ቁጥር 1 የሚጨርሰው "ትመስላለችና" በማለት ስለሆነ ምሳሌውን ከምዕራፍ 19 ጋር እንደሚያገናኘው እንረዳለን። ምዕራፉ በትክክል እንዳልተከፋፈለ እንገነዘባለን። የምዕራፍ 19ን የመጨረሻ ቁጥር ተመልክተው ከምዕራፍ 20 ቁጥር 16 ጋር ያዛምዱት። በነዚህ ጥቅሶች ጠቃሚዎቹ ቃላት ምንድናቸው? እነዚያን ቃላት በምሳሌያዊው ታሪክ ውስጥ ያገኟቸዋል (ቁ. 8፥ 10፥ 12፥ 14ን ይመልከቱ)። በምዕራፍ 20፡1 ላይ "ትመስላለችና" በሚለው ቃልና በምዕራፍ 20፡16 ላይ "እንግዲህ" በሚለው ቃል የተመለከቱትን ግንኙነቶች ሊገነዘቡ ይችላሉ?

በመቀጠልም ታሪኩ እነዚህን ሁለት ጥቅሶች እንዴት ግልጥ እንደሚያደርጋቸው ይመልከቱ። በታሪኩ ውስጥ የመጨረሻው መጀመሪያ ወይም የመጀመሪያው መጨረሻ የሆነበት ሁኔታ አለ? የኋለኞቹ ሠራተኞች ቀድመው ነበር የመጡት? እርግጥ በቅድሚያ ተከፍሏቸዋል፤ ነገር ግን በሌላ አኳኋን የቀደሙበት ነገር አለ? ተነጻጻሪው የሰዓት ክፍያቸውስ እንዴት ነው?

የአትክልቱ ባለቤት ለምንድነው ለኋለኞቹ ሠራተኞች መልካም ማድረግ የነበረበት? የሁለቱን ቡድኖች የአገልግሎት ስምምነቶች ያነጻጽሩ (ቁ. 2 እና 7)። በሁለቱ ቡድኖች መካከል የተለየ መንፈስ ወይም ስሜት ያያሉ? ወደ ኋላ መለስ ብለው ምዕራፍ 19ን ይመልከቱ፤ ኢየሱስ ምሳሌውን እንዲናገር መነሻ የሆነው የጴጥሮስ አባባል መሆኑን እያስታወሱ ጴጥሮስ ያሳየውን ስሜት ወይም መንፈስ ይመልከቱ። ወጣቱ ሀብታም (19፡22፥ በ1980 ዓ.ም. እትም) ጴጥሮስ ያሳየውን ስሜት ወይም መንፈስ አሳየ? ምናልባት በ19፡22፥ 27፥ 29፤ 20፡9-10 ባሉት ክፍሎች

የተጠቀሱት፥ "ታገኛለህ" እና "ተቀበሉ" የሚሉት ቃላት መመሳሰልን ወይም ግንኙነትን ያመለክቱ ይሆናል። አሁንስ የምሳሌውን ማዕከላዊ ወይም ዋና ትምህርት ሊገልጡ ይችላሉ?

የምሳሌውን መቼት ወይም መነሻና በኢየሱስ የተሰጠውን ተዛምዶ በጥንቃቄ አስተውለናል። የተደጋገሙና አገናኝ ቃላትን በጥንቃቄ ለመመልከትም ጥረናል። ምሳሌው በራሱ አገባብ ጠንካራ መልእክት ይሰጣል፥ እንደ ጴጥሮስ ሊቀበሉ ስላላቸው ነገር በጣም ለሚጨነቁ ሁሉ ከባድ ማስጠንቀቂያ ነው። ኢየሱስ፦ "ተጠንቀቁ" ይላል፤ ምክንያቱም ፊተኞች በፍጻሜው ኋለኞች ሊሆኑ ስለሚችሉ።

በወንጌል የሚገኙና ለጥናት የሚሆኑ ሌሎች ምሳሌዎች እነሆ፦

ማርቆስ 4፡30-32 የሰናፍጭ ቅንጣት

ሉቃስ 7፡41-43 ሁለት ተበዳሪዎች

ሉቃስ 11፡5-8 በእኩለ ሌሊት የሚመጣ ወዳጅ

ሉቃስ 16፡19-31 ባለጠጋውና አልአዛር (ይህ ምሳሌ ነው?)

ሉቃስ 18፡1-8 ዓመፀኛው ዳኛ

## ምሳሌያዊ ገለጣዎች

ምሳሌያዊ ገለጣዎችና ምሳሌዎች በአንዳንድ ሁኔታዎች ተመሳሳይ ስለሆኑ በአንድ ላይ ብንመለከታቸው መልካም ነው። ምሳሌያዊ ገለጣ የተስፋፋ ተለዋጭ ዘይቤ ነው ይባላል። በዮሐንስ 10 ውስጥ ምሳሌያዊ ገለጣ በአብዛኛው ታሪክ ሲሆን፥ በ15 ውስጥ ደግሞ በአብዛኛው ሥዕል ነው።

ኢየሱስ በዮሐንስ 15 ውስጥ፥ "እውነተኛው የወይን ግንድ እኔ ነኝ፤ ገበሬውም አባቴ ነው። ...እናንተም ቅርንጫፎቼ ናችሁ" (ቁ. 1 እና 5) ይላል። ይህ የምሳሌያዊ ገለጣ መሠረታዊ አወቃቀር ነው። ከዚያም ኢየሱስ የዚህ ግንኙነት ክፍል ለሆኑ ሌላ ገጽታዎች መንፈሳዊ ትርጉም ይሰጣቸዋል፤ ቅርንጫፎች በወይኑ ግንድ ላይ ሊኖሩና ፍሬ ሊያፈሩ ይገባቸዋል፤ የወይኑ ባለቤትም ፍሬ የሚያፈሩትን ቅርንጫፎች እየገረዘ፥ የማያፈሩትን ግን ያስወግዳቸዋል፤ ፍሬው ለወይኑ ባለቤት ክብሬታን ያስገኝለታል።

መሠረታዊ ትርጓሜውን በዚሁ ምሳሌያዊ ገለጣ ውስጥ ልናገኝ እንችላለን። ከርሱ ውጪ መሄድ አያስፈልገንም። (በዚህም የተነሣ ምሳሌያዊ ገለጣ ብዙ ጊዜ ከሌሎች ዘይቤዎች ይልቅ ለትርጓሜ ይቀላል።) ይህ ማለት ግን በምሳሌያዊ ገለጣው ውስጥ ያለ ነገር ሁሉ ግልጥ ነው ማለት አይደለም። አንዳንድ ሁኔታዎች ትርጓሜ ሳይሰጣቸው ይቀሩና ትክክለኛ

ትርጉማቸውን ማግኘቱ ይቸግረናል። የማያፈሩ ቅርንጫፎች ይወገዱና ይቃጠላሉ። የዚህ መንፈሳዊ ትርጉሙ ምንድነው? ቁጥር 6 ይህን እንደ አስፈሪና አስደንጋጭ እውነት ቢገልጠውም፥ ትርጉሙን ግን በግልጥ አያሳየንም። ስለሆነም እኛ ነን ትርጉሙን መፈለግ ያለብን።

ዮሐንስ 10 የመልካም እረኛና የበጎቹን ምሳሌያዊ ገለጣ ያጠቃልላል። እስኪ የምሳሌዎቹን ምንነትና የተሰጧቸውን ትርጓሜዎች እንዘርዝር፡-

| | |
|---|---|
| እረኛ | ኢየሱስ |
| በጎች | ትርጉም አልተሰጠም |
| በረኛው | ትርጉም አልተሰጠም |
| በረት | ትርጉም አልተሰጠም |
| በር | ኢየሱስ |
| ወንበዴዎች | ከኢየሱስ "በፊት የመጡ" |
| ሌላው | ትርጉም አልተሰጠም |
| ተኩላ | ትርጉም አልተሰጠም |
| ሞያተኛ | ትርጉም አልተሰጠም |

ኢየሱስ የዚህን ምሳሌ ትርጓሜ ጥቂቱን ብቻ ሰጥቶ፥ ሌላውን እኛ እንድናገኘው መተዉ የሚገርም ነው። ራሱን እንደ እረኛና እንደ በር ከመግለጡ በቀር እምብዛም ያደረገው ነገር የለም። ከእርሱ በፊት የመጡት እነማን እንደሆኑ ልናውቅ ይገባል። ሌሎች ሁኔታዎችን ለመፍታት የሚረዱት በምንባቡ የቀረቡ አሳቦች አሉ። እርሱ በጎቹን ያውቃቸዋል፤ እነርሱም ድምፁን ይለያሉ የሚለው፥ አማኞችን (ደቀ መዛሙርቱን) ያመለክታል። በበሩ የማይገቡ ወንበዴዎች ኢየሱስን የማይቀበሉ ወይም የሚቃወሙ ሐሰተኛ የሃይማኖት መሪዎች መሆን አለባቸው። ሞያተኛውም ሐሰተኛ እረኛ ማለት የሃይማኖት መሪ ነው። ነገር ግን በረት፥ ተኩላና ሌላው ሰው ሳይገለጡ ቀርተዋል። ከዚህ የምንረዳው ወይም ለመደምደም የምንችለው፥ ከሁሉም ዝርዝር ውስጥ ትርጉም ማግኘት አስፈላጊ ያለመሆኑን ነው። በምሳሌያዊ ገለጣ ውስጥ አንዳንድ ዝርዝሮች ትርጉም ቢኖራቸውም፥ በምሳሌዎች እንዳለውና ዮሐንስ 10 ላይ እንደምናየው የኢየሱስ ትርጓሜ በተወሰኑ አበይት ነጥቦች ላይ አሁንም ትኩረት ተሰጥቶታል።

አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ምሳሌያዊ ገለጣዎች፥ መዝሙር 80፡8-15፤ ምሳሌ 5፡15-20፤ መክብብ 12፡3-7 ናቸው።

## የትርጓሜ መመሪያ ነጥቦች

1. *የምሳሌያዊ ገለጣውን ዝርዝር ወይም ገጽታዎች ያስተውሉ።* ዮሐንስ 10ን አስመልክቶ እንዳደረግነው ሁሉ ዝርዝራቸውን መመዝገቡ መልካም ነው።

2. *ከገጽታዎቹ ለማንኛውም ቢሆን የተሰጠውን ትርጓሜ ያስተውሉ፤ በዝርዝርም ይመዝግቧቸው።*

3. *ከሌሎች ምንባቦች ተመሳሳይ ትርጉም ሊገኝ መቻል አለመቻሉን እየቃኙ ሌሎች ሁኔታዎችንም ይመልከቱ።* ለምሳሌ እያንዳንዱ ተለዋጭ ዘይቤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሌላ ስፍራ አገልግሏል? አንድ ነገር በሌላ ስፍራ ተቃራኒ ትርጉም ባላቸው ተለዋጭ ዘይቤዎች ሊገባ እንደሚችል በማስታወስ ቀኖናዊ ትርጓሜ ከመስጠት ይቆጠቡ። እንዲህ ያሉት የምሳሌያዊ ገለጣ ገጽታ ትርጉሞች ሊሆኑ እንደሚችሉ በመገመት ይመልከቷቸው እንጂ እርግጠኞች አድርገው አይቁጠሯቸው።

4. *ገጽታዎችን ወይም የሚሆኑ ነገሮችን ሁሉ ለመለየት አይሞክሩ።* ክርስቶስ በዮሐንስ 10 እና 15 ላሉት ምሳሌያዊ ገለጣዎች እንደዚህ አላደረገም። አጠራጣሪዎቹን ሳይሆን፥ በሚገባ ግልጥ የሆኑትን ትርጓሜዎች ይመልከቱ። በግድ ወይም በ'ይሆናል' ግምት ትርጓሜዎችን አይስጡ።

# 17

# የዕብራይስጥ ቋንቋ ፈሊጦች

ፈሊጥ የአንድ ቋንቋ የተለየ አገላለጥ ነው። እያንዳንዱ ቋንቋ ነገሮችን የሚገልጥባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉት። ፈሊጦች የቋንቋውን ተናጋሪዎች የአስተሳሰብ ሁኔታ ይገልጣሉ።

ለምሳሌ በአማርኛ "እሳት ካየው፥ ምን ለየው" ሲባል፥ ፈሊጣዊ አነጋገሩ የሚገልጠው እሳት ሳያማርጥ ወይም ልዩነት ሳያደርግ ያገኘውን ሁሉ እንደሚያቃጥል እንጂ፥ የሚያይበት ተፈጥሯዊ ዓይን እንዳለው አይደለም። ስለዚህ በማንኛውም ወቅትና ሁኔታ በአንድ ቋንቋ የተገለጠን መልእክት በሌላ ቋንቋ ሲገለጥ በትክክል ለመረዳት እንዲቻል፥ ከተቀባዩ ቋንቋ ተናጋሪዎች ባህልና ልምምድ ጋር የሚስማማ ፈሊጥ መምረጥና መጠቀም ያስፈልጋል።

የዕብራይስጥ ቋንቋም የራሱ ፈሊጦች አሉት። አንዳንዶቹ ዘይቤያዊ አነጋገሮች ናቸው። ነገር ግን በዕብራውያን አስተሳሰብ ልዩ በመሆናቸው የተነጣ በዚህ ምዕራፍ እንመለከታቸዋለን። በአዲስና ብሉይ ኪዳናት ውስጥም ይገኛሉ። ምክንያቱም የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች በአብዛኛው ዕብራውያን ነበሩ።

ፈሊጦች በብዛት የሚገኙት በየቋንቋዎቹ የመጀመሪያ እትሞች ነው። ይህ የሆነው አዲሶቹ እትሞች መልእክቱን በአብዛኛው ግልጥ ለማድረግ ሲባል ለኛ በሚገባን ወይም በራሳችን ፈሊጦች በመተካታቸው ነው። ለምሳሌ፥ በሕዝቅኤል 44፡12 (በ1954 ዓ.ም. እትም) ሌዋውያን ባለመታዘዛቸው እግዚአብሔር፥ "እጄን በላያቸው አንሥቻለሁ" ይላል። እጅ የሚነሣው ከባድ መሀላ ለመቀበል (በፍርድ ቤት እንደሚደረግ) ነው። የ1980 ዓ.ም. እትም መጽሐፍ ቅዱስ ግን፥ "እኔ እግዚአብሔር በፍጹም እምላለሁ" በማለት ይተረጉመዋል። አዲሱ ፈሊጥ የመጀመሪያዎቹን ፅንሰ አሳቦች በትክክል የሚገልጣቸው ከሆነ ስሕተት አይደለም። ያን ለመጠበቅ ግን ትልቅ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

ለምሳሌ፥ አንድ የዩዱክ ክርስቲያን በራሱ ቋንቋ የተጻፈውን መጽሐፍ ቅዱስ እያነበበ በአማርኛ ይተረጉምልናል እንበል። ዮሐንስ 14፡1ን፥ "ጉበትህ ላይ ስባሪ አታስቀምጥ" ብሎ ቢተረጉምልን ማንኛችንም ብንሆን አንረዳውም። የቃል በቃል ትርጉሙ ትክክለኛውን አሳብ አይገልጥልንም። በመሆኑም ፈሊጦች በሚተረጐሙበት ጊዜ በውስጣቸው ያዘሉትን ትርጉም በሚገባ መግለጥ የሚያስፈልግበት ጊዜ ይኖራል።

ከነዚህ ፈሊጦች አንዳንዶቹ ቴክኒካዊ መጠሪያዎች አሏቸው። ስለነሱ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት መዝገበ ቃላትዎን ይመልከቱ።

1. *አካለ ሰብዕነት [Anthropomorphism/አንትሮፖሞርፊዝም]።* ይህ በቀጥታ ወይም ቃል በቃል ሲተረጎም "የሰው አካል ወይም ቅርጽ" ማለት ነው። ይህ ፈሊጥ እግዚአብሔር አካል የሌለው ቢሆንም እንዳለው አድርጎ የሚናገር ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ከማወቃችን የተነሣ፥ ከነዚህ ፈሊጦች ብዙዎቹን ተቀብለናቸዋል። ስለሆነም አካለ ሰብዕን መጠቀማችንን ልብ ሳንል በፈሊጦቹ ታግዘን፥ "ጌታ ሆይ፥ እጅህን በምወደው ወይም በማፈቅረው ላይ አድርግ" ብለን እንጸልይ ይሆናል። አካለ ሰብዕነት የተለየና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የታወቀ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። በሌሎች ብዙ ቋንቋዎችም ይገኛል። ነገር ግን በዕብራይስጥ ቋንቋ ካለው ጠቀሜታ የተነሣ የቋንቋው ፈሊጥ አድርገን እንቆጥረዋለን።

ብዙ ምንባቦች፥ በተለይም ብሉይ ኪዳን ውስጥ፥ እግዚአብሔር አካላዊ ክፍሎች ያሉት በማስመሰል ይናገራሉ። "ፊት"፡- ዘጸአት 33፡23፤ መዝ. 11፡11፤ ኤርምያስ 21፡10። "ዓይን"፡- 2ኛ ዜና 7፡16፤ መዝሙር 11፡4፤ ኤርምያስ 16፡17። "ጆሮ"፡- መዝሙር 10፡17፤ ኢሳይያስ 37፡17፤ ዳንኤል 9፡18። "አፍንጫ"፡- ዘጸአት 15፡8፤ መዝሙር 18፡15፤ ኢሳይያስ 65፡5። "አፍ"፡- 1ኛ ነገሥት 8፡24፤ ኢሳይያስ 34፡16፤ ሚክያስ 4፡4። "ድምጽ"፡- ኢዮብ 40፡9፤ ዳንኤል 9፡11፥ 14። "ክንድ"፡- ዘዳግም 11፡2፤ ኢሳይያስ 62፡8፤ ኤርምያስ 21፡5። "እጅ"፡- ዘጸአት 33፡23፤ ኢሳይያስ 50፡2፤ ኤርምያስ 1፡9። "ጀርባ"፡- ዘጸአት 33፡23፤ ኢሳይያስ 38፡17፤ ኤርምያስ 18፡17። "ነፍስና ልብ"፡- ዘፍጥረት 6፡6፤ 2ኛ ዜና 7፡16፤ መዝሙር 11፡5። "እግር"፡- ዘጸአት 24፡10፤ መዝሙር 77፡19፤ ኢሳይያስ 60፡13። ቅርጽ ወይም "የሚታይ አካል"፡- መዝሙር 17፡15። የዚህ ፈሊጣዊ ቃል ሌላ አጠቃቀሞች የአካልን ክፍል በትክክል ባይጠቅሱም እንደ "መቀመጥ" እና "መሄድ" ባሉ የአካላት ግብሮች አማካይነት ሁኔታውን ያመለክታሉ። (መዝ. 78፡65፤ 113፡5፤ ኢሳ. 26፡21፤ አሞጽ 7፡7ን ይመልከቱ።)

እግዚአብሔር በሕልውናው አካል የሌለው መሆኑን ማስታወስ አለብን። በዮሐንስ 4፡24 እግዚአብሔር መንፈስ መሆኑን እና፥ በሉቃስ 24፡39 መንፈስ ሥጋና አጥንት የሌለው መሆኑን እናነባለን። (የሥላሴ ሁለተኛ አካል የሆነው ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ ሥጋ ነስቶአል ወይም ለብሷል፤ አሁን አምላክና ሰው ነው።)

ከላይ የተጠቀሱት አገላለጦች ቀጥተኛ ፍቺ ካልሆኑ ታዲያ ትርጉማቸው ምንድነው? ቁልፉ ጥያቄ እነዚህን የአካል ክፍሎች ለምን ጉዳይ ነው የምንጠቀምባቸው? የሚል ነው። በቀኝ እጃችን ምን

እናደርግባቸዋለን? ጥንካሬ የሚሻ ሥራ እንሠራባቸዋለን። የሰው ቀኝ እጅ ብዙውን ጊዜ ከግራው ይልቅ ይጠነክራል። ስለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች፥ እግዚአብሔር መለኮታዊ ብርታቱን ለማሳየት ሲል ኃይሉን በቀኝ እጅ በመግለጥ የሚጠቀም መሆኑን ይናገራሉ። እግዚአብሔር ራሱም ይህን ይገልጠዋል። በዓይኖቻችን ምን እናደርግባቸዋለን? በነርሱ አማካይነት ስለ ሌሎች ሰዎችና ነገሮች እንረዳለን። የእግዚአብሔር "ዓይኖች" የሚለው ቃል እርሱ እኛንና ፍጥረታትን በሙሉ የሚመለከት መሆኑን ያስረዳል። በጆሮዎቻችን ምን እናደርግባቸዋለን? እናደምጥባቸዋለን። የእግዚአብሔር "ጆሮ ክፍት ነው" ማለት እኛ የምንለውን ለመስማት ዝግጁ ነው ማለት ይሆናል።

በ2ኛ ዜና 16፡9፥ "እግዚአብሔር ልቡ በእርሱ ዘንድ ፍጹም የሆነውን ያጸና ዘንድ ዓይኖቹ በምድር ሁሉ ይመለከታሉና" የሚለውን እናነባለን። ቃል በቃል ሲወሰድ አባባሉ ስሜት አይሰጥም። እግዚአብሔር በሁለት ትልልቅ ዓይኖቹ ዓለምን እንደማያይ እናውቃለን። እዚህ የተገለጠው እውነት እግዚአብሔር በዓለም ላይ በየትኛውም ስፍራ ካለ እውነተኛ አማኝ ጋር እንደሚሆንና፥ ማንኛውንም ነገር በርሱ ፋንታ በብርታቱ የሚያከናውንለት መሆኑን የሚያስረዳ ነው። ስለዚህ በአካለ ሰብዓዊነት ገለጣ መጠቀም የእግዚአብሔርን ኃይልና ፍጹምነት ስዕል በአእምሮ ይቀርፃል።

ከሰው ቅርጽ ጋር የሚዛመዱትን ምንባቦች፥ እግዚአብሔር የሰው ስሜት ያለው መሆኑን ከሚናገሩት ጋርም፥ ልናገናኛቸው እንችላለን። እግዚአብሔር አዝኗል (ዘፍጥ. 6፡6)፤ አስታውሷል (ዘፍጥ. 19፡29)፤ ተጸጽቷል (ኤር. 18፡8፥ 10)። እንደነዚህ ያሉት ጥቅሶች ከሰው ስሜት እጅግ የሚልቀውንና ስለ እግዚአብሔር ያለውን እውነት ይገልጣሉ። መጸጸቱ ግን ልዩ ጉዳይ ነው። 1ኛ ሳሙኤል 15፡29 እግዚአብሔር ሰው ባለመሆኑ መጸጸት የማይገባው መሆኑን ይነግረናል። እግዚአብሔር የማይለወጥ ስለሆነ በትክክል ሲታይ ሊጸጸት አይችልም። ነገር ግን እግዚአብሔር ሰውን የሚመለከተው በራሱ በሰው ዝንባሌ ወይም አመለካከት መሠረት ስለሆነ፥ ያ ዝንባሌ በተለወጠ ጊዜ እግዚአብሔር ሰውን የሚመለከትበት ሁኔታም ይለወጣል። ይህ ሲታይ ታዲያ ሰው እንደሚጸጸት ሁሉ እግዚአብሔርም የሚጸጸት ይመስል ይሆናል፤ በመሠረቱ ግን አይጸጸትም። (ኤር. 26፡12-13ን ይመልከቱ።)

2. *ፍጹማዊ ለአንጻራዊ።* በዚህ አገባብ "ፍጹማዊ" ማለት "ከሌሎች ነገሮች ጋር ግንኙነት የሌለው" ማለት ሲሆን፥ "አንጻራዊ" ማለት ደግሞ "ከሌሎች ጋር ግንኙነት ወይም ተወዳዳሪነት ያለው" ማለት

ነው። ለምሳሌ፥ "አበበ ቡና ይወዳል" ማለት ፍጹማዊ አባባል ነው። "አበበ ከሻይ ይልቅ ቡና ይወዳል" ማለት አንጻራዊ አባባል ነው። ምክንያቱም ሻይና ቡና በመወዳደር ወይም በመመዛዘን ላይ ናቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንዴ ፍጹም የሆነን ነገር በተለምዶ 'ሀ' ሳይሆን 'ለ' ነው በማለት ወደ አንጻራዊነት ይለውጣል። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን ዮሴፍ ወደ ግብጽ ለሸጡት ወንድሞቹ፥ "እናንተ ወደዚህ የላካችሁኝ አይደላችሁም፥ እግዚአብሔር ላከኝ እንጂ" (ዘፍጥ. 45፡8) ሲል የተናገረው ነው። ይህ ቀጥተኛ ወይም ቃል በቃል የተወሰደ አባባል ከሆነ እውነት አይደለም። ወንድሞቹ ወደ ግብጽ የሸጡት መሆኑን ዮሴፍ አምኗል (ቁ. 5)፤ ለክፋት እንዳደረጉት አድርጎም ተቀብሎታል (ዘፍጥ. 50፡20)። ስለዚህ አባባሉ ፈሊጣዊ ነው። "የእናንተ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርም ሥራ ነበር" ማለቱ ሲሆን፥ አጉልቶ ለማሳየት የፈለገው የእግዚአብሔርን ልዑል ዓላማ ነው።

እንዲህ ያለውን የአነጋገር ፈሊጥ በአንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ ልብ አድርጎ ማጤኑ በጣም ይጠቅማል። ኤርምያስ 7፡22-23 ላይ እግዚአብሔር፡- "ከግብፅ ምድር ባወጣኋችሁ ቀን ስለሚቃጠል መሥዋዕት ለአባቶቻችሁ አልተናገርሁምና፥ አላዘዝኋችሁምም። ነገር ግን ቃሌን ስሙ፥ ...በዚህ ነገር አዝዣችኋለሁ" ይላል። የዘጸአትና የዘሌዋውያን መጻሕፍት፥ እግዚአብሔር ዕብራውያንን ከግብጽ ምድር ባወጣቸው ጊዜ ስለ መሥዋዕቶች ተናግሯል ይላሉ። ለዘብተኛ የሥነ-መለኮት ሰዎች በዘጸአትና በዘሌዋውያን መጻሕፍት የሚገኙ ታሪኮች በኤርምያስ መጽሐፍ ከሚገኝ ጥቅስ አንጻር ሲታዩ ትክክለኞች አይደሉም ብለው ያምናሉ። የሚያቀርቡት ስለ እግዚአብሔር ጥንታዊና የተሳሳቱ አሳቦችን ነው በማለት ይከራከራሉ። የኤርምያስ አባባል ግን ፍጹማዊውን ነገር በአንጻራዊው የመተካት ጉዳይ ነበር። እግዚአብሔር ስለ መሥዋዕቶች የተናገረ ቢሆንም፥ የርሱ ጉዳይ ይበልጥ ከሰዎች ልብና መታዘዝ ጋር ነበር። ይህን ፈሊጣዊ ገለጣ በሌሎች ክፍሎች ለማየት ከፈለጉ፡- ዘጸአት 16፡8፤ ዘዳግም 5፡2-3፤ መዝሙር 51፡16-17፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 1፡17፤ 9፡9-10፤ ፊልጵስዩስ 2፡4፤ 1ኛ ዮሐንስ 3፡18ን ይመርምሩ።

የዚህ የተለየ ፈሊጣዊ አጠቃቀም ወይም ዓይነት የሚገኘው እንደ ሉቃስ 14፡26 ባሉት ጥቅሶች ነው። አንድ ሰው ክርስቶስን ይከተል ዘንድ በርግጥ ቤተሰቡን፥ ሚስቱን እንኳን ቢሆን መጥላት አለበት? እንዲያ ቢሆን ኖሮ አሳቡ በኤፌሶን 5፡25 ከሚገኘውና ከሌሎች ብዙ ክፍሎች ጋር ይቃረን ነበር። ይህ አባባል አንጻራዊ አሳብን በፍጹማዊ ፈሊጥ የመግለጫ መንገድ

ሲሆን፥ የኔ የሚባሉና የሚፈቀሩ ነገሮች ሁሉ ለክርስቶስ ካለን ፍቅር አኳያ ሁለተኛ ደረጃ ሊሰጣቸውና እጅግ ወደ ኋላ ሊርቁ ይገባል የሚል ውሳኔ ያስፈልጋል ማለት ነው (ማቴ. 10፡37ን ከዚህ አሳብ ጋር ያነጻጽሩት)። ሮሜ 9፡13ንም ይመልከቱ።

ይህን ፈሊጣዊ አነጋገር እንዴት ሊገነዘቡት ይችላሉ? በመጀመሪያ እንደ ቀጥተኛ አባባል ይመልከቱት። ስሜት ይሰጣል? ወይም ግልጥ ነው? ካልሆነ እንደ ፈሊጣዊ አነጋገር ይቁጠሩት። በራሱ አገባብ ያጥኑት፤ ያኔ ትክክለኛ ትርጉሙን ለማግኘትዎ አንዳንድ ማረጋገጫዎች ያያሉ።

3. *አንጻራዊ ለፍጹማዊ።* ይህ ቀደም ሲል የተመለከትነው ፈሊጥ ተቃራኒ ነው። እዚህ ላይ ትርጉሙ ፍጹማዊ ሲሆን፥ ቅርጹ ግን አንጻራዊ ወይም ተወዳዳሪ ነው። ኢየሱስ ሉቃስ 11፡31-32 ላይ፡- "እነሆም፥ ከሰለሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ። . . .እነሆም ከዮናስ የሚበልጥ ከዚህ አለ" ይላል። ማን ወይም ምንድነው ከሰለሞንና ከዮናስ ጋር የተወዳደረ ወይም የተነጻጸረው? ከራሱ ከክርስቶስ በቀር ማንም ሊሆን አይችልም። ከነርሱ ምን ያህል ይበልጣል? ክርስቶስ ሰው ብቻ ቢሆን ኖሮ፥ ተቀባይነት ያለው ማወዳደሪያ ሊኖር ይችል ነበር፤ ነገር ግን እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ በመሆኑ ምንም ማወዳደሪያ የለም። ልዩነቱ በአንጻራዊነት ቢገለጥም ፍጹም ነው።

ብዙውን ጊዜ በእያንዳንዱ ሁኔታ አገባቡ መከፈቻውን የሚሰጥ ስለሆነ፥ ይህ ፈሊጥ በጣም ግልጥ ነው። የቱን ያህል የሚበልጥ? የቱን ያህል የሚሻል? ብለን ስንጠይቅ፥ ነጥቡን ወይም ጉዳዩን ልናይ እንችላለን። ከዚያ በኋላ አባባሉ ቀጥተኛ ይሁን ወይም ፈሊጣዊ ትንሽ አሳብ ይሰጠናል። እነዚህን ማመሳከሪያዎች ይመልከቷቸው፡- 1ኛ ሳሙኤል 15፡22፤ ዕዝራ 9፡13፤ መዝሙር 118፡8-9፤ ምሳሌ 21፡3፤ ዕብራውያን 1፡4፤ 3፡3፤ 6፡9።

4. *"የ. . ወንድ ልጅ" ወይም "የ. . .ሴት ልጅ"።* ይህ አገላለጥ ብዙ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ያጠቃልላል፡-

(ሀ) "ልጅ" የሚባለው ከአብራክ የወጣ ቢሆንም፥ በዘር ሐረግ ራቅ ያለ፥ ማለትም የልጅ ልጅ ወይም ከዚያ የራቀ ሊሆን ይችላል። ዕብራውያን "ወለደ" የሚለውን ግሥ በተመሳሳይ ሁኔታ ተጠቅመው በታል። ቃሉ ከአብራክ ለወጣ ወይም በትውልድ መሥመር ለተገኘ ለማንም መጠሪያ ሊሆን ይችል ነበር። ዕብራውያን ማን የማን አባት እንደነበረ አልዘነጉትም ወይም በግድየለሽነት አልጻፉም፤ ይህን ፈሊጥ በመጠቀም ተናገሩ ወይም መዘገቡት እንጂ። ይህ የሚያሳየን ስሕተት

መስሎ የሚታየን ነገር በእርግጥ ስሕተት አለመሆኑን ነው። ማቴዎስ 1፡8፤ ኢዮራም ዖዝያንን ወለደ ይላል፤ ነገር ግን 1ኛ ዜና 3፡11-12 በነዚህ ሁለት ስሞች መካከል ሦስት ትውልዶች የተዘለሉ መሆኑን ያመለክታል። (አዛሪያ ማለት ዖዝያን ነው።) ሌሎች ማገናዘቢያዎች 1ኛ ነገሥት 15፡3፤ 1ኛ ዜና 26፡24 ናቸው።

ለ. አንድ ሰው የተወሰነ ባሕርይ፥ ምናልባት ከአባቱ የወረሰውን ተፈጥሮ ከያዘ፥ ያን ባሕርይ በሚገልጥ ስም ይጠራል። በሐዋርያት ሥራ 4፡36 እንደምናነበው ሐዋርያት፥ አንዱን ሰው "በርናባስ" ብለው ስም አወጡለት፤ ምክንያቱም ሰውዬው፥ ስሙ እንደሚያመለክተው፥ "የመጽናናት ልጅ" ነበር። (በተጨማሪ ኢዮብ 41፡34፤ ኢሳ. 14፡12፤ ማቴ. 8፡12፤ ሉቃስ 10፡6፤ ኤፌ. 2፡3፤ 5፡6፤ 1ኛ ተሰ. 5፡5ን ይመልከቱ።)

ሐ. "ልጅ" ማለት ፍቅርን፥ "ልጅዎ" ማለት ደግሞ የሥጋ ዝምድና በሌለበት አክብሮትን ያመለክታል። 1ኛ ሳሙኤል 24፡16 እና 25፡8ን ይመልከቱ።

መ. ኤርምያስ 31፡9 ላይ ሕዝቡ በእግዚአብሔር "ልጅ" ተብሎ ተጠርቷል። "እኔ ለእስራኤል አባት ነኝ፥ ኤፍሬምም በኩሬ ነውና" ይላል። (ሆሴዕ 11፡1ን በተጨማሪ ይመልከቱ።)

ሠ. ዜጎች "የሕዝቡ ልጆች" ተብለው ይጠራሉ። ሰቆቃወ ኤርምያስ 4፡2ን ወይም ዘካርያስ 9፡13ን ይመልከቱ። መላው ሕዝብ የጽዮን "ሴት ልጅ" ወይም "ድንግሊት" ተብሎ ተጠርቷል (ሰቆ. 2፡13)።

እነዚህን ፈሊጦች በመፍታቱ ረገድ ትልቅ ችግር አይገጥምም። ከላይ የተጠቀሱትን መንገዶች ሲረዱ እያንዳንዱን ጥቅስ በአገባቡ መሠረት ሊመለከቱት ይችላሉ። የፈሊጣዊ አነጋገሩ ልዩ ሁኔታ ብዙውን ጊዜ በሚገባ ግልጥ ነው። ይህ ስለ ትውልድ ሐረግ ታሪክ ከሚናገሩ ክፍሎች ጋር ተመሳሳይ አይሆን ይሆናል። ከዚህ የተነሣ ከሌሎች ምንባቦች አንዳንድ ንጽጽሮችን ማድረግ ይኖርብዎ ይሆናል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ግን ለመወሰን የማይቻል ይሆን ይሆናል።

በብዙ ክፍሎች "የ...ልጅ" የሚል ቃል በሚያነቡበት ጊዜ ፈሊጣዊ አነጋገር ሳይሆን፥ ቀላልና ቀጥተኛ አባባል መሆኑን ይገንዘቡ። አንዳንድ ልዩ የሆኑ ሁኔታዎች ደግሞ አሉ። በኢዮብ 1፡6 እና 2፡1 እንዲሁም ምናልባት በዘፍጥረት 6፡2፥4 "የእግዚአብሔር ልጆች" የሚለው ቃል መላእክትን ያመለክታል። "የሰው ልጆች" የሚለው "ሰዎች" የሚል ሲመስል፥ በተጨማሪም በሕዝቅኤል በብዙ ክፍሎች ለምሳሌ፦ (2፡1፤ 3፡1፤ 4፡1) "የሰው ልጅ" የሚለው "ሰው"ን

የሚያመለክት ሐረግ ነው። ነገር ግን የዳንኤል ትንቢት ስለ ክርስቶስ በሚናገርበት ጊዜ ከሰው ስለሚበልጠው ሰው ነው የሚገልጠው (ዳን. 7፡13)።

"የ...ልጅ" የሚለውን የዚህን ሐረግ ልዩ ጥቅምም መመልከት አለብን፦ ከክርስቶስ መጠሪያዎች ወይም ስሞች አንዱ፦ "የእግዚአብሔር ልጅ" የሚል ነው። ይህ መጠሪያ ቢያንስ በአንድ ክፍል (ሉቃስ 1፡30-35) ከክርስቶስ በመንፈስ ተጸንሶ ከድንግል መወለድ ጋር በተገናኘ ሁኔታ ተጠቅሷል። ነገር ግን በመላው የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ለማለት ይቻላል፥ ይህ መጠሪያ ከእግዚአብሔር አብ ጋር አንድ ባሕርይ ያለው ዘላለማዊ ልጁ መሆኑን ያመለክታል። ትርጉሙ ከእግዚአብሔር ያንሳል የሚል ሳይሆን፥ እርሱ በእውነት እግዚአብሔር መሆኑን የሚያመለክት ነው። እነዚህን ክፍሎች ያጥኑ፦ ዮሐንስ 10፡33-36፤ 19፡7፤ ዕብራውያን 1፡8።

አማኞችም "የእግዚአብሔር ልጆች" ተብለዋል። ይህ አማኞች "የመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች" (2ኛ ጴጥ. 1፡4) መሆናቸውንና እንደ ክርስቶስም እንዲከብሩ (1ኛ ዮሐ. 3፡2) የተወሰነ መሆኑን ያመለክታል። በጭራሽ እግዚአብሔር አይሆኑም፤ ነገር ግን አገልጋዮቹና ለዘላለምም የሚያመልኩት ይሆናሉ (ራእይ 22፡3)።

5. *"ዘላለም" የሚለው ቃል በቀጥታ ሲተረጎም 'የማያቋርጥ' ወይም "ለምን ጊዜውም" ማለት ነው።* የቃሉ ቀጥተኛ ትርጉም ምሳሌዎች መዝሙር 9፡7 ("እግዚአብሔር ግን ለዘላለም ይኖራል") እና መዝሙር 45፡6 ("አምላክ ሆይ፥ ዙፋንህ ለዘላለም ነው") የሚሉት ናቸው።

በፈሊጣዊ ትርጉሙ፦ "የተጠቀሰው ነገር በዘመኑ ሁሉ ያለመሰናከል የሚቀጥል ወይም ያለጣልቃ ገብነት የሚኖር" ማለት ነው። ዘጸአት 21፡6 አንድ ባሪያ በሰባተኛው ዓመት (ቁ. 2) ነጻ ሆኖ መሄድ የማይፈልግና ለጌታው መገዛቱን ለመቀጠል የሚፈቅድ ከሆነ፥ ለዚሁ ምልክት ይሆን ዘንድ ጆሮው ተበስቶ "ለዘላለምም ባሪያ ይሁን" በማለት ያስተምራል። ጌታውና ባሪያው፥ ሁለቱም፥ በመጨረሻ ስለሚሞቱ አገልግሎቱ ያበቃል። በዚህ ስፍራ "ለዘላለም" ማለት ሁለቱም፥ ጌታውና ባሪያው በሕይወት እስካሉ ድረስ አገልግሎቱ አይቋረጥም ማለት ነው። የ1980 ዓ.ም. እትም የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ይህን "እስከዕድሜ ልኩ ድረስ ባሪያ ሆኖ ያገለግለው" በማለት ይተረጉመዋል።

ይህንኑ ቃል በተጨማሪ በመዝሙር 72፡17 ላይ፥ "ስሙ ለዘላለም ብሩክ ይሆናል፥ ከፀሐይም አስቀድሞ ስሙ ይኖራል" ተብሎ እናገኘዋለን። ሁለተኛው ስንኝ የመጀመሪያው ትይዩ ወይም ተመሳሳይ

ነው። ስለዚህ "ለዘላለም" የሚለው ቃል ትርጓሜ ፍጻሜ የሌለው ማለት አይደለም። ፀሐይ ትጠፋለች፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ሥርዓት እስከቀጠለ ድረስ ስሙን ወይም ክብሩን ምንም ሊሽረው አይችልም።

ይህ "ለዘላለም" የሚለው ቃል ፈሊጣዊ አገባብ፥ ትርጉሙን በሙሉ አያስወግድም። ታላቅ ትርጉም አለው። ሰውየው ወይም የተባለው ነገር እስከኖረ ድረስ ያለማቋረጥ የሚቆይ መሆኑን ይገልጣል። በተለይም ከእግዚአብሔር የተሰጠ ተስፋ ወይም ትእዛዝ ከሆነ፥ ምንም ሊያቆመው ወይም ጣልቃ ሊገባበት አይችልም። የእግዚአብሔር ተስፋዎች እውነት ወይም አይቀሬ ናቸው። ወይም ጌታ ለዘላለም የሚኖር መሆኑን የሚገልጡትንና፥ መጨረሻ የሌላቸው እውነቶችን በተመለከተ ጥያቄ አያነሣም። ይሁን እንጂ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋ ባለን እውቀት ትክክለኞች ለመሆን ይህን ፈሊጣዊ አነጋገር መገንዘብ ይኖርብናል። ሌሎች ጥቅሶች፡- 2ኛ ነገሥት 5፡27፤ 2ኛ ዜና 7፡16፤ መዝሙር 49፡11፤ ኢሳይያስ 32፡14-15፤ ኤርምያስ 31፡35-36 ናቸው።

## የትርጓሜ መሪ ነጥቦች

1. *የተለያዩ ፈሊጣዊ አነጋገሮችንና ተስማሚ ትርጉማቸውን ይማሩ።*

2. *አንድ ምንባብ ቀጥተኛ ወይም ቃል በቃል ሊሆን ይችል እንደሆነ ይመልከቱ።* ስሜት የማይሰጥ ከሆነ፥ ፈሊጣዊ አነጋገር ሊኖረው ይችላል ብለው ያስቡ።

3. *አገባቡን ይመርምሩ።* ይህን በማድረግ ብዙ ጊዜ ለትርጓሜው የሚሆን መክፈቻ ያገኛሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ እኛ ያልተነጋገርንባቸው ሌሎች ብዙ ፈሊጣዊ አነጋገሮች አሉት። ከተቻለ እነርሱን ለመማርና ለመረዳት ተጨማሪ መጻሕፍትን ያገናዝቡ። እንዲሁም ተጨማሪ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ለመለየት በጥንቃቄ ያጥኑ።

# 18

# የዕብራይስጥ ሥነ-ግጥም

ሥነ-ግጥም የሰውን አንዳንድ ጥልቅና ምጡቅ የልብ አሳቦችና ስሜቶች መግለጫ ነው። ልንገልጠው አይቻለን ይሆናል እንጂ፥ ሥነ-ግጥም መሆኑን ለማወቅ እንችላለን። ሥነ-ግጥም በአማርኛ ቋንቋ ዜማዊ ቅላጼ ባላቸውና ቤት በሚመቱ ስንኞች የሚታወቅ የአወቃቀር ቅርጽ ያለው የሥነ-ጽሑፍ ዘርፍ ሲሆን፥ ቋንቋው ብዙውን ጊዜ ውብና ረቂቅ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ሥነ-ግጥሞች አሉት፤ እነርሱም፦ መዝሙሮችና ምሳሌዎች ብቻ ሳይሆኑ ኢዮብ፤ መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን፤ ሰቆቃወ ኤርምያስና ከነቢያት መጻሕፍት ጭምር ናቸው። አንዳንዶቹ የኢየሱስ አባባሎች እንኳን ሥነ-ግጥማዊ ይመስላሉ። (ማቴ. 7፡6ና ዮሐ. 6፡35ን ይመልከቱ።) አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ሥነ-ግጥሞችን እንደ ግጥምነታቸው አያትሟቸውም። አንዳንዶቹ ግን ያትሟቸዋል።

## የሥነ-ግጥም መለያ ወይም ገጽታዎች

የመጽሐፍ ቅዱስ ሥነ-ግጥም መለያ ወይም ገጽታዎች በዕብራይስጥ ቋንቋ ግልጥ ቢሆኑም፥ ከትርጉም ብዛት ጠፍተዋል። ትርጓሜን ለመረዳት ይቻለን ዘንድ፥ በእጃችን በሚገኙት ቅዱሳት መጻሕፍት ያሉትን ሥነ-ግጥሞች ለመገንዘብ መቻል አለብን።

1. *ትይዩ ወይም ተመሳሳይነት [Parallelism]።* የዕብራይስጥ ሥነ-ግጥም ዋና መለያ ወይም ገጽታ፥ ግጥሙ ቤት የሚመታው ከድምፅ ይልቅ በአሳቡ መሆኑ ነው። ይህ ትይዩ ወይም አንጻር ይባላል። ይህ በቀላሉ የሚያስረዳን ሥነ-ግጥሙ የተጻፈው በጥንድ ስንኞች መሆኑን ሲሆን፥ አንዱ ስንኝ ከሌላው ጋር በአንድ ሁኔታ ይገናኛል። አንዳንድ ጊዜ ሦስት (ኢሳ. 41፡5) እንዲያውም አራት (መዝ. 27፡1) ስንኞች ቢኖሩም ብዙ ጊዜ ግን ሁለት ናቸው። ለምሳሌ፦

"ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ
ከኃጢአቴ አንጻኝ፤" (መዝ. 51፡2)

የሁለቱ ስንኞች ግንኙነት ሁልጊዜ ተመሳሳይ አይሆን ይሆናል። እርግጥ የተለያዩ መሠረታዊ አሳቦችን ለመግለጥና ስለተለያዩ አንጻሮች ለመናገር እንችላለን። ከነዚህም እያንዳንዱ የራሱ ተገቢ መጠሪያ አለው።

*ሀ. ድግግሞሽ በተመሳሳይ፥ እንዲሁም በትይዩ ወይም በአንጻር ይገለጣል።* በዚህ ጊዜ ሁለቱ ስንኞች አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ

አሳብን በተለያዩ ቃላት ይገልጣሉ። ኢሳይያስ 1፡3 መልካም ምሳሌ አለው፦

"እስራኤል ግን አላወቀም፥

ሕዝቤም አላስተዋለም።"

ሁለተኛው ስንኝ ለግልጥነት ወይም ለአንድነት ሲባል ያንኑ አሳብ ይደግመዋል። መዝሙር 33፡2 በቅርጽ ተመሳሳይ ነው፦

"እግዚአብሔርን በመሰንቆ አመስግኑት፥

አሥር አውታርም ባለው በገና ዘምሩለት።"

እዚህ ላይም አጠቃላይ አሳብ አለ፤ መጠቀሚያ መሣሪያውና ድርጊቱ ግን የተለያዩ ናቸው።

በዚህ ትይዩነት ውስጥ ብዙ ጊዜ አንድ ስንኝ ሌላውን ግልጥ ያደርገዋል (እንደገና የአገባብ መመሪያ መሠረት መሆኑ ነው)። ለምሳሌ፥ ኢሳይያስ 45፡7፦

*"ብርሃንን ሠራሁ፥ ጨለማውንም ፈጠርኩ፤*

*ደኅንነትን እሠራለሁ፥ ክፋትንም እፈጥራለሁ፤*

እነዚህን ሁሉ ያደረግሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ።"

በመጀመሪያው መሥመር "ብርሃን"ና "ጨለማ"፥ በሁለተኛው ደግሞ "ደኅንነት"ና "ክፋት" በተቃራኒነት ተገልጠዋል። ክፋት የደኅንነት ተቃራኒ ከሆነ ዘንድ ክፋቱ የሥነ-ምግባር ሳይሆን፥ ያለመረጋጋት ወይም ግራ የመጋባት ክፋት ነው። ጥቅሱ ክፉ ነገር አድራጊው እግዚአብሔር ነው አይልም።

ለ. *ንጽጽር በተቃርኖ ትይዩነት ይገለጣል።* እውነትን ይበልጥ ለማጉላት ሁለቱ ስንኞች ተነጻጻሪ፥ እንዲያውም ተቃራኒ አሳቦችን ይገልጣሉ። መጽሐፈ ምሳሌ የዚህ ዓይነቱ አያሌ ትይዩነት አለው። ብዙ ጊዜ ከስንኞቹ ሁለተኛው መሥመር ንጽጽርን ለማመልከት "ግን" በሚል ቃል ይጀምራል። ለምሳሌ 15፡1፦

"የለዘበች መላስ ቁጣን ትመልሳለች፤

ሸካራ ቃል ግን ቁጣን ታስነሣለች።"

(በተጨማሪም ከአሥራ አራቱ ቁጥሮች እያንዳንዱ ተቃራኒ ትይዩነት ያለው መሆኑን በመጽሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ 10 ላይ ይመልከቱ።)

ሐ. *መጨመር፥ ይህ በ'ውሑድ' ትይዩነት ይገለጣል።* በዚህ የሥነ-ግጥም ዓይነት፥ ሁለተኛው ስንኝ ለመጀመሪያው ተጨማሪ አሳብን ያክልለታል። አንዳንድ ጊዜም በመጀመሪያው መሥመር ለተገለጠው አሳብ ምክንያቱን ይሰጣል። ወይም "...ዘንድ" የሚል ቃል በማከል ዓላማን

ያሳያል (መዝ. 104፥5)። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ይህ ትክክለኛ ትይዩ አይደለም ይላሉ፤ ሆኖም ተዛማጅ ስንኞችና ተመጣጣኝ አባባሎች ስላሉት ትይዩ አድርገን ልንመለከተው እንችላለን።

*መ. ማስፋፋት፥ በማከተሚያዊ ትይዩነት ይገለጣል።* የዚህ ሥነ-ግጥም ሁለተኛ ስንኝ በመጀመሪያው ስንኝ ከተገለጠው ከፊሉን የሚደግም ሲሆን፥ አዲስ ነጥብ ወይም አሳብም ያክልበታል። ለምሳሌ መዝሙር 34፥4፡-

"እግዚአብሔርን ፈለግሁት መለሰልኝም፥
ከመከራዬም ሁሉ አዳነኝ።"

የትኛው አሳብ ነው ከመጀመሪያው ስንኝ በሁለተኛው የተስፋፋው?

*ሠ. ለውጥ፥ ይህ የሥነ-ግጥም ዓይነት በአርማዊ ወይም ልዩ ምልክታዊ ትይዩነት ይገለጣል።* አርማዊ ማለት ተምሳሌታዊ ወይም ተወካይ ማለት ነው። አንደኛው ስንኝ ቀጥታ ሲሆን፥ ሌላው ዘይቤያዊ ነው። ብዙ ጊዜ ሁለቱም ስንኞች ስለ አንድ ነገር ስለሚናገሩ ግጥሙ አምሳያዊ ትይዩም ይሆናል። በአንደኛው ቅርጽ ንጽጽርን ይገነዘባሉ። ለምሳሌ መዝሙር 42፥1 እንዲህ ይላል፡-

"ዋላ ወደ ውኃ ምንጭ እንደሚናፍቅ፥
አቤቱ፥ እንዲሁ ነፍሴ ወደ አንተ ትናፍቃለች።"

ስለተጠማው ዋላ የሚናገረው ንጽጽር፥ መዝሙረኛው ለእግዚአብሔር ስላለው ናፍቆት በሚናገረው ላይ ውበትንና ግልጥነትን ይጨምርበታል። ይህ ሁኔታ በኢሳይያስ 46፥11፥ "ከምሥራቅ ነጣቂ ወፍን፥ ከሩቅም አገር ምክሬን የሚያደርገውን ሰው እጠራለሁ" እንደተባለው፥ ተለዋጭ ዘይቤ ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር ምክሩን የሚቀበልና የሚያደርገውን ሰው ነጣቂ ወፍ ነው ይለዋል። በትይዩ ወይም በአንጻራዊ ንግግር ያለን የአጠቃቀም እውቀት "ነጣቂ ወፍ" የሚለው ቃል ቀጥታ ወይም ቃል በቃል የሚፈታ ያለመሆኑን እንድንገነዘብ ይረዳናል።

ስንኞቹ ከነዚህ ከተነጋገርንባቸው የሥነ-ግጥም ቅርጾች ከአንዱም የማይመስሉባቸው ብዙ ስፍራዎች ይገኛሉ። ዓይነቱን ለመሰየም ቢከብድዎ አይጨነቁ። ብዙ ጊዜ ግን ትርጉሙ ግልጥ ሆኖ ያገኙታል (ለምሳሌ፡- መዝ. 47፥4፥ 9)።

አያሌ የትይዩ ዓይነቶች አሉ፤ ሁሉም ግን ግልጥ አይደሉም። አንዳንዶቹ ስንኞች ከፊል አሳብ ወይም አወቃቀር ነው ያላቸው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች የሥነ-ግጥም አጻጻፍ በዘፈቀደ የተደረገ አልነበረም። ብዙ ጊዜ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ስንኞችን በጥምር ትይዩነት ያገናኟቸዋል። ሥነ-ግጥሙን በሚያጠኑበት ጊዜ የተለያዩ ምሳሌዎችን ሊያገኙ ይችላሉ።

አንጻርን ወይም ትይዩነትን እንዴት ልንተረጉመው እንችላለን? የሥነ-ግጥም ስንኞች የተዛመዱ መሆናቸውን ስንረዳ፥ እያንዳንዳቸውን በተናጠል ሳይሆን ግንኙነታቸውን ለመመልከት እንጥራለን። አንዳንድ ግንኙነቶች ሊኖሩ እንደሚችሉም እናውቃለን። በመሆኑም ስለ ትርጉሙ ጥርጣሬ ካለን፥ ተስማሚውን ለመምረጥ የተለያዩ አማራጮችን እንሞክራለን። ይህ እንዴት እንደሚሠራ በአንድ ምሳሌ እንመልከት። መዝሙር 22፡16፦

"ብዙ ውሾች ከብበውኛልና፤
የክፉተኞች ጉባኤም ያዘኝ፤
እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ።"

ነገሩ እንግዳ ቢመስልም፥ መዝሙረኛው በውሾች መንጋ መከበቡ እውነት ሊሆን ይችላል። ይህ ምትክ፥ ወይም ምሳሌያዊ ትይዩ ከሆነ "ውሾች" የሚለው ቃል በሁለተኛው ስንኝ ላለውና "ክፉተኞች" ለሚለው ቃል ዘይቤያዊ አነጋገር ነው። ምዕራፉን በሙሉ ስናነበው (የዚህን ጥቅስ አገባብ ማለት ነው) ሌሎች ዘይቤዎችን እንገነዘባለን። የነፍሳትን መጠቀስ ጨምሮ (በቁጥር 6 "እኔ ትል ነኝ") ይላል፤ ይህ በዚህ ምንባብ ውስጥ፥ የምሳሌያዊ ትይዩ አጠቃቀምን ያመለክታል።

እንዲሁም "ወይን መጠጣት" የሚለው አገላለጥ ቀጥተኛ ወይም ዘይቤያዊ ሊሆን የሚችልበትን ሁኔታ ከመዝሙር 60፡3 ያጥኑ። ይህን ጥቅስ ምትክ ወይም ምሳሌያዊ እንደሆነ መገንዘቡ፥ እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚያሰክር መጠጥ እንዲጠጡ አደረገ የሚለውን ትርጉም ያስወግዳል። በዚሁ መዝሙር ያሉ ሌሎች ዘይቤዎች በተጨማሪ ይህ ስንኝ ምናልባት ዘይቤያዊ ሊሆን እንደሚችል ያመለክታሉ።

2. *አምሳል ወይም ቅርጽ [Imagery]።* ሥነ-ግጥም ሁሉ ውብ፥ ስሜት የሚነካና ግልጥ ሥዕሎች ያሉት ዘይቤያዊ ቋንቋ አለው። በመጽሐፍ ቅዱስ ሥነ-ግጥም ውስጥ የተለያዩ ዘይቤያዊ አነጋገሮችን እናገኛለን። ለነዚህ እንዴት ትርጓሜ ልንሰጣቸው እንደሚገባ ቀደም ሲል ተመልክተናል።

3. *ግነታዊ ቋንቋ [Hyperbolic Language]።* ግነት ዘይቤያዊ አነጋገር ነው፤ ነገር ግን ሥነ-ግጥም ውስጥ ያለው ስፍራ እጅግ የጎላ ስለሆነ ለብቻው ልንመለከተው ይገባል። ሥነ-ግጥም ብዙ ጊዜ ከባድ ስሜትን

ይገልጣል፤ እናም ገጣሚው ጥልቅ ስሜቱን ለመግለጥ ሲል ያልተለመደ ወይም የተጋነነ ቋንቋ ለመጠቀም የሚገፋፋ ወይም የሚገደድ ይመስላል። እንዲህ ያሉ አባባሎችን ካልተገነዘብን አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን መረዳቱ ያስቸግራል።

ኢዮብ ለዚህ የሚረዳ አንድ ምሳሌ ሲሰጥ፥ ምዕራፍ 6፡26 ላይ "ተስፋ የሌለው ሰው ንግግር እንደንፋስ ነውና" በማለት ይህን አባባሉን ጓደኞቹ እንዲገነዘቡለት ይጠይቃል። ንግግሩ የተጋነነ መሆኑን ያውቃል። በ16፡12-13 ላይ እግዚአብሔር፥ "...አንገቴን ይዞ ቀጠቀጠኝ፤...ኩላሊቴንም ቆራረጠ" በማለት የቀድሞውን የመሰሉና ያልተለመዱ ቃላትን ይናገራል። ምዕራፍ ሁለትና ሦስት እንደሚያመለክቱት በግልጥ ወይም ቃል በቃል አይደለም የሚናገረው። ነገር ግን ጥልቅና ከባድ የሆነ ስሜቱን ማውጣቱ ነው። ንግግሩን በዚህ አኳኋን ልንረዳ እንችላለን። እንዲህ ያሉ ብዙ ምሳሌዎችን በመዝሙረ ዳዊት፥ በሰቆቃወ ኤርምያስና በትንቢተ ኤርምያስ ውስጥ ያገኛሉ።

እንዲህ ያለው ልዩ ቋንቋ ወይም አገላለጥ እርግማን በሚባሉት መዝሙሮች ውስጥም ይገኛል። እነዚህ መዝሙሮች ጸሐፊው የእግዚአብሔር ፍርድ ወይም ቁጣ በጠላቶቹ ላይ እንዲወርድ የሚጠይቅባቸው ሲሆኑ፥ ከነዚህ ዋና ዋናዎቹ፡- መዝሙር 58፡6-11፤ 59፡5፥ 13፤ 69፡22-23፤ 109፡6-15፤ 137፡8-9፤ 139፡19-22፤ 143፡12 ናቸው።

የነዚህ ምንባቦች አገላለጥ ወይም አዘማሚያ እግዚአብሔር ለኃጥአን ካለው የመሐሪነትና የፍቅር ባሕርይ ጋር የሚቃረን ስለሚመስል ምንባቦቹ በአተረጓጎም ረገድ የጎላ ችግር አላቸው። ጸሐፊዎቹ አሳባቸውን በታማኝነት ወይም በቅንነት የሚገልጡ ሆነው ገለጣቸው ግን ከእግዚአብሔር ፈቃድና ዓላማ ጋር የማይሄድ ነው ካልን፥ በቀረው የመዝሙር ክፍል ያለው አሳብ የእግዚአብሔር ይሁን ወይም የሰው ለመለየት ያስቸግረናል። ይህ ችግር ቀላል መልስ የለውም። ምንባቦቹን በጥንቃቄ፥ በተለይም በመዝሙሩ ርእስ የተመለከተው መነሻ በሚፈነጥቅልን ብርሃን መሠረት ልንመለከታቸው ይገባል። ለዚህ ሊያግዙ የሚችሉ አንዳንድ ነጥቦች እነሆ፡-

*ሀ. አንዳንድ ከባድ አገላለጦች፥ ቃል በቃል ወይም በቀጥታ የማይወሰዱና ዘይቤያዊ የሆኑ ናቸው።* ኢዮብ ስለ እግዚአብሔር በከባድ ቃል ወይም ድፍረት እንደተናገረ ሁሉ፥ መዝሙረኛውም፡- "ዓይኖቻቸው ይታወሩ"፥ "ጥርሶቻቸው በአፋቸው ውስጥ ይሰበሩ"፥ "ጻድቅ ...በኃጢአተኛው ደም እጁን ይታጠባል"፥ "ሕጻናቶችሽን ይዞ በዓለት

ላይ የሚፈጠፍጣቸው የተመሰገነ ነው” በማለት ተመሳሳይ ቋንቋ ይጠቀማል። ይህን በቀጥታ ወይም ቃል በቃል መውሰድ አግባብ አይሆንም። ጸሐፊዎቹ ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅር፥ እንዲሁም ምሕረቱን በሚያቃልሉ አመጸኞች ስለሚረክሰው እውነትና ቅድስና ያላቸውን መጨነቅ ነው የሚገልጡት። ጠንካራ ወይም ኃይለኛ ስሜት ክፉ ያናግራል። የዚህን መረዳት ከባድ ከሚያደርጉብን ምክንያቶች አንዱ፥ ምናልባት የመዝሙሩ ጸሐፊዎች ስለ እግዚአብሔር ከነበራቸው ታላቅ ቅናት ጥቂቱን ብቻ ማወቃችን ይሆናል።

ለ. *ጸሐፊዎቹ የሚናገሩት ስለ ግል ጠላቶቻቸው ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ጠላቶች ስለሆኑትም ነው።* በሌላ አነጋገር ፀቡ የግል አይደለም። ይህ ነጥብ በተለይ መዝሙር 139 ላይ ግልጥ ነው። ጸሐፊው ለእግዚአብሔር የማይታዘዙትን ወይም ኃጥአንን እንደሚጠላ ይናገራል። በአዲስ ኪዳንም ተመሳሳይ አገላለጥ ያላቸውን ቃላት፥ ክርስቶስ የተናገ ራቸውን አንዳንድ ቃላት ሳይቀር፥ ለማግኘት ይችላሉ፡- ማቴዎስ 18፡5-6፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 16፡22፤ ገላትያ 1፡8-9፤ ራእይ 6፡10፤ 18፡20።

ሐ. *ዳዊት፥ ስለ ጠላቶቹ፥ ሳኦልንም ጨምሮ፥ በጻፈውና ከሳኦል ጋር በነበረው ግንኙነት መካከል ያለውን ልዩነት ያስተውሉ።* መዝሙር 18፡40 ላይ፥ “የሚጠሉኝን አጠፋሃቸው” በማለት ጽፏል። የመዝሙሩን ርእስ ያስተውሉ። 1ኛ ሳሙኤል 24፡1-7 እና 26፡1-11 ውስጥ እንደምናነበው፥ ሳኦልን ሁለት ጊዜ በትዕግሥትና ራሱን በመቆጣጠር አልፎታል፤ ሊጎዳው አልፈለገም። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስን አንድ ክፍል፥ ከሌላው የማገናዘብ ሁኔታ፥ ቋንቋው ግነታዊ ዘይቤ መሆኑን ለማረጋገጥ ይረዳል።

የመጽሐፍ ቅዱስ *ሥነ-ግጥም* የእግዚአብሔርን ጸጋ ከሚያውቁና ከሚሹ፥ ጥልቅ በሆነ የኀዘን ስሜት፥ ፍቅር፥ ምስጋናና ተመስጦ ልባቸውን እፊቱ ከሚያፈሱ፥ እንዲሁም እንደኛ ኃጢአተኞች ከሆኑ ሰዎች ስለሚመጣ ለልባችን በግል ይናገራል። ከሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በበለጠ ሁኔታ በ*ሥነ-ግጥም* ራሳችንን መመልከትንና እግዚአብሔርን ማየትን እንማራለን።

## የትርጓሜ መመሪያ ነጥቦች

1. *የሥነ-ግጥም ጥንድ ስንኞች አንዱ ከሌላው ጋር የተዛመዱበትን ሁኔታ ለማየት ስንኞቹን ይተንትኗቸው።* እያንዳንዱን ከተለያዩ የትይዩ ዓይነቶች ጋር ያገናዝቡት። “እንደ” እና “ዘንድ” የሚሉትንና የመሳሰሉ ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ቃላትን ይፈልጉ። አንዱ ስንኝ ዘይቤያዊ ሆኖ፥

ሌላው ቀጥታ ወይም ቃል በቃል መሆኑን የሚያመለክቱ ሁኔታዎች መኖር አለመኖራቸውን ለማረጋገጥ ይሞክሩ።

2. *ዘይቤያዊ አነጋገሮችን ይፈልጉ።* በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ 13 ላይ በቀረቡት መመሪያዎች መሠረት ይተንትኑና ትርጓሜ ይስጧቸው።

3. *ኃይለኛ ወይም የቁጣ ቃል በሥነ-ግጥም ውስጥ ማግኘት የተለመደ በመሆኑ እንዲህ ያለውን ቃል ያጢኑ።* ለድ ንባብ እንዲህ ባለው ቋንቋ አይገለገልም። እንደዚህ ዓይነቱ ቋንቋ ወይም አነጋገር የሚገልጠው፥ ጸሐፊው በግል ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ጠላቶች ላይ ያለውን ጥላቻና ስሜት መሆኑን ይገንዘቡ።

# 19

# ትንቢት

የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ ትንቢትን በሚያጠናበት ጊዜ፥ ከትርጓሜ አበይት ችግሮች አንዳንዶቹ እንደሚገጥሙት አንድ ጸሐፊ ተናግሯል። ይህ እውነት ይሆን ይሆናል፤ ቢሆንም ሊያስፈራን ወይም ተስፋ ሊያስቆርጠን አይገባም። የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢትን በተመለከተ ትልቅ የእምነት ልዩነት እንዳለ እንገነዘባለን። ሆኖም ግን ስለ ክርስቶስ የመጀመሪያና ዳግም ምጽአት የተነገረው ትንቢት፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ እጅግ ጠቃሚ ክፍሎች አንዱ ነው። እግዚአብሔር ስለ ወደፊቱ ሁኔታ የገለጠውን ለመማር የሚቻለንን ጥረት ሁሉ ማድረግ አለብን።

ነቢይ፥ በመጀመሪያና ቀዳሚ ትርጉሙ፥ በሌላ ፋንታ የሚናገር አንድ ቃል አቀባይ ነው። አሮን የሙሴን መልእክት በመናገሩ የሙሴ ነቢይ መባሉን ዘጸአት 7፡1 ውስጥ ያስተውሉ። እንግዲህ የእግዚአብሔር ነቢይ፥ የእግዚአብሔርን መልእክት የሚያስተላልፍ ወይም በእግዚአብሔር ፋንታ የሚናገር ነው። ነቢዩ በተለይ ያለበትን ዘመን ሁኔታ አስመልክቶ ለሰዎች የሚናገር ሲሆን፥ ስለወደፊቱ ግን ይናገር ወይም አይናገር ይሆናል። "መተንበይ" የሚለው ቃል በጣም የተለመደ በመሆኑ፥ የትንቢትን ትርጓሜ በምንመለከትበት ጊዜ ሁሉ በዚህ አገባቡ እየተጠቀምን እግዚአብሔር የወደፊቱን ሁኔታ የተናገረባቸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ገለጣዎች ለመረዳት እንጥራለን።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ሰፊው ክፍል ትንቢቶችን ያካተተ ነው። እነዚህም የተለያዩ ሲሆኑ፥ በብሉይና በአዲስ ኪዳኖች ውስጥ ይገኛሉ።

1. *ፈጣን (በቅርብ ጊዜ የሚፈጸሙ) ትንቢቶች።* እንዲህ ያሉት ትንቢቶች በተነገሩ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚፈጸሙ ናቸው (ዘጸ. 14፡4፥ 13-17፤ ኤር. 38፡18)።

2. *ዘግየት እያሉ በዚያው ዘመን የተፈጸሙ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች።* ዘዳግም 28፡53 እና ሰቆቃወ ኤርምያስ 4፡10፤ ኢያሱ 6፡26 እና 1ኛ ነገሥት 16፡34።

3. *በአዲስ ኪዳን ዘመናት የተፈጸሙ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች።* እነዚህ ትንቢቶች በተለይ የክርስቶስን ማንነትና አገልግሎት የሚያመለክቱ፥ እንዲሁም የትንቢት ዋና ክፍል ስለሆኑ በአቢይነት የምንመለከታቸው ይሆናሉ። ስለዚህ ጉዳይ የሚጠቀሱ አያሌ ማስረጃዎች አሉ።

4. *በአዲስ ኪዳን ዘመናት የተፈጸሙ የአዲስ ኪዳን ትንቢቶችም አሉ (ማቴ. 16፡21 እና ማቴ. 27)።*

5. *ያልተፈጸሙ የብሉይና የአዲስ ኪዳን ትንቢቶች።* እነዚህ በአብዛኛው ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጋር የሚዛመዱ ስለሆኑ በጥልቀት እንመለከታቸዋለን።

ከነዚህ አንዳንዶቹ ይደራረባሉ። ለምሳሌ አንዳንዶቹ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች፥ ሁለቱንም የክርስቶስ ምጽአቶች የሚመለከቱ ናቸው። እንዲሁም የአሁኑን ጊዜና የክርስቶስን ዳግም ምጽአት የሚያመለክቱ አንዳንድ የአዲስ ኪዳን ትንቢቶች ገና ያልተፈጸሙ ናቸው።

በ1ኛ ጢሞቴዎስ 4፡1 እንደተገለጠው፥ ትንቢት ወደፊት ይፈጸማሉ ተብለው ከተነገሩ ግልጥ ነገሮች በላይ በአጠቃላይ የሚነገሩትንም የሚጨምር መሆኑን ልንረዳ ይገባል። ምሳሌ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኝ ሌላ የትንቢት ክፍል ነው። ራእይ እግዚአብሔር ትንቢታዊ መልእክቱን የሚያስተላልፍበት ልዩ መንገድ ነው። ራእይ ለነቢዩ ወይም ለባለ ራእዩ ለራሱ እንዲፈታለት የሚደረግበት ሁኔታ ነበር። ዳንኤል 4 እና ራእይ 17 መልካም ምሳሌዎች ናቸው።

## የትንቢት መለያዎች ወይም ባሕርያት

የመጽሐፍ ቅዱስን ትንቢቶች ለመፍታት አበይት ባሕርያቱን መረዳት ይገባናል።

1. *የነቢዩ ትንቢታዊ አመለካከት።* ነቢዩ እግዚአብሔር እንደገለጠለት የሩቆችንና የተለያዩ የወደፊት ሁነቶችን በመንፈስ ይመለከት ነበር ማለት ነው። ልምምዱም እጅግ የራቀን ተራራ በቅርቡ እንዳለ አድርጎ ከመመልከት ይመስላል። ለምሳሌ አንድ ሰው ብዙ የተራራ አናቶችን በሩቁ ሲመለከት፥ ከቆመበት ርቀት አንጻር የተቀራረቡ ይመስሉት ይሆናል። ሲቀርባቸው ግን የተራራቁ ሆነው ያገኛቸዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ ነቢያትም ሁለት ትልልቅ "የተራራ ጫፎችን" ተመለከቱ። የክርስቶስን የመጀመሪያና ዳግም ምጽአት፥ ሥቃይና ድሉን፥ እናም ሁነቶቹ የሚፈጸሙባቸውን ጊዜያት የተቀራረቡ በማስመሰል በአንድ ላይ ተናገሯቸው። በትክክለኛው ሁኔታ ወይም በቅደም ተከተላቸው ተቀራራቢ ሲሆኑ አሁን እንደምንረዳቸው ግን በጣም የተለያዩ ወይም የተራራቁ ናቸው።

ለምሳሌ በኢሳይያስ 61፡1-3 ያለውን ይመልከቱ። ክርስቶስ ይህን ክፍል ካነበበ በኋላ፥ ቃሉ ስለ እርሱ እንደሚገልጥ ጠቅሶ መጽሐፉ ወይም ትንቢቱ በዚያን ዕለት መፈጸሙን ተናግሯል (ሉቃስ 4፡16-21)።

በኢሳይያስ 61፡2 ግን ሁለት ታላላቅ አዋጆች ተተንብየዋል። አንዱ የጸጋ ጊዜ ሲሆን፥ ሌላው የበቀል ዘመን ነበር። ክርስቶስ የመጀመሪያውን አነበበና ሁለተኛውን ሳይነካ ንግግሩን አቋረጠ። ለምን? የበቀል ቀን የሚያመለክተው የትኛውን ዘመን ነው? በርግጥ የርሱን የመጀመሪያ ምጽአት ዘመን አልነበረም።

ያ ክፍል በዚያን ዘመን የሚፈጸም አልነበረምና አላነበበውም። በትንቢቱ ግን ሁለቱም እውነቶች ተቀራርበው ነው የተቀመጡት። እንደ ዘፍጥረት 3፡15 እና መዝሙር 22 ባሉት ክፍሎች ተመሳሳይ ምንባቦችን ሊያገኙ ይችላሉ።

2. *የቅርብና የሩቅ ፍጻሜ።* ብዙ ትንቢቶች ከሁሉ በፊት በተነገሩበት ዘመን በቅርብ የሚፈጸመውን ሁኔታ ያመለከቱ ቢሆንም፥ እግዚአብሔር የታሪክ ሁሉ ጌታ ነውና ትንቢቱ ቆይቶ እንዲፈጸም አዘዘ። ስለዚህ የአንድ ትንቢት የመጀመሪያ ክንውን፥ የሁለተኛው ተምሳሌት ነው። የዚህ ምሳሌ፥ ልጁን አስመልክቶ ለዳዊት የተሰጠው ተስፋ ነበር። በ2ኛ ሳሙኤል 7፡12-16 የተነገረው ትንቢት በግልጥ የሚያመለክተው የዙፋኑ ወራሽ የሆነውን ልጁን ሰለሞንን ነው። በዕብራውያን 1፡5 ላይ ግን ቁጥር 14 ክርስቶስን የተመለከተ ነው። እርሱ፥ ማለት ክርስቶስ የዳዊት ትልቅ ልጅ ሲሆን፥ ሰለሞን ደግሞ የክርስቶስ አምሳያ ነው። ሰለሞን የዳዊት፥ እንዲሁም የእግዚአብሔር ልጅ ነበር። እጅግ ልዩና ታላቅ በሆነ አኳኋን ቢሆንም፥ ክርስቶስም እንደዚሁ ነው።

ዕንባቆም 1፡5-6 እና የሐዋርያት ሥራ 13፡41 የትንቢትን ሁለት ጊዜ መፈጸም የምናይበት ሌላው ከአዲስ ኪዳን የምናገኘው መረጃ ነው። እንደዚህ ያለ መረጃ ሲኖረን ስለ ትርጓሜው እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን። ይህ ከሌለን ግን ቀኖናዊያን መሆን የለብንም።

ይህን የሚመስልና ትርጓሜ ለመስጠት የሚከብደው ትንቢት ግን፥ ክርስቶስ ከድንግል እንደሚወለድ ኢሳይያስ የተናገረው ነው (ኢሳ. 7፡14)። አካዝ እንደ እግዚአብሔር ቃል አልታዘዝ ሲል፥ እግዚአብሔር ራሱ ከድንግል የሚወለድን ልጅ፥ ለንጉሡ ምልክት እንደሚሰጠው ተናገረ። አገባቡ (በተለይም ቁ. 16-17) ትንቢቱ በዚያን ዘመን የተፈጸመ መሆኑን ያመለክታል። በዚህ መሠረት እንግዲህ ሕጻኑም በዚያ ዘመን ተወልዷል ማለት ነው። ነገር ግን ማቴዎስ ይህን ትንቢት ስለ ክርስቶስ የተነገረ አድርጎ ነው የሚያቀርበው። ይህ አንድ ግዙፍ ችግር ይፈጥራል (ማቴ. 1፡22-23)። በአካዝ ዘመን የወለደች ድንግላዊት በትክክል ነበረች? ይህ መፈጸሙን የሚያመለክት ማስረጃ የለም። ምናልባት ትንቢቱ በተነገረበት ጊዜ ድንግል የነበረች ወጣት ባል አግብታ በአጭር ጊዜ ውስጥ

ልጅ ወልዳ ይሆናል። "ድንግል" ተብሎ ስለተተረጎመው የዕብራይስጥ ቃልም አንዳንድ ጥያቄዎች አሉ። ስለ ማቴዎስ 1፡23 ግን ምንም ጥያቄ የለም። በምዕራፉ የተጠቀሰው ቃል በአገባቡ መሠረት ስለ አንድ ድንግላዊት መግለጡን ያረጋግጣል። ይህ ትንቢት አስቸጋሪ በመሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች በትርጓሜው አይስማሙም። ይሁን እንጂ ስለ ክርስቶስ የሚጠቀሰው ማስረጃና መንታዎቹ ክንውኖች ግልጥ ናቸው።

3. *ዘይቤያዊ ቋንቋ።* ትንቢቶች፥ ቀደም ሲል የተመለከትናቸውን የመሳሰሉ አያሌ ዘይቤያዊ አነጋገሮች፥ ተምሳሌቶች. . .ወዘተ. እና ቀጥታ ወይም ቃል በቃል ገለጣዎች አሏቸው። የትርጓሜ ችግር እያንዳንዱን ዘይቤ መፍታቱ ሳይሆን፥ ትንቢቱ የተፈጸመው በቀጥታ፥ በተዘዋዋሪ ወይም በመንፈሳዊ ሁኔታ መሆኑን መረዳቱ ላይ ነው። ይህን ጥያቄ የምንመለከትበት ሁኔታ፥ የተፈጸመ ትንቢት ያልተፈጸመውን ለመፍታት እንደ ቁልፍ ያገለግላል በሚለው አሳብ ላይ የተመሠረተ ይሆናል። አዲስ ኪዳን የብሉይ ኪዳን ትንቢቶችን እንዴት እንደሚፈታቸው መመልከት አለብን። ቀጥሎ ካሉት ብዙዎቹን ልብ ማለቱ መልካም ይሆናል፡-

ሀ. *የሚከተሉት ትንቢቶች፥ በአዲስ ኪዳን መሠረት፥ በቀጥታ አልተፈጸሙም?*

ሚክያስ 5፡2 እና ማቴዎስ 2፡6፡- ቤተልሔም፥ የክርስቶስ የትውልድ መንደር።

ዘካርያስ 9፡9 እና ማቴዎስ 21፡5፡- የክርስቶስ በአህያ ውርንጫ ተቀምጦ እንደ ንጉሥ ኢየሩሳሌም መግባት።

ኢሳይያስ 56፡7 እና ማቴዎስ 21፡13፡- የእግዚአብሔር ቤት፥ ቤተ መቅደስ፥ የጸሎት ቤት።

ኢሳይያስ 7፡14 እና ማቴዎስ 1፡22-23፡- የድንግል ልጅ መውለድ።

መዝሙር 22፡18 እና ዮሐንስ 19፡23-24፡- ወታደሮች ዕጣ ተጣጥለው የክርስቶስን ልብስ መከፋፈላቸው።

ለ. *የሚከተሉት ትንቢቶች በዘይቤያዊ መንገድ አልተፈጸሙም?*

መዝሙር 118፡22 እና የሐዋርያት ሥራ 4፡11፤ 1ኛ ጴጥሮስ 2፡7፡- ክርስቶስ፥ ግንበኞች የናቁት የማዕዘን ድንጋይ።

ኢሳይያስ 22፡22 እና ራእይ 3፡7፡- በጫንቃው ላይ ያለው መክፈቻ የንጉሥነት ሥልጣኑን ያመለክታል።

ዘካርያስ 13፡7 እና ማቴዎስ 26፡31 ደግሞ ክርስቶስ የተመታ ወይም የቆሰለ እረኛ መሆኑን ይገልጣል።

ሐ. *የብሉይ ኪዳን ቀጥተኛ እውነት የአዲስ ኪዳንን መንፈሳዊ እውነት አስቀድሞ በመግለጡ የሚከተሉት ትንቢቶች በመንፈሳዊ መንገድ አልተፈጸሙም?*

ኤርምያስ 31፡31-34 እና ዕብራውያን 8፡8-12፤ 10፡15-17፡- ከእስራኤል ጋር የተገባው አዲስ ኪዳን እንዲሁም የአሕዛብ አማኞች አሁን ያሉበት መንፈሳዊ ሕይወት ወይም ልምምድ።

ኢሳይያስ 2፡2-3 እና ዕብራውያን 12፡22፡- ምድራዊቱ ጽዮንና ኢየሩሳሌም፥ ስለ አማኞች መንፈሳዊ መኖሪያ ይናገራሉ።

አሞጽ 9፡11-12 እና የሐዋርያት ሥራ 15፡16-17፡- የዳዊትና የኤዶም ድንኳን እድሳት አሁን በመንፈሳዊ ሁኔታ ተከናውኗል።

አዲስ ኪዳን ትንቢቶችን በነዚህ ሦስት መንገዶች የሚፈታ ከሆነ፥ እኛም ሌሎችን ትንቢቶች ከሦስቱ በአንደኛው መንገድ ልንፈታ መቻላችን ግልጥ ይመስላል። ይህ ትክክለኛው ትርጓሜ ወይም አፈታት ምን እንደሆነ በቀላሉ ወይም በፍጥነት እንድናውቅ ባይረዳንም፥ ሊሆኑ የሚችሉትን ነገሮች እንድናውቅ ያግዘናል። ትንቢቶች ሁሉ በአንድ መንገድ የማይፈቱ መሆናቸውን እግዚአብሔር ያሳየናል። እናም አዲስ ኪዳን ትንቢቶችን እንዴት እንደሚያያቸው ባጠናን መጠን፥ ትንቢቶችን ሁሉ የመረዳት ጥልቅ እውቀት እናገኛለን። ይህን የሚመለከቱ አንዳንድ መመሪያ ነጥቦችን በኋላ እንመለከታቸዋለን።

4. *ልዩ ሰዋስው።* በመሠረቱ ትንቢቶች ሁሉ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በሚጠቀሙበት የሰዋስው ዓይነት ስለሚጠቀሙ፥ ለዚህ የትንቢት ባሕርይ ይህ ስያሜ ተስማሚ መጠሪያ አይሆን ይሆናል። ይሁንና አንዳንድ ጊዜ ትንቢት በሰዋስው ሥርዓት መሠረት የሚገለጡ ጊዜያትን የሚጠቀምባቸው መንገዶች አሉት።

ሀ. *ኃላፊ ጊዜን የሚገልጡ ግሦች የወደፊቱን በማመልከት ያገለግሉ ይሆናል።* በኢሳይያስ 53 ለክርስቶስ የተነገረው ታላቅ ትንቢት የወደፊቱን የሚናገር ቢሆንም፥ ከምዕራፉ መጀመሪያ እስከ ቁጥር 10 አጋማሽ ድረስ የተገለጠው በኃላፊ ጊዜ ነው። ከቁጥር 10 የመጨረሻ ክፍል እስከ ቁጥር 12 ድረስ ያሉት ሁኔታዎች (ከክርስቶስ መሠቃየት በኋላ የሚከተለውን ነገር ምንነት የሚናገሩት) ከሚቀድማቸው ክፍል ይልቅ ትንቢቱ ለተነገረበት ጊዜ የወደፊት ድርጊቶች ባይሆኑም፥ የተገለጡት በትንቢትነት ነው።

ለ. *ልክ እንደ አማርኛ፥ በዕብራይስጥ ቋንቋ የአሁን ጊዜ ድርጊትን በሚያመለክተውና የወደፊት ድርጊትን በሚያመለክተው ግሥ*

መካከል ልዩነት የለም። ለምሳሌ በዘካርያስ 9፥9 ላይ "ንጉሥሽ ይመጣል" የሚል አለ። ይህም "ንጉሥሽ አሁኑኑ ይመጣል"፥ ወይም "ንጉሥሽ ወደፊት ይመጣል" በሚል ሊተረጎም ይችላል። ይህ ዓረፍተ ነገር በትንቢት መጽሐፍ የሚገኝ በመሆኑ፥ ጉዳዩ የሚያመለክተው ነቢዩ ዘካርያስ "ወደፊት ይሆናል" ብሎ የተነበየውን ነው እንላለን።

5. *ቅድመ ሁኔታዊ የሆኑና ያልሆኑ ትንቢቶች።* ብዙ ትንቢቶች ቅድመ ሁኔታዊ እንዳለመሆናቸው መጠን ማለት እግዚአብሔር ከሌሎች ሁኔታዎች ውጪ የሚያደርገውን ወይም ሊሆን ያለውን ነገር ይገልጣል። የሌሎቹ ብዙ ትንቢቶች መፈጸም ግን በሕዝቡ ታዛዥነት የሚወሰን ይሆናል። ቅድመ ሁኔታዊ ትንቢቶች በተለምዶ አጠቃላይ ሲሆኑ፥ አንድን የተወሰነ ድርጊት ከመግለጥ ይልቅ የፍርድ ወይም የበረከት ሊሆኑ ይችላሉ። ይሁን እንጂ እውነተኛ ትንቢቶች ናቸው፤ መጽሐፍ ቅዱስም የብዙዎቹን ፍጻሜ ይመዘግባል። አንዳንዶቹ ክፍሎችም:- ዘዳግም 28፤ ኤርምያስ 18፥8፥ 10፤ 26፥12-13፤ ሕዝቅኤል 18፥30-32፤ 33፥13-15፤ ዮሐንስ 3፥4 (ይህ በአገባቡ መሠረት ግልጥ ሊሆን ይችላል)። በትንቢቱ ውስጥ ቅድመ ሁኔታ ካለ በአገባቡም ውስጥ ይኖራልና የትንቢቶች ሁሉ አገባብ ጠቃሚ ነው።

6. *እውነትን መግለጥና መደበቅ፤ አንዳንድ ሰዎች ትንቢት ከጊዜው አስቀድሞ የተጻፈ ታሪክ እንደሆነ አድርገው ያስባሉ።* ትንቢቶች አንዳንድ ጊዜ ድንቅ የሆኑ ዝርዝር ጉዳዮችን የሚያመለክቱ ናቸው። ከዚህም የተነሣ ሰዎች ትንቢት እውነቶችን ሁሉ ለመግለጥ የሚቀርብ ወይም የታለመ ነው በማለት ይደመድማሉ። ነገር ግን ብዙ ትንቢቶች እውነትን ይደብቃሉ፤ ይገልጡትማል። ጥሩው ገላጭ ምሳሌ ስለ አራቱ አውሬዎች ዳንኤል ያየው ራእይ ነው (ዳን. 7)። በ7፥15-16 ላይ ዳንኤል ባየው ነገር ተቸግሮ፥ ስለ ትርጓሜው በዚያ ከቆሙት አንዱን እንደጠየቀ ይናገራል። በዚህም አያበቃ፤ ተጠያቂው ራእዩን እንደተረጎመለትም ይናገራል። በትርጓሜውም አራቱ ታላላቅ አውሬዎች፥ አራት ነገሥታት ወይም መንግሥታትን እንደሚወክሉ ተነገረው። ሆኖም የመንግሥታቱ ስም ወይም አንዳንድ ዝርዝር ጉዳዮች አልተነገሩትም። ስለሆነም ነገሥታቱ እነማን እንደሚሆኑ በቅድሚያ ማወቁ የማይቻለው ይሆን ነበር። በሕልሙ ወይም በራእዩ እውነት ተገልጧል፤ ደግሞም ተደብቋል። ስለዚህ ያልተፈጸሙት ትንቢቶችን በእርግጠኝነት ለመፍታት እንደምንችል በምናስብበት ጊዜ ጥንቃቄ ማድረግን ልንለማመድ ይገባል።

## ቁልፍ ትንቢት

ከላይ የተጠቀሱትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢቶች ባሕርያት ወይም መለያዎች ማስታወስ ይጠቅመናል። የምናጠናቸውን ትንቢቶች ለመፍቻ አንዳንድ መመሪያ ነጥቦች ይሆኑናል።

ከብሉይ ኪዳን እጅግ ጠቃሚ ትንቢቶች አንዱ ለሆነው እናው ላቸው ዘንድም ይረዳናል። ይኸውም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ክርስቶስ የተጠቀሰው የመጀመሪያ ቀጥተኛ ትንቢት ዘፍጥረት 3፡15 መሆኑን ነው። ይህ ክፍል ወይም ትንቢት፥ የተመለከትናቸውን ብዙ መለያዎች የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የምናገኛቸውን አበይት የትንቢት ማዕከላዊ ጭብጦች ያጠቃልላል።

1. *ትንቢታዊ እይታ።* በሴቲቱ ዘር ሰኮና (“ተረከዝ”፥ በ1980 ዓ.ም. እትም) መቀጥቀጥና በእባቡ ጭንቅላት መቀጥቀጥ ምን የወደፊት ሁኔታዎች ተተንብየዋል? እነዚህ በአንድ ላይ ቢጠቀሱም፥ የኢየሱስ መሠቃየትና ድል፥ ሁለቱን ምጽአቶቹን ጨምሮ ክንዋኔዎች ናቸው።

2. *የቅርብና የሩቅ ፍጻሜ።* እግዚአብሔር በሴቲቱና በእባቡ መካከል ያደረገው ጠላትነት በሔዋን አማካይነት የቅርብ ፍጻሜ አግኝቷል። የሩቁ ፍጻሜ በክርስቶስና በሰይጣን መካከል ያለው ጠላትነት ነበር።

3. *ዘይቤያዊ ቋንቋ።* ጭንቅላትና ሰኮና መቀጥቀጥ የሚለው ገለጣ፥ ቀጥተኛ ወይም የቃል በቃል ትርጉም ሊሆኑ አይችሉም፤ ከአካል ጉዳት ባሻገር የተሟላ መንፈሳዊ ትርጓሜ አላቸው።

4. *እውነትን መግለጥና መደበቅ።* የእውነቱ ጥቂት ክፍል ተገልጧል። የትንቢቱን ሙሉ ትርጉም ለመረዳት የሚቻለው ግን በኋለኞቹ ትንቢቶችና ሁነቶች ላይ በሚፈነጥቀው ብርሃን ብቻ ነው።

5. *የግጭቱ ጭብጥ ወይም ፍሬ ነገር።* የመጽሐፍ ቅዱስ ጠቅላላ ክፍል ይህን ግጭት የሚመለከት ነው። ቅራኔውም በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል እንዲሁም በእግዚአብሔር ሰዎችና በዲያብሎስ ጭፍራዎች መካከል ነው። ክርስቶስ የሴቲቱ ዘር በመሆን፥ ግጭቱን ድል ይነሳ ዘንድ ታሪክ ውስጥ ገባ።

6. *የእግዚአብሔር ክብር ዓላማ መልእክት ወይም ፍሬ ነገር።* “እኖራለሁ” ይላል እግዚአብሔር። አንዳንድ ጊዜ ሰይጣን ከፍ ያለ ቢመስልም፥ በመላው መጽሐፍ ቅዱስ የሚታየው የእግዚአብሔር ዓላማ ክንውን ነው። የራእይ መጽሐፍ የዚህን ዓላማ የመጨረሻ ክንውን ያሳያል።

7. *የመሢሑ ጭብጥ።* የ‘ሴቲቱ ዘር’ እና “እርሱ” የሚለው ተውላጠ ስም አንድ ሰውን ያመለክታል።

8. *የሙሺሑ መሠቃየት መልእክት ጭብጥ።* "አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ።" ይህ ዓይነቱ ቁስል ለሞት የሚያደርስ አይደለም፤ ግን ሥቃይን ያመለክታል።

9. *የሙሺሑ ድል መልእክት ወይም ይዘት።* "እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፥" የሚለው ቃል መሢሑ እባቡን ወይም ሰይጣንን ክፉኛ የሚያቆስለው መሆኑን ይገልጣል። ቃሉ ወይም ምስሉ፥ የተረከዝና የጭንቅላትን መቀጥቀጥ ነው በንጽጽር የሚያቀርበው።

የመጨረሻዎቹ ሁሉት ጭብጦች፥ የትንቢት ማዕከላዊ ጭብጦች ወይም መልእክቶች ናቸው። ጴጥሮስ የነቢያትን መልእክት፥ "ስለ ክርስቶስ መከራ ከእርሱም በኋላ ስለሚመጣው ክብር" በማለት ያጠቃልለዋል (1ኛ ጴጥ. 1፡11)። ሁለቱ ደቀ መዛሙርት "ክርስቶስ ይህን መከራ ይቀበል ዘንድና ወደ ክብሩ ይገባ ዘንድ ይገባው የለምን?" (ሉቃስ 24፡25-26) በማለት ነቢያት ስለ እርሱ የጻፉትን ባለማመናቸው ጌታ ነቅፏቸዋል። የክርስቶስ መከራና ክብር የብሉይ ኪዳን ትንቢት ሁለት የትኩረት ነጥቦች ናቸው። ሌሎች ነጥቦችና መልእክቶች በሙሉ ትርጉ ማቸውን የሚያገኙት ከነዚህ በሚዛመድ አኳኋን ነው።

## የትርጓሜ መመሪያ ነጥቦች

የትንቢትን የትርጓሜ ነጥቦች ብናጠቃልላቸው ይረዳናል።

1. *አዲስ ኪዳን ትንቢትን የሚገልጥበትን ወይም የሚያቀርብበትን ሁኔታ ያጥኑ።* ይህን ማድረግ ያለብዎ አንድን የትንቢት ክፍል (ምንባብ) ለመፍታት ሲሞክሩ ብቻ ሳይሆን፥ በመደበኛው የአዲስ ኪዳን ጥናትዎ ጊዜም ነው። ምንባቦቹንና በጥናትዎ ጊዜ የተማሩትን መመዝገቢያ ማስታወሻ ደብተር ይኑርዎ።

2. *ከእያንዳንዱ ትንቢት፥ በመጀመሪያ ትንቢቱ በተነገረበት ዘመን ለነበሩ ሰዎች የነበረውን መልእክት ወይም ትርጉም፥ እንዲሁም የቅርብ ፍጻሜውንና፥ ፍሬ መልእክቱን ለመረዳት ይጣሩ።* ክንዋኔውን ለማግኘት ከመሞከር በፊት ይህን መማሩ ጠቃሚ ነው። ለምሳሌ የሐጌ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን ቤት ስለመሥራት የሚለው ነገር አለ። ያ ምን ማለት ሊሆን ይችላል? ዕዝራ 4፡24-5፡2 መነሻውን በመስጠት፥ የሐጌን ንግግር ዓላማ ያሳያል። የእግዚአብሔርን ቤት መሥራትን አስመልክቶ የሚያቀርበው ማሳሰቢያ፥ እግዚአብሔር ወደፊት በሰማይና በምድር መለኮታዊ ኃይሉን ለማሳየትና ሕዝቡንም ለመባረክ ምን እንደሚያደርግ ከተነበየው ጋር የተያያዘ ነው። የሩቁን ፍጻሜ ዕብራውያን 12፡26-29 ግልጥ ያደርገዋል።

3. *ቀጥተኛ ወይም የቃል በቃል ትርጉሙን ልብ ይበሉ።* ከአገባቡ ወይም ከሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንጻር ትርጉሙ ግልጥ ነው? ኢሳይያስ 11፡6-9 የወደፊቱን ውብ ሕብራዊ ሥዕል ይሰጣል። የዱር አራዊት ከለማዳ እንስሳትና ከሕጻናት ጋር ሊኖሩ የሚያስችላቸው አንዳች ሁኔታ አለ? ቀጥተኛ ፍጻሜስ ሊኖረው ይችላል? የዘይቤያዊ አነጋገር ምልክቶችን ምንባቡ ውስጥ ያስተውላሉ? (ቁ. 1ን እንዲሁም 4 እና 5ትን ይመልከቱ።) በእነዚያ ጥቅሶች ወይም ቁጥሮች ውስጥ ያለው ቋንቋ ከቁጥር 6-9 ላሉት ጥቅሶች ዘይቤያዊ ትርጉም ይኖረዋል?

4. *የተመለከትናቸውንም የትንቢት መለያ ባሕርያት ልብ ይበሏቸው።* በምንባቡ ሊገኙ የሚችሉትን ማናቸውንም ትንቢቶች ለመገንዘብ ይጣሩ። ካገኟቸው መሆን በሚገባው መንገድ ይተርጉሟቸው። ለምሳሌ በዮሐንስ 5፡28-29 ያለው ትንቢት ስለ ሙታን ትንሣኤ የሚናገር ነው፥ ወይስ ሁለት ትንሣኤዎችን ይተነብያል? ቋንቋውን ከሁለቱ በአንዱ መንገድ ለመረዳት ይቻላል። አንዳንዴ በጊዜ የተለያዩ ሁነቶች ከትንቢት አቅጣጫ በሌላ ትንቢት ሊገናኙ መቻላቸውን በማስታወስ፤ እነዚህ ሁለት ትንሣኤዎች በጊዜ ሊለያዩ የሚችሉ መሆኑን (መለያየት "አለባቸው" ሳይሆን ይለያዩ "ይሆናል") ይገነዘባሉ። መሆን ወይም ያለመሆናቸውን ለማረጋገጥ ሌሎች ምንባቦችን ማጥናት ይገባዎታል።

5. *በምንባቦቹ ውስጥ ዘይቤያዊ አነጋገሮችን፥ አምሳያዎችን፥ ፈሊጣዊ አነጋገሮችን. . . ወዘተ. ይፈልጉ።* ካገኟቸው፥ ስለነሱ በተሰጡት መመሪያዎች አማካይነት ለመተርጎም ይሞክሩ። አንዳንድ ዘይቤያዊ አነጋገሮች ልንለያቸው በማይቻለን አኳኋን ከተራው ቋንቋ ጋር ይመሳሰላሉና በጥንቃቄ ይመልከቷቸው።

ትንቢት ቀላል ጉዳይ አይደለም። ነገር ግን እግዚአብሔር የተባረከ እውነቱን ሊያስተምረን ከመረጣቸው መንገዶች አንዱ ነው። ለዚህ ጠቃሚ የሆነ የእግዚአብሔር መገለጥ ከፍተኛ የጥናትና የጸሎት ጊዜ መስጠቱ ተገቢ ይሆናል።

# 20

# ትምህርተ-ሃይማኖት

ትምህርተ-ሃይማኖት የሚለው ቃል በሁለት መንገዶች አገልግሎት ላይ ውሏል፡- (1) እውነትን በአጠቃላይና አሠራሩን፥ ማለት ሥርዓቱን ለማመልከት፥ (2) የተወሰነ ወይም የተለየ እውነትን ለማመልከት። በመጀመሪያው አሳብ መሠረት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የእግዚአብሔር አጠቃላይ ትምህርት ነው። በሁለተኛው አሳብ መሠረት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የእግዚአብሔር እውነት አንዱ ክፍል ነው፡- እንደ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት። የሁለቱም አሳቦች መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ስለዚህ ትክክለኛውን ትምህርተ-ሃይማኖት በሥርዓት ለመግለጥ ይቻለን ዘንድ፥ የመጽሐፍ ቅዱስን ትርጉም መረዳት ይኖርብናል። ይህ እንደገና ጥልቅ የሆነን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና የትርጓሜን ትክክለኛ ጠቀሜታ አጉልቶ ያመለክታል።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደተወሰነ የመማሪያ መጽሐፍ ትምህርቶቹን ነጣጥሎ አያቀርባቸውም። የዚህ አንዱ ምክንያት፥ ትምህርተ-ሃይማኖት ስለ ራሱ ሲባል ብቻ የሚማሩት አንድ የእውቀት ዘርፍ አለመሆኑ ነው። ይልቁንም፥ መጽሐፍ ቅዱስ የምንኖርበት እውነት ነው። ስለ እግዚአብሔር የምንማረው ከእርሱ ጋር በሕብረትና ለፈቃዱም በመታዘዝ ለመኖር ይቻለን ዘንድ ነው። ጳውሎስ "የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ለትምህርት... ይጠቅማል" (2ኛ ጢሞ. 3፡16) ይላል። እግዚአብሔር ቅዱስ ቃሉን የሰጠን፥ እርሱ እንደሚፈልገን ለመሆን ይቻለን ዘንድ ነው።

ይህን ነጥብ በ1ኛ ዮሐንስ 3፡2-3፥ "...እርሱን እንድንመስል እናውቃለን። በእርሱም ይህን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ንጹሕ እንደሆነ ራሱን ያነጻል" በሚለው ቃል ውስጥ ልናይ እንችላለን። ስለ ዳግም ምጽአቱ ያለን እምነት ወደ ሕይወት ንጽሕና ማምራት አለበት። (እንደ ኢሳይያስ 40፡27-31 እና ፊልጵስዩስ 2፡5-8 ያሉ ታላላቅ የትምህርተ-ሃይማኖት ክፍሎችንም ይመልከቱ።)

ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን እውነት በሕይወት ሁኔታዎች መሠረት ያቀርባል። ትምህርተ-ሃይማኖትን ከአብርሃም ሕይወት፥ ከዳዊት ትግሎችና፥ ነቢያት ለእስራኤል ካቀረቧቸው ምልጃዎች እንማራለን። የአዲስ ኪዳን ትምህርተ-ሃይማኖታዊ መልእክቶችም ሰዎች እንደ ክርስቲያኖች እንዲኖሩ ለመርዳት የተጻፉ ደብዳቤዎች ናቸው። በመሆኑም በብዙ ስፍራዎች ከተሰጡት ትምህርቶች አንድ እውነታ

ለማግኘት እንጠብቃለን ወይም ተስፋ እናደርጋለን። ስለ እግዚአብሔር የሚያስተምረንን ትምህርተ-ሃይማኖት በተመለከተ በመቶዎች፥ ምናልባትም ከዚያ በላይ በሺሆች የሚቆጠሩ ጥቅሶች ይገኛሉ።

## ትምህርተ-ሃይማኖትን የምንረዳበት መንገድ

የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርተ-ሃይማኖት የምንረዳበትን መንገድ ወይም ዘዴ በግልጥ መለየት መልካም ነው። መነሻ የእምነት ነጥቦች ምንድናቸው?

1. *መጽሐፍ ቅዱስ፥ እግዚአብሔር እናውቀው ዘንድ የሚፈልገውን ትምህርተ-ሃይማኖት ይሰጠናል።* ይህንንም 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡16-17 ግልጥ ያደርገዋል። የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርት ይጠቅማል።

2. *መጽሐፍ ቅዱስ የትምህርተ-ሃይማኖት በቂ ምንጭ ነው።* እኛ ልናውቀው የሚገባንን ትምህርት በሙሉ እግዚአብሔር በዚህ ብቸኛ መጽሐፉ ሰጥቶናል። ከመጽሐፍ ቅዱስ ሌላ ሥልጣን ያለው ምንጭ የለም። የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ወይም ደንብ፥ እውቀታችን፥ ከስሜት የምናገኘው መረዳት፥ ባጠቃላይ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ የሆነ ምንም ነገር የእግዚአብሔርን እውነት ለማስተማር በቂ አይደለም።

3. *መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ወጥ የሆነ ትምህርተ-ሃይማኖት ይሰጣል።* በአዲስ ኪዳን ያለው ትምህርት በብሉይ ኪዳን ካለው አይቃረንም። ጳውሎስ የኢየሱስን ትምህርት፥ ወይም ያዕቆብ የጳውሎስን ትምህርት አይቃረንም። መጽሐፍ ቅዱስ ግልጥና አንድ ወጥ የሆነ የእግዚአብሔር እውነት መገለጥ ነው።

ሆኖም ግን በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ የተለየ ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች ሊኖሩ ይችላሉ። ኤርምያስ እግዚአብሔር በሕዝቡ ኃጢአት ምክንያት በሚሰጠው ፍርድ ላይ ሲያተኩር፥ ሆሴዕ ይበልጥ የሚናገረው ስለ እግዚአብሔር ምሕረት ነው። ነገር ግን ለምሳሌ ብሉይ ኪዳን ስለ እግዚአብሔር ቁጣ፥ አዲስ ኪዳን ደግሞ ስለ ፍቅሩ ያስተምራል ለማለት አንችልም። ሁለቱም ኪዳናት የእግዚአብሔርን ፍቅርና ቁጣ ነው የሚያስተምሩት።

አሁንም ቢሆን የእግዚአብሔር እውነት መገለጥ እያደገ ነው የሚሄደው። ይኸውም የመጀመሪያዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የእምነትን ሙሉነት አያቀርቡም ማለት ነው። እግዚአብሔር ስለ ራሱና ስለ መንገዶቹ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየገለጠ ሄደ። አዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር መገለጥ ማሳረጊያና ፍጻሜ በመሆኑ ከብሉይ ኪዳን ይለያል። (ይህን አሳብ በዚሁ መጽሐፍ ምዕራፍ 21 ውስጥ በሰፊው እንመለከታለን።)

4. *ትምህርተ-ሃይማኖትን ማጥናት የሚኖርብን አንድን የተለየ ጉዳይ የሚነኩ ምንባቦችን በሙሉ በማጥናት ነው።* ጥያቄያችን "መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?" የሚል እንደመሆኑ መልሱን ለማግኘት መላውን መጽሐፍ ቅዱስ እናጠናለን። መጽሐፍ ቅዱስ ከግል አሳባችን እንዲስማማ አናደርግም፥ ወይም የግል አሳባችንን ወደርሱ አናመጣም። ትምህርተ-ሃይማኖታችንንም በአንድ ወይም በሁለት ምንባቦች ላይ አንመሠርትም። ይህ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ይበልጥ የምንነጋገርበት ታላቅ ጉዳይ ነው።

5. *ስለ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ለመረዳት እንችላለን ብለን አናስብም።* እኛ ፍጡሮች፥ እርሱ ደግሞ ወሰን የሌለውና ኃያል ፈጣሪ ነው። ከዚህም የተነሣ ስለርሱ ያለውን እውነት ሁሉ መገንዘቡ አይቻለንም። ቢሆንም ከባድና ልንገነዘባቸው የማይቻሉንን ጥያቄዎች መልስ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምናገኝ እናምናለን፤ በተረዳነው መጠን ለመኖር እየጣርንም ከመረዳታችን በላይ ለሆነው ነገር በእግዚአብሔር እንታመናለን።

6. *መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጻራሪ የሚመስሉ እውነቶችን እንደምናገኝ እናውቃለን።* እነዚህ እውነቶች በአንዳንድ ሁኔታዎች ተቃራኒዎች ቢመስሉም፥ ሁለቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በትምህርትነት ይሰጣሉ። በመሰለን መንገድ ሁለቱን ለማጣመር ወይም ለማስማማት አንችልም። ለምሳሌ ክርስቶስ አምላክም ሰውም መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል። ሰው እንጂ እግዚአብሔር ውሱን አይደለም። ታዲያ እንዴት ነው ክርስቶስ በአንድ ጊዜ ውሱንና የማይወሰን ሊሆን የሚችለው? እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ግን እርሱ ሁለቱንም ነው። በዚህ ረገድ የሚነሡትን ችግሮች ሁሉ ጠቢባን ሊያቃልሏቸው አይችሉም። ነገር ግን እነርሱም ሆኑ እኛ፥ የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት ተቀብለን ሁለቱንም እውነቶች እንደ ክርስቶስ ትምህርተ-ሃይማኖት ክፍሎች ልንይዛቸው ይገባል።

7. *ትምህርተ-ሃይማኖት ቅድስናን ያስከትላል።* ትምህርተ-ሃይማኖቶችን ባጠናን መጠን የእግዚአብሔርን መልእክት ለመረዳትና ለመታዘዝም እንሻለን።

## የትርጓሜ መመሪያ ነጥቦች

ትምህርተ-ሃይማኖትን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን እንዴት ለመማር እንደምንችል እንመልከት።

1. *ትምህርተ-ሃይማኖትን ከዘይቤያዊ ክፍሎች ይልቅ፥ በቀጥታ ወይም ቃል በቃል አባባሎች ላይ ይመሥርቱ።* ዘይቤያዊ ምንባቦች ወይም ክፍሎች (እንደ ምሳሌ ያሉት) የተጠቀሱት አንድ ዋና ትምህርት

ለማስተማር ነው። የታሪኩ አካል በሆኑት ክፍሎች ዝርዝር ውስጥ ዓላማቸው ማስተማር ያልሆነ ትምህርተ-ሃይማኖቶችን በቀላሉ እናገኝ ይሆናል። "ሥዕል"ን መተርጎም ግልጥ አባባልን ከመፍታት ይልቅ ችግር አለበት።

ለምሳሌ የአባካኙን ልጅ ታሪክ ይመልከቱ (ሉቃስ 15)። አንዳንድ ለዘብተኛ የሃይማኖት ምሁራን ይህን ታሪክ አንድ ኃጢአተኛ ወደ እግዚአብሔር የሚመለስበትን መንገድ ማስተማሪያ እንደሆነ አድርገው ይወስዱታል። በታሪኩ ውስጥ ምንም ለሥርየት ሲባል የተከናወነ ሞት ስለሌለበት፥ እግዚአብሔር የኃጢአተኛውን መናዘዝ ወይም ንስሐ መግባት ብቻ የሚፈልግ አፍቃሪ አባት ነው ብለው ይደመድማሉ። ክርስቶስ ስለ ኃጢአት ቅጣት መሠቃየቱ አያስፈልግም ማለታቸው ነው።

ወይም የወይኑን ግንድና የቅርንጫፎቹን ተምሳሌት ይመልከቱ (ዮሐ. 15)። በዚህ ምሳሌ እንደተገለጠው አንዳንድ ቅርንጫፎች ተቃጥለዋል። እነዚህ ማለት፥ የተቃጠሉት ቅርንጫፎች እውነተኛ አማኞችን ይወክላሉ? እውነተኛ አማኞች በመጨረሻ ይቃጠላሉ? ከሆነስ፥ በምን ሁኔታ? ለነዚህ ጥያቄዎች የሚሆኑ መልሶች ከቀጥታ ንግግሮች (ጥያቄያዊ ያልሆኑ) መገኘት አለባቸው፤ ያኔ ይሆናል ይህ ምንባብ እውነትን የሚያስረዳው። እንዲህ ካለው ምንባብ ትምህርተ-ሃይማኖት መፍጠር ተገቢ አይደለም።

2. *ትምህርተ-ሃይማኖትን ከአደናጋሪ ገለጣዎች ይልቅ ግልጥ በሆኑት ላይ ይመሥርቱ።* መጽሐፍ ቅዱስ ግልጥ ያልሆኑ ምንባቦች ወይም ክፍሎች አሉት። አንዳንዶቹ ለአንደኛው ተማሪ ግልጥ ሲመስሉ፥ ለሌላው ደግሞ ከባድ ይመስሉ ይሆናል። ሆኖም አንዳንድ ምንባቦች በተማሪዎች ሁሉ ዘንድ በአስቸጋሪ ወይም በከባድነት የታወቁ ስለሆኑ፥ ትምህርተ-ሃይማኖትን በነዚህ ምንባቦች ላይ አለመመሥረት ብልኅነት ነው።

ለምሳሌ ጴጥሮስ፥ ኢየሱስ "ሄዶ በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው" ይላል (1ኛ ጴጥ. 3፡19)። በዚህ አስቸጋሪ ወይም ከባድ ጥቅስ ትርጉም ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን አይስማሙም። በመሆኑም ከዚህ ጥቅስ በመነሣት ኃጢአተኛ ከሞተ በኋላ ሌላ የንስሐ ዕድል ይኖረዋል ብሎ መደምደም ስሕተት ይሆናል። ምንም ሁለተኛ ዕድል እንደሌለ ነው ቀጥታ ምንባቦች የሚያስረዱት።

3. *ትምህርተ-ሃይማኖትን ከታሪካዊዎቹ ምንባቦች ይልቅ ለትምህርት በሚሆኑት ክፍሎች ላይ ይመሥርቱ።* ብዙዎቹ የትንቢት መጻሕፍት፥ እንዲሁም የክርስቶስ ንግግሮችና መልእክቶች በሙሉ ትምህርታዊ ናቸው። በመሠረቱ፥ ትምህርታዊ ከሆኑት የመጽሐፍ ቅዱስ

ክፍሎች ትምህርት ይገኛል። ታሪካዊ ክፍሎችን፥ ሁነቶችን ወይም ድርጊቶችን ይመዘግባሉ፤ ስለሆነም ከነሱ ከሚገኘው ትምህርት ይበልጡ ቀጥተኛ ያልሆነና ተዘዋዋሪ ነው። እርግጥ አንዳንድ ጊዜ፥ በአንድ ሁኔታ እግዚአብሔር ወይም ከነቢያቱ አንዱ በቀጥታ ተናግረውታል። ቢሆንም ትምህርተ-ሃይማኖትን በቀላሉ በአንድ ሰው ድርጊት ተዘዋዋሪ ሁኔታዎች ብቻ ላይ መመሥረት የለብንም።

ለምሳሌ አንድ ጊዜ ማዕበል በተነሣ ወቅት ኢየሱስ በጀልባ ውስጥ ተኝቶ ሳለ ደቀ መዛሙርቱ ፈርተው ነበር (ማቴ. 8፡24)። ታዲያ ከዚህ ሁኔታ በመነሣት እግዚአብሔር ችግርን የማያውቅ ወይም ስለሚገጥመን ችግር የማይገደው ነው ብለን የምንደመድም ሞኞች መሆን አለብን? በማቴዎስ 25፡5 ላይ እንደምናየው አሥሩ ልጃገረዶች አንቀላፍተው ነበር። የዚህ ትርጓሜ ኢየሱስ ዳግም በሚመጣበት ጊዜ ሰው ሁሉ ይተኛል ማለት ነው? እንዲሁም በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ከተመዘገቡ ድርጊቶች ብቻ በመነሣት የመንፈስ ቅዱስን ትምህርተ-ሃይማኖት ከመመሥረት መጠንቀቅ አለብን። ከነዚህ ታሪኮች እንማራለን፤ ስለ ትምህርተ-ሃይማኖቱ እርግጠኛ ለመሆን ግን በመልእክቶች የተሰጠ የመንፈስ ቅዱስ ትምህርት ያስፈልጋል።

4. *ትምህርተ-ሃይማኖትን በጥቂቶቹ ላይ ብቻ ሳይሆን፥ በሁሉም ተዛማጅ ክፍሎች ላይ ይመሥርቱ።* የተወሰኑ ወይም ጥቂት ክፍሎችን በመመልከት ብቻ ትምህርተ-ሃይማኖትን መቀመርና ሌሎች ምንባቦች ከእነርሱ ጋር እንዲስማሙ አድርጎ ትርጓሜ ለመስጠት መሞከር ስሕተት ነው። ሌሎች ምንባቦች ሊታዩ የሚገባቸው ከመነሻቸው ጀምሮ ሊሆን ይገባል።

ለምሳሌ፥ "እርሱንም ኢየሱስን ከሚወጣው ቁጣ የሚያድነንን" (1ኛ ተሰ. 1፡10) የሚለውን እና "እግዚአብሔር ለቁጣ አልመረጠንምና" (1ኛ ተሰ. 5፡9) የሚሉትን ጥቅሶች አንድ ክርስቲያን ይመለከታል እንበል። ከነዚህ ጥቅሶች ብቻ በመነሣት እግዚአብሔር በመጨረሻው ጊዜ፥ ቤተ ክርስቲያን "ታላቁ መከራ" በሚለው ፍዳ ውስጥ እንድታልፍ አያደርጋትም ብሎ ይወስናል። እንደ ማቴዎስ 24፡29-51 ያሉትን ክፍሎች ሳይመለከት ይህን የሚወስን ከሆነ፥ ድርጊቱ መጽሐፍ ቅዱስን የመመርመሪያ ወይም ወደ ትክክለኛው ትምህርተ-ሃይማኖት መድረሻ ቀጥተኛ መንገድ አይሆንም።

እርግጥ ለአንዳንድ ትምህርተ-ሃይማኖቶች በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ምንባቦች መኖራቸው ነው ችግሩ። እነዚህን ከመጽሐፍ ቅዱስ በጥልቀት ማጥናት ይቅርና ማግኘቱ እንኳን ረጅም ጊዜ ይወስዳል። ስለሆነም ይህን ማድረጉ የማይቻልዎ ይሆን ይሆናል። ግን የእግዚአብሔርን እውነት

በመገንዘቡ ረገድ እጅግ የሚረዳዎ ስለሆነ፥ በዚህ መንገድ ቢያንስ አንዳንድ የትምህርተ-ሃይማኖት ጥናት ለማድረግ መሞከር ይኖርብዎታል።

ሰው ሁሉ እንዲህ ያለ ዝርዝር ጥናት ሊያደርግ እንደማይቻለው እንገነዘባለን። ስለሆነም ብዙዎች ትምህርተ-ሃይማኖትን ከመምህራን፥ ከመጻሕፍት፥ ከስብከት ወይም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መማር ይኖርባቸዋል። እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ያስቀመጣቸው አስተማሪዎችም ታላቅ አስተዋጽኦ ለማድረግ የሚችሉበት ዘርፍ ይህ ሊሆን ይችላል። ለዚህ አገልግሎት የሚያስፈልጉ ስጦታዎችን እግዚአብሔር ለአንዳንዶች ይሰጣቸዋል። እውነትን ለመማር፥ ጥርት ባለ አኳኋን ያቀናብሩና ከአማኞች ጋር ይወያዩበት። የትምህርተ-ሃይማኖትን እውቀት በሙሉ በግል ጥናትዎ ብቻ ለማግኘት ባለመቻልዎ ቅር አይሰኙ።

5. *አንዳንድ ትምህርተ-ሃይማኖቶችን ለመረዳት ይረዳዎ ዘንድ ቃላትን ያጥኑ።* በተለይም አንድ ትምህርተ-ሃይማኖት በአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል፥ ለምሳሌ "ሰንበት" እንደሚለው ባለ የተጠቃለለ ከሆነ ይህን ለመረዳት ይረዳዎት ዘንድ ቃላትን ያጥኑ። በማጣቀሻ መጻሕፍትም ይጠቀሙ። ቃላትን ያለ ማጣቀሻ መጽሐፍ ለማጥናት ይችሉ ይሆናል፥ ግን እጅግ ከባድ ነው። እናም እነዚህን ነጥቦች ያስታውሱ፦

ሀ. *አንድ ቃል የማይገኝላቸው ወይም በአንድ ቃል የማይገለጡ ትምህርተ-ሃይማኖቶች መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ።* በመሆኑም ስለነሱ ምንም የቃላት ጥናት ማድረግ አይቻልም፦ ለምሳሌ፥ "ሥላሴ" ለሚለው ቃል።

ለ. *ትምህርተ-ሃይማኖት የቀረበባቸው፥ ነገር ግን ቀጥተኛ ቃል የሌላቸው ምንባቦች ወይም ክፍሎች አሉ።* ትምህርቱን ስናጠና እንዲህ ያሉትን ክፍሎች ቸል አንላቸውም። ለምሳሌ፥ "መቀደስ" የሚለው ቃል በ1ኛ ተሰሎንቄ 4፥3 ሲገኝ፥ ትምህርቱ በ1ኛ ዮሐንስ 1 እና 3 ውስጥ በሚገባ ተገልጧል። ቃሉ ግን በነዚህ ምዕራፎች ውስጥ ጥቅም ላይ አልዋለም። ይሁን እንጂ እነዚያ ምንባቦች ለትምህርቱ ጠቃሚ ድጋፍ ናቸው።

ሐ. *አንዳንድ ትምህርተ-ሃይማኖቶች የሚገለጡባቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ቃላት አሏቸው።* እንዱን ቃል ብቻ በማጥናት ሌሎቹን ቸል አይበሏቸው። ለምሳሌ፥ "ቅድስና"፥ "ጽድቅነት"፥ "ንጽሕና" የሚሉት ቃላት ከአንድ ትምህርተ-ሃይማኖት ጋር የሚዛመዱ ናቸው።

6. *እያንዳንዱን ምንባብ በትርጓሜ አጠቃላይ መመሪያዎች አማካይነት የተረዱት ለመሆንዎ እርግጠኛ ይሁኑ።* ከመሠረታዊ የትርጉም

መመሪያዎች ውጪ መሆን በጭራሽ አንችልም። ለምሳሌ፥ ስለ "ቅድስና" ስናጠና በግሡ ውስጥ የተመለከተው ጊዜ* እንደ 1ኛ ዮሐንስ 3፡6፥ 9 ላሉ ጥቅሶች ጠቃሚ ነው።

7. *ትምህርተ-ሃይማኖትን በግምት በሚቀምሩበት ጊዜ ይጠንቀቁ።* ለምሳሌ፥ አንድ እውነት በመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ክፍል ውስጥ ተሰጠ እንበል። ያ እውነት ከሆነ፥ "አንድ ነገር" ከዚያ ይቀጥላል ብለን እንደመድማለን። ይህ "አንድ ነገር" ግምት ወይም "ይሆን ይሆናል" ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጥ ተቀምጦ አናገኘውም፤ ቢሆንም ትርጉሙን ከመጽሐፉ ካለው እውነት በመነሣት የምናገኘው ነው። የምናስተምር ከሆነም ግምትነቱን በማስታወስ ማስተማር ይኖርብናል።

ለምሳሌ፥ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች፥ እግዚአብሔር አንዳንድ ሰዎችን የመረጠበት ልዑላዊ ምርጫ የመጽሐፍ ቅዱስ ግልጥ ትምህርት እንደሆነ ይረዳሉ። ከዚህ በመነሣትም እግዚአብሔር ሌሎቹን ደግሞ ለፍርድ ወይም ለኩነኔ መርጧቸዋል ብለው ይገምታሉ። ይህ ግምት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን የሚልበት ስፍራ የለም። እንዲህ ያለው ግምት እውነት ይሆን ወይም አይሆን ይሆናል። ቢሆንም ግምት እንደሆነ አድርገን ልንመለከተው ይገባል።

8. *ከ'ይሆን ይሆናል' መንፈሳዊ ትምህርት ይጠንቀቁ።* ብዙ ጊዜ ቅዱስ ቃሉን ስናሰላስል፥ አእምሯችን ይሆናሉ የሚላቸውን አንዳንድ ነገሮች መገመት ስለሚጀምር ግምታዊ አስተያየት መስጠቱ ቀላል ነው። ለምሳሌ፥ በዘላለም ውስጥ አንዳንድ ሰዎችን እንደ ሕጻናት፥ ሌሎቹን ደግሞ እንደ አዋቂዎች እናስባቸው ይሆናል። ወደፊት በሌሎች ዓለማት (ፕላኔቶች) ላይ እንደምንኖርም እናስብ ይሆናል። ትክክል ይሁኑም አይሁኑ እነዚህ አሳቦች ከመጽሐፍ ቅዱስ የተገኙ ትምህርቶች ሳይሆኑ የ'ይሆን ይሆናል' ግምቶች ናቸው። ልንጠነቀቅባቸው ይገባል።

9. *ትምህርተ-ሃይማኖትን በሚቀምሩበት፥ በሚያከማቹበት ወይም በሚያስተምሩበት ጊዜ፥ ቅዱስ ቃሉ የሚያጎላውን ብቻ ያጉሉት።* እግዚአብሔር የገለጠው እውነት ሁሉ ጠቃሚ ነው፤ አንዳንድ እውነቶች ግን ከሌሎቹ ይበልጥ ጠቃሚዎች ናቸው። ክርስቶስ እንደገና ይመጣል የሚለው እውነት ቤተ ክርስቲያን "ታላቁ መከራ" ተብሎ በሚታወቀው ሥቃይ ወቅት በምድር ላይ ትኖራለች ወይም አትኖርም ከሚለው ጥያቄ ይልቅ ጠቃሚ ነው። ጳውሎስ በአገልግሎቱ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች በ1ኛ ቆሮንቶስ 1፡17 ላይ አመልክቷል፤ እንደዚሁ ሁሉ በትምህርተ-ሃይማኖትም ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች ሊኖሩ ይገባል። ስለዚህ

---

* በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ 9፥ ከገጽ 53-55 ያለውን ገለጣ ይመልከቱ።

ትምህርቱን ለመረዳት ብቻ ሳይሆን፥ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያጎላቸውን እውነቶችም ለመመልከት ይጣሩ።

10. *የትምህርተ-ሃይማኖቱን ተግባራዊ ጠቀሜታ ይፈልጉ።* መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቱ በተግባር የሚውልበትን መንገድ በግልጥ ያስቀምጣል። ምክንያቱም እግዚአብሔር እውነቱን የገለጠው በዚህ ምክንያት ነውና። ያን እውነት ለማግኘትና በሥራ ላይ ለማዋል የእግዚአብሔርን እገዛ መፈለግ የኛ ግዴታ ነው።

## ትምህርተ ሥላሴ

እነኝህን፥ ማለት ትምህርተ-ሃይማኖትንና የነዚህን ጥናቶች አንዳንድ ችግሮች መመልከቱ የመጽሐፍ ቅዱስን አንድ ጠቃሚ ትምህርት ለመገንዘብ ይረዳናል። ትምህርተ ሥላሴን በአጭሩ እንመለከታለን።

ይህ ትምህርተ-ሃይማኖትና "ሥላሴ" የሚለው ቃል ራሱ እንኳን ወደ ክርስትና እምነት የመጣው፥ ራሳቸውን ለመጽሐፍ ቅዱስ የሰጡ ተማሪዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን አንዳንድ የእውነት አቅጣጫዎች ባስተዋሉ ጊዜ ነው።

1. *አንድ አምላክ አለ፦* ዘዳግም 6፡4፤ 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡5 እና ሌሎችም ጥቅሶች።

2. *"አብ" የተሰኘ መለኮታዊ አካል አለ፤* እሱ እግዚአብሔር ነው፦ ሮሜ 1፡7፤ ኤፌሶን 4፡6፤ ፊልጵስዩስ 2፡11።

3. *እንዲሁም ሌላ መለኮታዊ አካል አለ፤* "ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ" እግዚአብሔር የሆነ፦ ዮሐንስ 5፡18፤ ዕብራውያን 1፡8፤ 2ኛ ጴጥሮስ 1፡1፤ 1ኛ ዮሐንስ 4፡15።

4. *ሌላ መለኮታዊ አካልም አለ፤* "መንፈስ ቅዱስ" ተብሎ የሚጠራና እግዚአብሔር የሆነ፦ የሐዋርያት ሥራ 5፡3-4።

5. *በነዚህ ሦስት መለኮታዊ አካላት መካከል ልዩነታቸውን የሚያሳዩ አካላዊ ሁኔታዎች አሉ፦*

ማቴዎስ 3፡16፦ የእግዚአብሔር (የአባቱ) ድምፅ በሰማያት እንደተሰማ፥ (መንፈስ ቅዱስን የሚወክለው) ርግብ፥ ኢየሱስ (ልጁ) ላይ አረፈበት።

ዮሐንስ 14፡26፦ አብ ሌላውን አጽናኝ ይልካል።

ዮሐንስ 15፡26፦ ኢየሱስ ምስክር የሆነውን አጽናኝ ይልካል።

ዮሐንስ 5፡20፦ አብ፥ ወልድን ይወዳል።

እነዚህ አምስት የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች እንዴት ይዋሃዳሉ ወይም ይጠቃለላሉ? ሦስቱ እግዚአብሔር ተብሏል፤ ግን አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው ያለው። አንዱ ከሌላው፥ የሚለያዩ እንደመሆናቸው፥ ሦስቱ የአንድ አካል ዓይነት አሠራር ወይም ቅርጽ ብቻ ሊሆኑ አይችሉም። ስለዚህ እውነቱ፥ በአንድ አምላክ ውስጥ ሦስት አካላት አሉ የሚለው መሆን አለበት። ‘‘አካል’’ የሚለው ቃል በትክክል ሊገልጣቸው አይችልም፤ ቢሆንም ልዩነቶቹ በአካል የሚገለጡ በመሆናቸው ‘‘አካል’’ የሚለው ቃል ለዚህ ጉዳይ የሚመረጥ ይመስላል። ከእግዚአብሔር ምንነት ጋር ስለተዛመደ ትምህርተ-ሃይማኖት በምንናገርበት ጊዜ፥ ቃላት ጉዳዩን የመግለጥ ብቃት የሌላቸው መሆኑን በቀላሉ እንረዳለን። የምንመለከተው የተገለጠና ሙሉ በሙሉ ልንረዳው የማይቻለንን እውነት ነው። ቢሆንም እንቀበለዋለን፤ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንም እውነተኛውን ትምህርተ-ሃይማኖት ለዘመናት ተቀብላዋለች። እንደ ማቴዎስ 28፡19፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 13፡14፤ ራእይ 1፡4-5 ባሉ ሌሎች ክፍሎችም የተረጋገጠ ነው።

እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መኖርዎ የሚመሠረተው፥ ስለ እርሱ በሚኖርዎ እውቀት በማደግዎ ላይ ስለሆነ፥ መጽሐፍ ቅዱስዎን ለመረዳት በሚፈልጉበት ጊዜ ሁሉ አንዳንድ ትምህርተ ሃይማኖታዊ ጥናት ማድረግ ይገባዎታል። ብዙ ያሠራዎ ወይም ያደክምዎ ይሆናል፤ ቢሆንም ብዙ መንፈሳዊ በረከቶችን ይሰበስቡበታል።

# 21

# የብሉይና የአዲስ ኪዳናት ግንኙነት

ክርስቲያኖች፥ በተለይም አዳዲሶቹ፥ መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት ሲፈልጉ፥ የብሉይ ኪዳን ትርጉምና ከአዲስ ኪዳን ጋር ያለው ግንኙነት እጅግ ታላላቅ ችግሮቻቸው ሆነው ያገኟቸዋል። ብዙ ክርስቲያኖች ብሉይ ኪዳን ግራ የሚያጋባ ስለሚሆንባቸው እሱን ለመረዳት የሚያደርጉትን ጥረት ያቋርጣሉ። ንባባቸው ሙሉ በሙሉ በአዲስ ኪዳን ላይ ያተኮረ ይሆናል፤ ከብሉይ ኪዳን የሚያነቡት ቢኖር ምናልባት መዝሙረ ዳዊትን ነው።

ይህ መልካም ወይም አስፈላጊ አሠራር አይደለም። እግዚአብሔር የሰጠን ሁለቱንም ኪዳናት የሚያጠቃልለውን አንድ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ብሉይ ኪዳንም የተሰጠን የእግዚአብሔር ቃል ነውና ልንረዳው እንችላለን። ክርስቶስ አንድ ጊዜ ለሁለት ደቀ መዛሙርቱ ብሉይ ኪዳንን አስረዳቸው (ሉቃስ 24)። ዛሬም ለኛ መንፈስ ቅዱስ ያስረዳናል። ታዲያ መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት እናጥናው?

## የአንድነት ነጥቦች

የብሉይ ኪዳንን ትርጉም ለመረዳት ተገቢ የሚሆነው መንገድ፥ አዲስ ኪዳን ብሉይን እንዴት እንደሚመለከተው መመርመር ወይም ማጤን ይሆናል። ይህ የሁለቱን ኪዳናት ግንኙነት እግዚአብሔር የሚያይበት መንገድ ነው። ታዲያ አዲስ ኪዳን በብሉይ ኪዳን ላይ ያለው እይታ ምንድነው? ለዚህ ጥያቄ የሚሆኑ መልሶችን በመጽሐፍ ቅዱስ በርካታ ምንባቦች ውስጥ እናገኛለን።

1. *ጸሐፊው ወይም ደራሲው እግዚአብሔር ነው።* በዕብራውያን 1፡1-3 መሠረት፥ እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካይነት ለአባቶች ተናገረ። የነቢያት ጽሑፎች በብሉይ ኪዳን ስለሚገኙ ብሉይ ኪዳን ከእግዚአብሔር ነው። 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡14-17 መላው መጽሐፍ ቅዱስ "የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት" ወይም እስትንፋሰ-እግዚአብሔር መሆኑን ይመሰክራል። ጢሞቴዎስ ከልጅነቱ ጀምሮ ያወቃቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ምን መሆ ናቸውን ስናስብና በነዚህ ጥቅሶች የተገለጠውን ስናሰላስል፥ ያ ቅዱስ መጽሐፍ ብሉይ ኪዳን መሆኑን እንገነዘባለን። ምክንያቱም በዚያ ዘመን አዲስ ኪዳን አልተሰበሰበም፥ በእግዚአብሔር ቃልነትም እውቅና አላገኘም

ነበርና። በመሆኑም እነዚህ ሁለት ምንባቦች፥ የብሉይ ኪዳን ምንጩ እግዚአብሔር መሆኑን ይገልጣሉ። በአዲስ ኪዳን ውስጥም ከዳር እስከዳር የሚታየው ገለጣ ወይም ሥዕል ይህ ነው። ሌሎች ጥቅሶች ወይም ንባቦችን ለመመልከት ከፈለጉ፥ የሐዋርያት ሥራ 28፡23፤ ሮሜ 1፡17፤ 9፡25፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 6፡2፥ 16ን ይመልከቱ።

2. *አንድ የቤዛነት እቅድ።* አዲስ ኪዳን፥ ብሉይ ኪዳን ከእግዚአብሔር መሆኑን መናገር ብቻ ሳይሆን፥ ከዚያም ይበልጥ የሚለው አለው። 2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡14-17ን እንደገና እንመልከተው። ጳውሎስ፥ ስለ ብሉይ ኪዳን ጠቀሜታ ምን ይላል? እነዚህ ቅዱሳት ጽሑፎች፥ ድንቅ የሆነ ነገር ሊሠሩ እንደሚችሉ ያስተምራል፤ በነርሱ አማካይነት "ደኅንነት የሚገኝበትን ጥበብ" (ቁ. 15) ልንማር እንችላለን። በሌላ አባባል እነዚህ ጽሑፎች የእግዚአብሔርን የቤዛነት እቅድ ያሳያሉ፤ ሰው ከኃጢአት የሚድንበትን ሁኔታ ያስታውቃሉ።

ሌሎቹ ምንባቦችስ ምን ይላሉ? በሮሜ 4፡1-9 ጳውሎስ ስለ አብርሃምና ዳዊት፥ መንፈሳዊ ልምምድ ይናገራል። በሁለቱም መካከል የነበረው የእውነት ተመሳሳይነት ምንድነው? በነርሱና በኛ ደኅንነት ወይም ቤዛነት መካከል ያለው ግንኙነትስ? እግዚአብሔር ያለ ሥራ ጽድቅን ቆጠረላቸው ይላል ጳውሎስ። በእምነታችን ወይም በእምነታችን አማካይነት በእርሱ ጸጋ ጸደቁ። እኛንም በተመለከተ ይኸው ነው። ሁለታችንም፥ ማለት እኛም ሆንን እነርሱ፥ ጽድቅን የምናገኘው በዚሁ አኳኋን ነው ይላል። እንግዲህ ይህ ምንባብ በጢሞቴዎስ መልእክት ካለው ጋር ተመሳሳይ የሆነ እውነትን ይገልጣል። በብሉይ ኪዳን ዘመን፥ በብሉይ ኪዳን መገለጥ አማካይነት ሰዎች የእግዚአብሔርን የቤዛነት እቅድ አወቁ። በዚህ ጉዳይ ሌሎች የአዲስ ኪዳን ክፍሎችን ሊያጠኑ ይችላሉ፦ የሐዋርያት ሥራ 24፡14-15፤ ሮሜ 4፡10-25፤ 8፡1-3፤ 11፡13-24፤ ገላትያ 3፡6-29፤ ያዕቆብ 2፡18-26። ብሉይ ኪዳን መዳን የምንችልበትን ሁኔታ ብቻ ሳይሆን፥ ከዚያም የበለጠ ይነግረናል። ከእግዚአብሔር ጋር ስለመመላለስም ያስተምረናል። (2ኛ ጢሞ. 3፡16-17፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡6፥ 11ን ይመልከቱ።) ለየዕለቱ ሕይወታችን መመሪያ የሚሆነን በጣም ጠቃሚ መንፈሳዊ እውነት አለበት።

3. *መካከሉ ክርስቶስ ነው።* አዲስ ኪዳን ስለ ብሉይ ኪዳን የሚገልጠውና ብዙ ሰዎችን የሚያስደንቅ ሌላም ነገር አለ። በብሉይ ኪዳን የተገለጠው ማን ነው? ብሉይ ኪዳን የደኅንነትን መልእክት መስጠት ብቻ ሳይሆን፥ በክርስቶስ ማንነት ላይም ያተኩራል። ከምጽአቱ በፊት የተጻፈ ሆኖ አሁንም የሚገልጠው ክርስቶስን ነው። በመሆኑም በአያሌ መንገዶች የተገለጠውን ክርስቶስን ለማየት ይቻለን ዘንድ ብሉይ ኪዳንን ማንበብ ይኖርብናል።

(ሀ) *በአንዳንድ ታላላቅ ሥራዎች።* ከነዚህ ታላላቅ ሥራዎች አንዱ የዓለም መፈጠር ነው። በዘፍጥረት 1 ላይ የክርስቶስ ስም አይታይም፤ ነገር ግን በዮሐንስ 1፡1-3፤ በቈላስይስ 1፡16 እና በዕብራውያን 1፡2 የተገለጠው ቃል ትርጉም ምንድነው? ክርስቶስ በመፍጠር ተግባር እንዴት እንደተሳተፈ በትክክል አናውቅ ይሆናል፥ ቢሆንም "ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና" የሚለው ይህ እውነት ግልጥ ነው። ስለዚህ ስለ ፍጥረት የሚናገሩ የብሉይ ኪዳን ክፍሎችን ስናስብ በውስጣቸው ክርስቶስን ማየት አለብን።

ክርስቶስ እያከናወናቸው ያሉ ሌሎች ሥራዎችንም ማሰብ እንችላለን። ለምሳሌ:- "ሁሉም በእርሱ ተጋጥሞአል" (ቈላ. 1፡17)። ይህ ተግባር ፍጥረተ ዓለምን መንከባከብን ወይም መደገፍን ያጠቃልላል።

(ለ) *በመታየት ወይም በመገለጥ።* ይህ "ቲያፈኒ" [Theophany] የሚባል ሲሆን፥ ትርጉሙም "የእግዚአብሔር መገለጥ ወይም መታየት" ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመናት እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ በሰው አምሳል ታይቷል። እግዚአብሔር እንደዚህ ባለው ሁኔታ በተገለጠ ጊዜ፥ በትክክል የታየው ክርስቶስ መሆኑን የሚጠቁም ማረጋገጫ አለ። ይህ ግን በዚያን ጊዜ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ነበር ማለት አይደለም። ለመገለጥ ሲል የሰውን መልክ (ቢያንስ የሰውን አምሳል) ያዘ ማለት ነው።

አንድ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል ዘፍጥረት 16ን ልንመለከት እንችላለን። "የእግዚአብሔር መልአክም" ለአጋር ይታያል (ቁ. 7)፤ ሥልጣኑም ግልጥ ነው (ቁ. 10)።

ይህ ማን እንደሆነ አጋር ትገነዘባለች (ቁ. 13)። በተጨማሪም ዘፍጥረት 22፡11-12፤ 31፡11-13ን ይመልከቱ።

ይህ አካል እግዚአብሔር እንደሆነ ለመረዳት እንችላለን፤ ታዲያ ለምንድነው እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ ማሰብ ያለብን? አንዱ ምክንያት:- ክርስቶስ የእግዚአብሔር መገለጥ ነው። ይህን ብዙ ክፍሎች ወይም ምንባቦች ያስተምራሉ። እንግዲህ እግዚአብሔር በሰው አምሳል ወይም አካል ራሱን በገለጠ ጊዜ የታየው፥ ክርስቶስ እንደሆነ መረዳት አለብን።

ሐ. *ሕዝበ እስራኤልን በማዳን።* ይህ ከእግዚአብሔር ታላላቅ ሥራዎች አንዱ ሲሆን፥ በኋላም እንደ እግዚአብሔር ኃይል ታላቅ ማረጋገጫነት ተጠቅሷል (ዘዳግም 6፡12፤ 7፡8፤ መሳ. 6፡8-10፤ መዝ. 81፡10፤ ኤር. 23፡7)። የእስራኤል ሕዝብ ከግብፅ ባርነት ነጻ ወጥተውና በበረሃው ምድር ተጉዘው በተስፋይቱ ምድር ተቀመጡ። ጳውሎስ የዚያን የማዳን ታሪክ ክፍል፥ በ1ኛ ቆሮንቶስ 10፡1-11 ይጠቅሳል። እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የነበረውን ግንኙነት አስመልክቶ እነዚያ ሁኔታዎች ብዙ

ያስተምሩናል (ቁ. 11)። በዚያ ታሪክ ውስጥ ክርስቶስ እንደነበረም ጳውሎስ ይጠቁማል (ቁ. 4)። የታሪኩ ጥልቅ ትርጉም ክርስቶስን ይመለከታል፦ በማዳን ሥራ ውስጥ ልናየው እንችላለን፤ ይህም እኛን የማዳኑ ሥራ ታላቅ ሥዕል ነው።

መ. *በግል ደኅንነት።* በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ግለሰቦችን ወደ እምነትና ታዛዥነት ለማምጣት በመሻት ይገናኛቸው ነበር። ብዙዎቹ እግዚአብሔርን በግል ሊያውቁት ችለዋል። አብርሃም፥ ዳዊት እና ሌሎች ብዙ ወንዶችና ሴቶች በእግዚአብሔር እምነት ኖረዋል (ዕብ. 11)። በመንፈሳዊ ረገድ ድነው ነበር፤ እንዲህ ያለው መዳን የሚገኘውም በክርስቶስ ሥራ አማካይነት ብቻ ነው። ሙሉ ታሪካዊ መገለጥ ባይኖራቸውም፥ ቅዱስ ቃሉን ለመረዳት አእምሯቸው ክፍት የሆነ ሁሉ፥ ስለ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በጊዜው ከእግዚአብሔር የተወሰነ እውቀት አግኝተዋል (ሉቃስ 24፡45-47)። የኃጢአት ሥርየት ሕግ በመሥዋዕት ተገልጦ ወይም ተስሎና በትንቢት ተነግሮ በእግዚአብሔር የታወጀ ነበር። መንፈሳዊ ብርሃን የበራላቸው የክርስቶስን ቀን ያዩ ከመሆናቸውም በላይ፥ ስለ ሥራውም የተወሰነ ፅንሰ-አሳብ ነበራቸው (ዮሐ. 8፡56)። እግዚአብሔርን ማወቅንና ከርሱ ጋር መራመድን ተማሩ (ዘፍጥ. 5፡22፤ 6፡9፤ ኢዮብ 19፡25)። ጠቃሚ ልዩነቶች ቢኖሩም የብሉይ ኪዳን ዘመን አማኞች፥ እንደ ክርስቲያኖች ሁሉ ዋነኛ በሆነ አንድ ዓይነት መሠረት ላይ የነበሩ መሆናቸውን ዕብራውያን 11 ግልጥ ያደርጋል። በቅዱስ ቃሉ ጥናት ስንገፋ ስለ ግንኙነቱ ይበልጥ እንማራለን።

ሠ. *በምስያ ወይም በዓይነቶች።* እነዚህንና ክርስቶስ የተገለጠባቸውን አንዳንድ መንገዶች ቀደም ሲል ተመልክተናል። (ምዕራፍ 15ን ይመልከቱ።)

ረ. *በቀጥተኛ ትንቢቶች።* እነዚህንም በአጭሩ ተመልክተናቸዋል። (ምዕራፍ 19ን ይመልከቱ።)

መላው መጽሐፍ ቅዱስ፥ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትንም ጨምሮ፥ በክርስቶስ የተማከለና ስለ እርሱም ምስክርነት ያለው ነው (ዮሐ. 5፡39)። እርሱ ራሱ ለደቀ መዛሙርቱ ከነዚያ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ስለ ራሱ አስተምሯቸዋል (ሉቃስ 24፡25-27)። ይህ ብቻ አይደለም፥ ስለርሱ ማወቅ የሚገባቸውን አስቀድመው ስላልተረዱ ገሠጻቸው። ስለዚህ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ተገልጦ ለማየት መሻት አለብን። ነገር ግን ስለርሱ ሙሉ መገለጥን የሚሰጠን አዲስ ኪዳን ነውና፥ በብሉይ ኪዳን የምናገኘውን ለማመሳከር ወይም ለማረጋገጥ ሁልጊዜ በአዲስ ኪዳን መጠቀም ይኖርብናል።

እነዚህ የመጀመሪያ ሦስት ነጥቦች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን መሠረታዊ አንድነት ያመለክታሉ፡- 1. ብሉይና አዲስ ኪዳን ከእግዚአብሔር ናቸው፤ 2. የማዳን እቅዱን ይገልጣሉ (ይህም በመሠረቱ አንድ እቅድ ነው) እና 3. ያ እቅድ በክርስቶስ የተማከለ መሆኑን ያመለክታሉ። የመዳን መንገድ ሁለት ወይም ሦስት ሳይሆን፥ አንድ ብቻ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጣል። ይህን ነው የተመለከትናቸው ክፍሎች በሚገባ የሚገልጡት።

## የማነጻጸሪያ ነጥቦች

አንዳንድ በብሉይ ኪዳን የሚገኙ ሁኔታዎች ከአዲስ ኪዳን መገለጥ ጋር በቀጥታ እንደሚነጻጸሩ አዲስ ኪዳን ያመለክታል። ሁሉም አንድ ዓይነት ባይሆኑ እንኳን ብዙ የማነጻጸሪያ ነጥቦች አሉ፡- ምናልባት ቢያንስ ሦስት የተለያዩ ዓይነቶች። አንደኛ፥ በመላው የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን ዘመናት፥ በእግዚአብሔር የተሰጠውን መገለጥ ጨምሮ፥ ንጽጽሮች አሉ። ሁለተኛ፥ በብሉይ ኪዳን ሕግ ወይም ከእስራኤል ጋር ብቻ በነበረው የብሉይ ኪዳን ቃል ኪዳንና፥ በአዲስ ኪዳን የአዲሱ ቃል ኪዳን መገለጥ መካከል ንጽጽሮች አሉ። ሦስተኛ፥ ደኅንነት በሥራ እንደሚገኝ እስራኤላውያን በተሳሳተ ሁኔታ በተረዱት የድሮው ኪዳንና፥ ይኸው ደኅንነት በእምነት በሚገኝበት የእግዚአብሔር መንገድ በሆነው የአዲስ ኪዳን መገለጥ መካከል ንጽጽር፥ እንዲያውም ቅራኔ አለ።

ሦስተኛው ዓይነት ንጽጽር በእግዚአብሔር በታቀዱ ሁለት ነገሮች መካከል አይደለም፤ በእግዚአብሔር እቅድና በሰው መረዳት መካከል እንጂ። በዚህ ምዕራፍ፥ የመጀመሪያዎቹ ሦስት ነጥቦች የሚያመለክቱት፥ እግዚአብሔር ሁለት ተቃራኒ የደኅንነት መንገዶች ወይም የሕይወት አቅጣጫዎች የሌሉት መሆኑን ነው። ስለዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሚገጥመን ስፍራ ለይተን ልናውቀው የሚያሻ ቢሆንም፥ አሁን ግን ከአይሁዶች መሳሳት ጋር ጊዜ ማባከን አይገባንም። (ሐዋ. 15፡7-11፤ ሮሜ 9፡30- 10፡13፤ እና ገላትያ 3 ስለዚህ ጉዳይ የሚናገሩ ምንባቦች ናቸው።) በአጠቃላይ የብሉይንና የአዲስ ኪዳንን ዘመናት ከሚያመለክቱ ንጽጽሮች በመነሣት፥ የመጀመሪያዎቹን ሁለት የንጽጽር ዓይነቶች እንመለከታለን።

1. *የአሮጌውና የአዲሱ ዘመናት*

*ዕብራውያን* 7፡16፥ 24፥ 28፤ 9፡10 ከጊዜ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ንጽጽሮች ያመለክታሉ። ብሉይ ኪዳን ጊዜያዊ ሲሆን፥ አዲስ ኪዳን ግን ዘላለማዊ ነው። ንጽጽሩም "ጊዜያዊ" በሆነውና "ቋሚ" ወይም "የመጨረሻ" በሆነው መካከል ነው።

ማርቆስ 1፡15 እና ገላትያ 4፡3-4ን ልብ ይበሉ። "የዘመኑ ፍጻሜ ደረሰ" የሚለው ቃል ትርጉም ምን ሊሆን ይችላል? ያልተፈጸመ ወይም የዝግጅት ጊዜ መሆኑን አያመለክትም? አዲስ ኪዳን የብሉይ ኪዳንን ዘመን የሚያየው እንደዚህ ዓይነት ዘመን አድርጎ ነው። ዓለምና የአይሁድ ሕዝብ ለክርስቶስ ምጽአት መዘጋጀት ነበረባቸው። በ'ዝግጅት' እና በ'ፍጻሜ' መካከል ንጽጽር አለ።

የአዲስ ኪዳን ብዙ ምንባቦች (ለምሳሌ ማቴ. 1፡22፤ 2፡17-18፤ 4፡14-16፤ ሐዋ. 3፡18፥ 21-24፤ 8፡32-35፤ 13፡27-29) በብሉይ ኪዳን የተነገረ ወይም የተጻፈ ጉዳይ እየተፈጸመ መሆኑን ይገልጣሉ። በ'ትንቢት' እና በ'ፍጻሜው' መካከል ንጽጽር አለ።

አንድ ሌላ ንጽጽር ደግሞ በሚከተሉት ጥቅሶች ውስጥ ይገኛል:- ማቴዎስ 10፡5-6፤ 15፡24፤ የሐዋርያት ሥራ 3፡26፤ 10፡34-35፤ 18፡5-6። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር በቅድሚያ የመረጠው ወይም የተገናኘው የትኛውን ሕዝብ ነበር? እነዚህ የአዲስ ኪዳን ጥቅሶች እግዚአብሔር በአሁኑ ዘመን ማንንም ሳይለይ፥ ሕዝቦችን በሙሉ በተመሳሳይ ሁኔታ እንደሚመለከት ያሳያሉ። እንግዲህ ንጽጽሩ በአንድ ሕዝብና በሁሉም ሕዝቦች ወይም በአይሁዶች ብቻና አይሁዶችና አሕዛብ በአንድነት በሆኑበት ሁኔታ መካከል ነው ለማለት እንችላለን።

አሁንም ሌላ ግልጥ ንጽጽር በዕብራውያን 7፡19፤ 9፡15፤ 10፡4-7፥ 10፥ 14፤ 11፡39-40 ልናይ እንችላለን። ይህ ንጽጽር "ከፊል" ወይም ጎዶሎ በሆነውና "ምሉዕ" ወይም ፍጹም በሆነው መካከል ነው። ይህ ፍጹምነት ወይም ጎዶሎነት በአሁኑ ጊዜ ኃጢአት የለሽ ፍጹምነት ያለ የሚያስመስል ወይም በቀጥታ ኃጢአትን የሚመለከት አይደለም። እግዚአብሔር በዘመኑ ውስጥ ያለውን እቅድ ፍጻሜ ነው የሚያመለክተው።

## 2. አሮጌውና አዲሱ ኪዳናት

አጠቃላይ ዘመናትን ከሚመለከቱት ከላይ የተጠቀሱ ንጽጽሮች በተጨማሪ፥ አሮጌውንና አዲሱን ኪዳናት በተለይ የሚያመለክቱ ጥቂት ንጽጽሮች እንዳሉ ለመገንዘብ እንችላለን።

ዕብራውያን 8፡5፤ 9፡10-11፤ 12፡18-24ን ይመልከቱ። በዚህ ስፍራ የብሉይ ኪዳን "ምድራዊው" (ወይም ቁሳዊው) ምዕራፍ "መንፈሳዊ" ከሆነው የአዲስ ኪዳን አቻዎቹ ጋር ተነጻጽሯል። ወደፊት ወይም ወደ ላይ፥ ማለት ወደ መንፈሳዊ እውነቶች ያመለከቱ ሁኔታዎች ወይም ገጽታዎች ነበሩ። ይሁን እንጂ ንጽጽር ፍጹም አይደለም፤ ዕብራውያን 11፡10፥ 16 እና ሌሎችም ክፍሎች የብሉይ ኪዳን ዘመን

አማኞች መንፈሳዊና ሰማያዊ ግቦች እንዲሁም ተስፋዎች እንደነበሯቸው ያሳያሉ።

አንድ የላይኛው ቀጥተኛ ተቃራኒ የሚመስል ንጽጽር መኖሩ እንግዳ ነገር ነው። (ዕብ. 8፡2፥ 5፤ 10፡1፤ ቈላ. 2፡16-17ን ይመልከቱ።) የብሉይ ኪዳን ምድራዊ ሁኔታዎች የ'እውነተኛው'፥ ወይም 'ትክክለኛው'፥ "ጥላ"፥ ወይም 'ቅጅ'፥ ናቸው ይባላል። እውነተኛው በሰማይ ያለ ነው፤ ሆኖም በአዲስ ኪዳንም ተገልጧል። ድንኳኑ በሰማይ ካለውና አሁን ከምንለማመደው መንፈሳዊ እውነት፥ ማለትም የእግዚአብሔር መኖሪያ ወይም ማደሪያ ጋር ይነጻጸራል።

ይህ በሙሴ ሥነ-ሥርዓታዊ ሕግ በግልጥ ተመልክቷል። መሥዋዕትን የማቅረብ (ዘሌዋ. 1-8)፥ በዓላትን የማክበር (ዘሌዋ. 23)፥ የመገናኛውን ድንኳን የመሥራት (ዘጸ. 25-28) እና ሥነ-ሥርዓቱን መከታተል (ዘጸ. 29-30) ዋናዎቹ ክፍሎች ናቸው። እንዲሁም፥ ማሕበራዊና አስተዳደራዊ ሕጎች አሉ (ለምሳሌ፦ ለምፅን በተመለከተ፥ ዘሌዋ. 13 እና ብድርንና ባርነትን በተመለከተ፥ ዘሌዋ. 25)። እነዚህን ሕጎች ለምን አንከተላቸውም? ምክንያቱም እንደ ዕብራውያን 9፡11-14፤ 10፡1-10 ያሉትን የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ስለምናነብና፥ ሕጉ ክርስቶስ የመሠረተው መንፈሳዊ እውነት ጥላ ስለሆነ፥ እንዲሁም ያን ጥላ እግዚአብሔርም የደመሰሰው መሆኑን ስለምንረዳ ነው። ያን እውነት ነው አሁን ለመከተል የምንፈልገው። አንድ የተወሰነ የብሉይ ኪዳን ሕግ ወይም ክፍል የጥላው አካል ብቻ ወይም ቋሚ ተቀባይነት ያለው ነው ብሎ ለመወሰን ሁልጊዜ ቀላል አይሆን ይሆናል። ሆኖም በጥናቱ ይበልጥ ስንገፋበት እግዚአብሔር ስለነዚህ ነገሮች ማስተዋልን ይሰጠናል።

ሦስተኛውን ንጽጽር በኤርምያስ 31፡31፥ 34፤ ሮሜ 8፡3 እና ዕብራውያን 7፡18 ላይ እናስተውላለን። ይህ በ'ድካም'ና በ'ብርታት' መካከል ያለ ንጽጽር ነው። ይህ ማለት የእግዚአብሔር ኃይል በብሉይ ኪዳን አልተገለጠም ማለት አይደለም። ብዙ ጊዜ እንደተገለጠ ቅዱስ ቃሉ ይመሰክራል። ነገር ግን እግዚአብሔር የሰጠው ሕግ ድካም ነበረበት፦ ይኸውም ሰው ሊጠብቀው አለመቻሉ ነው። ያ እውነት ሕጉን ከአዲስ ኪዳን ጋር የማነጻጸሪያ መሠረት ነው። ይኸውም እግዚአብሔር ሕጉን በሰዎች ልብ ሲያኖር፥ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ሕጉን ለመጠበቅ የሚችሉበት ይሆናል።

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች በብሉይና በአዲስ ኪዳን መካከል ሌላ ንጽጽር ያያሉ፤ ይኸውም ብሉይ የ'ሕግ' ሲሆን አዲስ ኪዳን የ'ጸጋ' ነው የሚል ይሆናል። ስለዚህ አሥርቱ ትእዛዛት የብሉይ ኪዳን

አካል፥ ምናልባትም ምሰሶው ስለሆነ፥ እኛ እንደ አማኝነታችን ስለነርሱ የሚያገባን ምንም ነገር የለም ብለው ይደመድማሉ።

ይህን ጥያቄ እንዴት እንፍታው? እነዚህን ጥቅሶች በማጥናት፥ ይሆናል፦ ማቴዎስ 15፡3-7፤ 19፡17-18፤ ማርቆስ 10፡19፤ ሉቃስ 4፡8፤ 11፡2፤ ሮሜ 1፡23፤ 2፡24፤ 13፡9፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 5፡11፤ 8፡5-6፤ 10፡14፤ ኤፌሶን 4፡25፥ 28፤ 5፡3፤ 6፡1-3፤ ቈላስይስ 3፡5፥ 9፤ 1ኛ ተሰሎንቄ 1፡9፤ 1ኛ ጢሞቴዎስ 6፡1፤ ያዕቆብ 2፡10-11፤ 4፡2፤ 1ኛ ዮሐንስ 5፡21፤ ራእይ 13፡6፤ 22፡9።

እነዚህ ጥቅሶች ከአሠርቱ ትእዛዛት መካከል ዘጠኙ በአዲስ ኪዳን፥ በተለይም በመልእክቶቹ መጠቀሳቸውን ያሳያሉ። በመሆኑም ለኛ የተሰጡ የእግዚአብሔር ሕግጋትና የአዲሱ ቃል ኪዳን አካል ናቸው። እግዚአብሔር ሕግጋቱን እንድንታዘዝ ይፈልጋል። ያልተደገመውና አራተኛ የሆነው ንጽጽር፦ "የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ" የሚል ነው። የመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ሰንበትን ታከብር ነበርን? የመጀመሪያውን ሰንበት በቀጣይነት ለማክበሯ አንድም ማረጋገጫ የለም። ክርስቲያኖቹ የሳምንቱን መጀመሪያ ቀን ያከብሩ እንደነበር ግን አንዳንድ ማስረጃዎች ያመለክታሉ። (ሐዋ. 20፡7፤ 1ኛ ቆሮ. 16፡2ን ይመልከቱ።)

ስለዚህ አሠርቱ ትእዛዛት በሕግ የተሰጡት ለአይሁዶች ቢሆንም፥ ያለጥርጥር እግዚአብሔር ለሁሉም ሕዝቦቹ የሰጣቸው ቋሚ መሰፈርት ናቸው። በአራተኛው ንጽጽርም ምንም እንኳን ትእዛዙ በአንድ ዓይነት መልክ ባይደገም "የጌታ ቀን" ቋሚ መመሪያ በመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ዘንድ የተሠራበት ይመስላል። በፍጥረት ክንውን ወቅት ሰባተኛው ቀን በእግዚአብሔር ተቀድሶ እንደነበር እናስታውሳለን። ይህ የሆነው ሕግ ከመሰጠቱ እጅግ ቀድሞ ነው። ስለዚህ ከጸጋ በታች ብንሆንም "ከክርስቶስ ሕግ በታች" (1ኛ ቆሮ. 9፡21) ነን፤ በመሆኑም ቋሚ የሆነው የእግዚአብሔር የሥነ-ምግባር (ሞራል) ሕግ ለኛም ዛሬ የእግዚአብሔር ፈቃድ ናቸው (በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ 22 ቁጥር 1ን ይመልከቱ)።

ብዙ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ የሚያዩት ሌላ ንጽጽር አለ፤ ይኸውም የብሉይ ኪዳን የሥነ-ምግባር ሥርዓት ከአዲስ ኪዳን ሥርዓት ጋር የማይስማማ ነው የሚል ነው። የብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች ለአዲስ ኪዳን ደረጃ ብቁ አለመሆናቸው ብቻ ሳይሆን፥ አንዳንድ ጊዜም ስለ ጠባያቸው በእግዚአብሔር የማይገሰጹም ነበሩ።

ከአንዳንድ ሁኔታዎች ሲታይ በእግዚአብሔር የተሰጡት ሕግጋት ከአዲስ ኪዳን ሕግጋት ዝቅ ያሉ ይመስላል። ለምሳሌ፥ እስራኤላውያን አማሌቃውያንን ፈጽመው እንዲያጠፉ እግዚአብሔር አዟቸዋል (ዘጸ.

17፡8-16)። ሌሎች ሕዝቦችም መደምሰስ ነበረባቸው (በዘጸአት 34፡12-16 እና በዘዳግም 7፡1-5 እንዳለው)። እስራኤላውያን ከፍልስጤማውያን ጋር ስምምነት እንዳያደርጉ፥ ነገር ግን እንዲገሏቸውና ከአገር እንዲያስወጧቸው ተነግሯቸው ነበር (ዘጸ. 23፡23-33)። በአንዳንድ ሁኔታዎች ሴቶችና ሕጻናት እንኳን እንዲገደሉ ሲያዝ (ዘዳግም 20፡16-18)፥ እግዚአብሔር እስራኤላውያን ያልሆኑ ሕዝቦችን በጭካኔ ያያቸው ይመስላል። በማንኛውም ሁኔታ ይህ ድርጊቱ ለመላው ዓለም ፍቅሩንና ምሕረቱን ከገለጠበት ሁኔታ ጋር የሚጣጣም አይመስልም። ይህን ችግር እንዴት ነው የምንረዳው?

በመጀመሪያ የተደመሰሱት ሕዝቦች በምግባራቸው የረከሱ ነበሩ፤ የቅድስና ሕግ ወይም ሥርዓትና እውነተኛ አምልኮ አልነበራቸውም። እግዚአብሔር አንድን ሕዝብ ከሌላው ይበልጥ ስለወደደ፥ ያ ሕዝብ ታላቅ ስለሆነ ወይም ከሌላ ሕዝብ የተሻለ ስለሆነ አይደለም ሊቀድሰው የፈለገው። (ዘዳግም 7፡7ን ይመልከቱ።) እርግጥ እግዚአብሔር እስካስተማራቸው ድረስ እስራኤላውያንም ቢሆኑ ያለ ሕግ ወይም ሥርዓት ነበሩ። ነገር ግን ይህን ሕዝብ ብቻ ለቅድስና ስለመረጠው ሕዝቡ በአካባቢው ካለው ርኩሰት ሁሉ መለየት ነበረበት።

ከዚያም ሌላ እግዚአብሔር ሌሎች ሕዝቦችንም ለረጅም ጊዜ ታግሷቸዋል። እስራኤላውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር ከመመለሳቸው እጅግ አስቀድሞ እግዚአብሔር፡- "የአሞራውያን ኃጢአት ገና አልተፈጸመምና" (ዘፍጥ. 15፡16) ብሏል። ይህ ጥቅስ አንድ ሕዝብ ንስሐ ገብቶ ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ ፈቃደኛ በማይሆንበት ጊዜ ኃጢአት መፈጸሙን ያስረዳል። እስከዚያ ጊዜ ድረስ እግዚአብሔር ታጋሽ ነውና ይጠብቃል። ያ ነጥብ ወይም ጊዜ ሲደርስ ግን ይቀጣል። በአንዳንድ ሁኔታዎች አንድ ሕዝብ ሌላውን በጦርነትና በመግደል እንዲያጠፋው በማድረግ ቀጥቷል። በእስራኤል ጠላቶች ላይም ይህን ማድረግ ነበረበት። ምክንያቱም ይህን ካላደረገ እስራኤልን በማርከስ ተግባራቸው ይገፉበታል። በትክክል የተደረገው ይህ መሆኑን ዘኁልቁ 25፡1-2፤ 31፡1-20 እና መሳፍንት 2፡1-4 በግልጥ ያሳያሉ። እስራኤላውያን እነዚህን ጠላቶቻቸውን ስላላጠፏቸው ከጠላቶቻቸው የተነሣ ራሳቸው ረከሱ።

እንግዲህ እስራኤላውያን በጠላቶቻቸው ላይ የበቀል እርምጃ መውሰዳቸው፥ ወይም እግዚአብሔር ማድላቱ አይደለም። ይህ የእግዚአብሔር ተግባር አንድን የተበከለ ወይም የታመመ የኅብረተሰብ ክፍል ለማስወገድ መደረግ ያለበት ቀዶ ሕክምና ነው። (በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ 18 ቁጥር 3 ላይ "የእርግማን መዝሙሮች" ተብለው ስለሚጠሩት መዝሙሮች የተገለጠውን ይመልከቱ።)

ሌላው እንቆቅልሽ በብሉይ ኪዳን ጊዜ እግዚአብሔር ከአንድ በላይ ጋብቻንና "ቀላል" ፍችን ፈቅዶ አሁን የከለከለበት እውነታ ነው። እንደ አብርሃምና ዳዊት ያሉ መንፈሳዊ መሪዎች ከአንድ በላይ በአንዳንድ ሁኔታዎች ከዚያም የበዙ ሚስቶች ነበሯቸው። ቢሆንም ይህ ድርጊት ስሕተት ሆኖ የተቀጡበትና በእግዚአብሔር የተገሠጹበት ሁኔታ ያለ አይመስልም። እስራኤላውያን ወንዶች "የፍች ጽሕፈት" በመስጠት ብቻ ከሚስቶቻቸው እንዲለዩ እግዚአብሔር ፈቅዶላቸዋል (ዘዳግም 24፡1-4)።

ይህ እውነተኛ ችግር ቀላል መልስ የለውም። ቢሆንም ከማቴዎስ 19፡3-9 ፍንጭ ልናገኝ እንችላለን። እግዚአብሔር ለምን በብሉይ ኪዳን ጊዜ መፍታትን እንደፈቀደ ክርስቶስ በዚያ ስፍራ ያስረዳል። ክርስቶስ መፋታት የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ዕቅድ ነበር ይላል? አይልም። ታዲያ እንዴት ነው ያ የመጀመሪያ ዕቅድ ከአዲስ ኪዳን ዕቅድ ጋር የሚነጻጸረው? ክርስቶስ መልሱን በዝርዝር ባይገልጥም፥ እግዚአብሔር ካንድ ዕቅድ በላይ እንዳልነበረው ያመለክታል። ይልቁንም እርሱ ከመጀመሪያው አንድ ወንድ ለአንድ ሴት የሚል ታላቅ መሥፈርት ወይም የጋብቻ ሥርዓት ነበረው።

በብሉይ ኪዳን ዘመን፥ ለምን ይህን ዝቅተኛ የሥነ-ምግባር ደረጃ ዝም አለ? "ስለልባችሁ ድንዳኔ" አለ ክርስቶስ። ማለትም ሰዎች ያን ከፍ ያለ ደረጃ፥ መቀበሉ አልሆነላቸውም ነበር። ይበልጥ ጠቃሚ የሆኑ የሕይወትና የአምልኮ ሥርዓቶችን በመማር ላይ ነበሩና፥ እግዚአብሔርም ሌሎች ነገሮችን አልፈለገባቸውም። እንደ ሕጻናት ቀስ በቀስ ነው ያስተማራቸው። ሥርዓቱ አልተለወጠም፤ ቢሆንም እጅግ ከፍተኞቹን ወይም የርሱ መሥፈርት ያልሆኑ ነገሮችን ግን ለጊዜው ፈቅዷል።

የትርጓሜ ችግሮችን የሚያስከትሉ ሌሎች የብሉይ ኪዳን ዘመን የሥነ-ምግባር መሥፈርቶችና ሁኔታዎች አሉ። እነዚህን ቀደም ሲል ከተመለከትናቸው ጉዳዮች ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ ልንረዳቸው እንችላለን። ባጠቃላይ፥ የብሉይ ኪዳንን ሥነ-ምግባራዊ ሥርዓቶች ከአዲስ ኪዳን ሥነ-ምግባር ሥርዓት ጋር ለማነጻጸር አንዳንድ መሠረታዊ መርሆችን ልናስተውል እንችላለን።

ሀ. *እግዚአብሔር ፈቃዱን ለሰው የገለጠው በተከታታይ ወይም በማያቋርጥ መንገድ ነው፤* በኋላ በክርስቶስና በሐዋርያቱ አማካይነት እንደገለጠው፥ በቀድሞዎቹ ዘመናት መሥፈርቶቹን ሙሉ በሙሉ አልገለጠም ነበር። (ማቴ. 5፡27-28 እና ዕብ. 1፡1-2ን ይመልከቱ።)

ለ. *በብዙ ሁኔታዎች የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን የፈጸሙት፥ እግዚአብሔር እንዲያደርጉ የነገራቸውን ነበር ማለት አይቻልም።* እኛ እንደምናደርገው እነርሱም አንዳንድ ጊዜ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ዞር ይሉ

ነበር። (1ኛ ነገሥት 10፡23፥ 26፤ 11፡1-3ን ከዘዳግም 17፡16-17 ጋር ይመልከቱ።)

ሐ. *እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ ያልፈቀዳቸው ነገሮች ሲፈጸሙ ዝም ብሏል ወይም አልከለከለም።* በሌላ አባባል ያልተስማማባቸውን ነገሮች ዝም ብሏቸዋል። በአንዳንድ ሁኔታዎች እግዚአብሔር ያለመፍቀዱም አልተጻፈም (ማቴ. 19፡3-9)።

መ. *የብሉይ ኪዳን ሥነ-ግጥም፥ ጠንካራ አንዳንድ ጊዜም በዘይቤያዊ አነጋገር ስለ እግዚአብሔር ክብርና ስለ እውነት ከመቆርቆር የተነሣ የተነገረ ስለሆነ፥ እንደተራና ቀጥተኛ አባባል ተቆጥሮ ትርጓሜ ሊሰጠው አይገባም።* (መዝ. 58፡6ን ይመልከቱ።)

ይህ ሁለቱ ኪዳናት ስላላቸው ግንኙነት በአጭሩ የተደረገ ቅኝት ነው። ታዲያ ብሉይ ኪዳንን እንዴት እንመልከተው? መልሱን አዲስ ኪዳን ያስተምረናል። ብሉይ ኪዳንን እንደ እግዚአብሔር መገለጥ እናየዋለን፤ ልክ የአዲስ ኪዳንን ያህል ለኛ የእግዚአብሔር ቃል ነው። የእግዚአብሔርን የማዳን ዕቅድ ማለትም፥ እርሱ ወንዶችና ሴቶችን በጸጋው የሚያድንበትንና ክርስቶስን እንዲመስሉ የሚያደርግበትን መንገድ እናይበታለን። ስለዚህም ብሉይ ኪዳን ክርስቶስን በተለያዩ መንገዶች ይገልጥና ምጽአቱን ያዘጋጃል። ይህ የሁለቱ ኪዳናት አንድነት ብዙ የብሉይ ኪዳን ክፍሎችን እንድንረዳ ያግዘናል።

ንጽጽሮቹም አሉ። ቸል ብለንና ልዩነት እንደሌላቸው በመቁጠር ባንድ ላይ ልንጠቀልላቸው አይገባም። ያሉትን የንጽጽር ዓይነቶች ለመገንዘብ አዲስ ኪዳን ይረዳናል። ስለዚህ ጊዜያዊ ሁኔታዎችንና ቋሚ ሥርዓቶችን ብሉይ ኪዳን ውስጥ ለማግኘት እንተጋለን። እናም ከእግዚአብሔር ጋር ለሚኖረን ግንኙነት ያበራልን ዘንድና በጸጋው ለማደግ እናነበዋለን።

# 22

# ለእግዚአብሔር ቃል መልስ መስጠት

ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ትርጓሜ ብዙ አጠቃላይና ልዩ መመሪያዎችን ተመልክተናል። የመጽሐፍ ቅዱስን ጥናት በተገቢው ትኩረት ለመጀመር እንደጓጉ ተስፋ አደርጋለሁ። ከዚያ በፊት ቃሉን በትኩረት ስለመመልከት የተሰጡ አሳቦችን እያስተዋሉ ምዕራፍ ስድስትን እንደገና ቢያነቡ በጣም ይጠቅምዎታል።

ጥናቱ ከመጀመሩ በፊት የእግዚአብሔርን ቃል የማወቅን ትክክለኛ ግብ በጥንቃቄ ማሰብ ይገባናል። እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን የሰጠን ለምን ዓላማ ነው? ቃሉ ራሱ ይነግረናል። የእግዚአብሔር ልጆች እንድንሆንና ለክብሩም እንኖር ዘንድ ነው። መጽሐፍ ቅዱስዎን የመረዳትዎ የመጨረሻ ግብ ለእግዚአብሔር ክብር መኖር ነው።

አንድ ሰው በንድፈ አሳብና በቴክኒካዊ ጥናቱ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ ብዙ ሊማር ይችላል። ነገር ግን እውነተኛ መረዳት የሚመጣው አንድ ሰው እግዚአብሔር በቃሉ አማካይነት ለሚገለጠውና ለሚፈልግበት ነገር መልስ ሲሰጥ ብቻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋውን በአእምሮ በመተንተን ሳይሆን፥ አንድ ሰው እግዚአብሔር ሲናገረው መልስ በሚሰጥበት ጊዜ ብቻ የሚታወቅ መንፈሳዊ አቅጣጫ አለው።

ለምሳሌ ሮሜ 12፥1 ምን ይላል? ስንተነትነው፥ "እንግዲህ" የሚለው ቃል እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ለኛ ያለውን ጸጋ የሚናገሩትን የመጀመሪያዎቹን አሥራ አንድ ምዕራፎች ወደ ኋላ እየተመለከተ መሆኑን ልናይ እንችላለን። እነዚህ ምዕራፎች የጳውሎስ ልመና የተመሠረተበትን ነገር ያሳያሉ። "መሥዋዕት" እና "ሕያው" የሚሉትን ቃላት ሙታን ከነበሩት የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች ጋር በማያያዝ እናጠናቸዋለን። መሥዋዕት ማለት ለእግዚአብሔር በፍጹም መሰጠት መሆኑን አውቀን፥ በመሞት ሳይሆን በመኖር ሕይወታችንን ለእግዚአብሔር መስጠት እንደሚኖርብን እንረዳለን። ቋንቋው የሚገልጣቸውን ሌሎች የትርጓሜ ነጥቦችና ደረጃዎችም ልብ ልንል እንችላለን። ይህ ሁሉ ግን ፍጹም ንድፈ አሳባዊ ልምምድ ከሆነ ምንባቡን በትክክል አልተረዳነውም። ሮሜ 12፥1 ላይ ያለውን ቃል በሙሉ

ለመረዳት፥ የቃሉን ትርጉም መረዳት ብቻ ሳይሆን፥ ራሳችንንና መላው ሰውነታችንን ለጌታ መስጠት ይገባናል።

በ2ኛ ቆሮንቶስ 3፡6 ላይ "ፊደል ይገላል" የሚል እናነባለን። ይህ ማለት የእግዚአብሔርን ትእዛዛትና ሕግጋት ሳንከተል መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ፥ ለማጥናት እና ለማወቅ ብንሞክር፥ ልባችን ለእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳይገዛ ይደነድናል ማለት ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ሁልጊዜ መንፈሳዊ ፈተና አለው። ስለሆነም መጽሐፉ የእውቀት ቅርንጫፍ እንደሆነ ሌላ መጽሐፍ መጠናት ያለበት አድርገን ከማሰብ መጠንቀቅ ይኖርብናል።

በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስ የሚጠይቃቸው ጉዳዮች፥ አማራጮች ሳይሆኑ በሥልጣን የሚቀርቡ ናቸው። እግዚአብሔር አሳብ አያቀርብልንም። "ይህን ልታደርግልኝ ትፈቅዳለህ?" በማለት አይለማመጥም። "ይህን ፈጽም!" ብሎ ያዘናል። ያለን ብቸኛ አማራጭ መታዘዝ ወይም አለመታዘዝ ሲሆን፥ መታዘዝ ደግሞ ለመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ቁልፍ ነው።

